ሕዳር 2007

አዲስ አበባ

# ብሔርን መሠረት ያደረገው የህወሃት/ኢሕአዴግ ፌደራሊዝም ለኢትዮጵያ ይበጃል?

በአብነት ዘገየ

ማውጫ


| ማውጫ | ገጽ |
|---|---|
| 1 የብሔርን ጉዳይ የሚመለከቱ አንዳንድ ሃሳቦች ............ | 1 |
| 1.1. የኢትዮጵያ አመሠራረት ............ | 1 |
| 1.2. የኢትዮጵያ የቀድሞ መንግስታትና የብሔር ጥያቄ ............ | 7 |
| 1.3. የብሔር ጭቆና በኢትዮጵያ? ............ | 9 |
| 1.4. በኢትዮጵያ ሰፍኖ ለቆየው የጭቆና አገዛዝ የወቅቱ የአገሪቱ ልሂቃን የሰጡት ምላሽ. | 11 |
| 1.5. አማራ ጨቋኝ ብሔር ሌሎቹ የኢትዮጵያ ብሔሮች ተጨቋኝ ብሔሮች? ............ | 13 |
| 2 ብሔር ተኮር ፌደራሊዝምን ወደኢትዮጵያ ማን አመጣው? ለምን? ............ | 16 |
| 2.1. የ1960ዎቹ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ንቅናቄ ............ | 16 |
| 2.2. የህወሃት አቋም ............ | 19 |
| 2.3. ህወሃት አቋሙን (ከጥቅሙ አንፃር አይቶ) የኢትዮጵያ ሕግ ስለማድረጉ ............ | 21 |
| 2.4. ህወሃት ብሄር ተኮር የፌደራል አደረጃጀትን ለምን መረጠ ............ | 23 |
| 2.5. የህወሃት/ኢ.ሕአዴግ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ............ | 25 |
| 3 በአምባገነኑ ህወሃት/ኢ.ሕአዴግ የተጫነብን ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ውጤቶች ...... | 32 |
| 3.1. የህወሃት/ኢ.ሕአዴግ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ውጤቶች ............ | 32 |
| 3.2. የብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ተጠቃሚው ማነው? ............ | 45 |
| 4 ለኢትዮጵያ የሚበጁ ብሔር ተኮር ያልሆኑ አማራጮች ............ | 46 |
| 5 ማጠቃለያ ............ | 60 |
| 6 ዋቢ ጽሑፎች ............ | 67 |


የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የህወሃትን ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ጥቅሞችና ጉዳቶች ማሳየትና የተሻሉ አማራጮችን መጠቆም ነው፡፡ህወሃትና የግል ጥቅማቸውን የሚያስቀድሙ ብሄር ተኮር ልሂቃን የስርዓቱ ዋና ተጠቃሚዎች ሲሆኑ ሕዝቡ ግን ተጎጂ መሆኑ ተብራርቷል፡፡በመሪዎቻችን ገደብ የለሽ ስልጣን ምክንያት (የየትኛውም ብሔር ተወላጅ የሆኑ) ኢትዮጵያውያን (ከብሔር ጋር የተያያዙትን ጨምሮ) ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን የሚያስከብሩበት ምቹ ሁኔታ ተፈጥሮላቸው አያውቅም፡፡ ስለሆነም ለታሪካዊ ችግሮቻችን ሁሉ መፍትሔው የሚገኘው የብሔር ጭቆናን ለብቻ በመነጠል ሳይሆን የጭቆናዎቹን ዓይነቶችና ውስብስብነት አገናዝቦ ለሁሉም ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ነው፡፡ይህን ለማሳካት አገራዊ ብሔርተኝነት ላይ ያተኮረ፣ የመዋሃድ ግፊት የማያደርግ፣ በማንነት ልዩነት ላይ ያልተመሰረተና የሁሉንም ዜጎች መሠረታዊ መብቶች በእኩልነት የሚያስከብር ዴሞክራሲያዊ የፌደራል መንግስት ስርዓት እንደሚያስፈልግ ተመልክቷል፡፡

# ብሔርን መሠረት ያደረገው የህወሃት/ኢሕአዴግ ፌደራሊዝም ለኢትዮጵያ ይበጃል?

ፌደራላዊ የሆነ የመንግስት ሥርዓት አወቃቀር ለኢትዮጵያ ጠቃሚ መሆኑን በርካቶች ይስማሙበታል፡፡ አከራካሪው ጉዳይ የፌደራላዊው መንግስት ስርዓት በምን መስፈርት ላይ መመስረት አለበት የሚለው ነው፡፡ የህወሃትን[1] ስልጣን መቆናጠጥ ተከትሎ የወጣው የ1987ቱ ሕገ መንግስት የፌደራሉ ሥርዓት አባል የሆኑትን ክልሎች ለማዋቀር መሠረት ያደረገው ብሔርን (ዘርን)[2] ነው፡፡

ይህ የብሔር መስፈርት አወዛጋቢ ሆኖ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የፌደራሉ መንግስት አካል የሆኑት ክልላዊ መንግስታት እንዲከፋፈሉ የተደረገበትን የብሔር መስፈርት ጥቅምና ጉዳቶች ማሳየትና የተሻሉ አማራጮችን መጠቆም ነው፡፡

## 1. <u>የብሔርን ጉዳይ የሚመለከቱ አንዳንድ ሃሳቦች</u>

### 1.2. <u>የኢትዮጵያ አመሠራረት</u>

ኢትዮጵያ በዓለም ካሉት ጥንታዊ አገሮች መካከል አንዷ እንደሆነች ይነገራል፡፡ የታሪክ ተመራማሪ የሆኑት ዶ/ር ተሻለ ጥበቡ ‹‹The Making of Modern Ethiopia›› በሚለው መጽሐፋቸው ላይ እንዳሰፈሩት ኢትዮጵያ የምን ያህል ጊዜ ታሪክ አላት ለሚለው ጥያቄ ምላሹ የኢትዮጵያ ታሪክ ቆይታ አጥኚው እንደፈለገው ሊሆን እንደሚችል ይጠቁማሉ፡፡[3] ይህንን ያሉትበት ዋና ምክንያት የኢትዮጵያን ታሪክ የሚተነትኑ የታሪክ ተማራማሪዎች የሚጠቀሟቸው የተለያዩ የጊዜ ሰሌዳዎች በመኖራቸው ነው፡፡[4]

የኢትዮጵያን ታሪክ ቆይታ በሚመለከት የተለያዩ ሰዎች የተለያየ አቋም መያዝ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ኢትዮጵያ እንደአገር የተፈጠረችው እንደማናቸውም የዓለም አገራት[5] በጦርነት፣

በፍልሰትና አገር በመገንባት ሂደት መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡ የጦርነቶቹ ዓላማም የፖለቲካ ስልጣን መያዝና ግዛት ማስፋት ነበረ፡፡

ታሪክ መመዝገብ ከተጀመረበት ጊዜ በፊት (prehistory) የሰዎች መኖሪያ የነበሩት የኢትዮጵያ ዝቅተኛ ቦታዎች (lowlands) እንጂ ከፍ ያሉት ሜዳማ ቦታዎች (plateau) እንዳልነበሩ ይገመታል፡፡[6] በውል ባልታወቀ ዘመን (ምናልባትም ከደቡብ አረቢያ የመጡ) የሃም (ብዙ ጊዜ ኩሽ ተብለው የሚጠሩ)[7] ሕዝቦች በወረራ ሜዳማዎቹን ቦታዎች በመያዝ ከነባር ጥቁር ሕዝቦች ጋር ተቀላቅለው መዋለዳቸው ይነገራል፡፡ እነዚህ ሃሞች ካካተቷቸው መካከል ቤጃ፣ቤኒ አመር፣ቢለን[8]፣አገው፣የተለያዩ የሲዳማ ጐሳዎች ወዘተ… ይገኙበታል፡፡[9]

ከዚህም ሌላ በትግሬ፣በአማራ፣በጐጃሜ እና በሸዋ ሰዎች ላይ 80 በመቶ የሆነ የሃም ደም እንዳለ ይነገራል፡፡[10] ሌሎቹ ሃሞች ደግሞ እንደናይሎቲክ ቋንቋ ካላቸው ጥቁር ሕዝቦች ጋር ተዋልደዋል፡፡[11]

***ኢትዮጵያ እንደአገር የተፈጠረችው እንደማናቸውም የዓለም አገራት በጦርነት፣ በፍልሰትና አገር በመገንባት ሂደት መሆኑን መካድ አይቻልም፡፡***

*ከክርስቶስ ልደት በፊት* በነበረው 7ተኛው ክፍለ ዘመን የሴም ሕዝቦች ወደኢትዮጵያ በብዛት በመፍለሳቸው ምክንያት ጥልቅ የሆነ የባሕል ለውጥ ተከስቷል፡፡[12] በፍልሰት የመጡት የአረብ ጐሳዎች[13] (ሳባዊ ስልጣኔአቸውን ይዘው) ትግራይ ውስጥ ከሰፈሩ በኋላ ከቀደሙት የሃም (ኩሽ) ሕዝቦች ጋር ተዋህደው የአክሱም ስልጣኔን አምጥተዋል፡፡

*ከክርስቶስ ልደት በፊት* በነበረው በ10ኛውና በ4ተኛው ክፍለ ዘመናት መካከል ከደቡብ አረቢያ ተጨማሪ የአረብ ጐሳዎች ፈልሰዋል፡፡ ከዚያም ወራሪዎቹ ከፍ ባሉት የኢትዮጵያ ሜዳማ ቦታዎች ላይ ቀድመው ከሰፈሩት ሕዝቦች ጋር ተዋልደው የባሕል ለውጥ

አስከትለዋል፡፡ ከመካከላቸው የተወሰነ ቡድን ወደ ሃረርና ወደ ጉራጌ አገር እንዲሁም ሲዳማዎች ወደያዟቸው ቦታዎች ሰፍረዋል፡፡[14]

> *[በቀድሞ ዘመናት በኢትዮጵያ የተደረጉት] ጦርነቶች ዋና ዓላማቸው የሃይማኖት ጀብደኝነት ሳይሆን ግዛት የማስፋፋት ፍላጐት ነበር፡፡*

በ7ተኛው ክፍለ ዘመን የአክሱም ዘመነ መንግስት ሲዳከም[15] ከሴም ባሕል ጋር የተዋሃዱት ሕዝቦች በአርብቶ አደር ቤጃዎች ወረራና ሠፈራ ምክንያት ተፈናቅለው ለኑሮ ብዙም ምቹ ወዳልሆኑት የመሃል ትግራይ፣የአማራ[16] እና የሸዋ ደጋማ አካባቢዎች ለመኖር ተገደዋል፡፡ ከአክሱም በኋላ በአገው ቤተሰብ የተመራው የዛግዌ ዘመነ መንግስት በ11ኛው ክፍለ ዘመን ተተክቷል፡፡ ተከታዩ ሰለሞናዊ አገዛዝም የአገሪቱን ግዛት እያሰፋ ቀጥሏል፡፡

በሌላ በኩል ሶማሌ፣ ኦሮሞና አፋር-ሳሆ ከእሲያ በመፍለስ ወደምስራቅ አፍሪካ የባሕር ዳርቻዎች ሰፍረዋል፡፡ አፋር- ሳሆዎች ወደሰሜን ሲሰራጩ፣ ሱማሌዎች የሰፈሩበት ቦታ[17] ለኑሮ ምቹ ስላልነበረ ወደደቡብና ወደደቡብ ምዕራብ[18] በመስፋፋታቸው ኦሮሞዎቹን ወደደቡብ ምዕራብ የገፉ ሲሆን ቀድመው በቦታው የነበሩትን የባንቱ ጐሳዎች ደግሞ ወደደቡብ ገፍተዋቸዋል፡፡[19] የሲዳማ ጐሳዎች ቀድመው ምዕራባዊና ደቡባዊ የኢትዮጵያ ክፍሎችን ተቆጣጥረው የነበረ ቢሆንም ከጊዜ በኋላ በሌሎች ወረራ ሊገፉ ችለዋል፡፡[20]

ኢትዮጵያ የክርስትናም ሆነ የእስልምና ኃይማኖቶችን በቀዳሚነት[21] ካስተናገዱት አገሮች መካከል አንዷ መሆኗ ይታወቃል፡፡ በአንድ በኩል የክርስቲያን በሌላ በኩል ደግሞ የሙስሊም ኃይሎች የአገሪቱን ስልጣን ለመቆጣጠርና በኢትዮጵያ ክርስቲያናዊ ወይም እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ውጊያዎች አድርገዋል፡፡ በሁለቱም በኩል ጦር የሚያውጁት መሪዎች የአገሪቱን የፖለቲካ ስልጣን ተቆጣጥረው ሌላውን ለማስገበር ነበር፡፡ የእነዚህ ጦርነቶች ዋና ዓላማ የሃይማኖት ጀብደኝነት ሳይሆን ግዛት የማስፋፋት ፍላጐት ነበር፡፡[22]

በታሪክ አጋጣሚ በኢትዮጵያ ረጅም ምዕተ አመታትን የዘለቀ የክርስቲያን መንግስት የተመሰረተ ቢሆንም የኢትዮጵያ ክርስቲያንና ሙስሊም ሕዝቦች ለዘመናት በመከባበርና በመተሳሰብ አብረው ሲኖሩ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡

በ16ኛው ክፍለ ዘመን[23] በአህመድ ግራኝ[24] የተመራውና በቱርኮች[25] የታገዘው የሙስሊም ጦር በሰለሞናዊው መንግስት ላይ ወረራ አካሂዶ ሠፊ ቦታዎችን በመቆጣጠር በኢትዮጵያ የሙስሊም አስተዳደር ለመመስረት መሞከሩ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በፖርቱጋሎች የታገዘው ሰለሞናዊው መንግስት ይህን ከባድና ዓመታትን የፈጀ ጦርነት አሸንፏል፡፡

የኢትዮጵያው ሰለሞናዊ መንግስት በዚህ ረጅም ጦርነት ምክንያት እጅግ ተዳክሞ ነበረ፡፡ በዚያው በተዳከመበት ወቅት እንደገና ሌላ ከባድ ጦርነት አጋጠመው፡፡ ይህም የኦሮሞ የጦር መሪዎች ያካሄዱት ወረራ ሲሆን መሪዎቹ በተሳካ ሁኔታ ከፍተኛ ቁጥር የነበራቸውን የኦሮሞ ሕዝቦች ወደዚያው በማፍለስ ሰፋፊ ለም መሬቶችን እንዲይዙ ያደረጉበት ነው፡፡[26] ይህ ሁኔታ በታሪክ ተመራማሪዎች ዘንድ ‹‹ታላቁ የኦሮሞ ሕዝቦች ፍልሰት››[27] በመባል ይታወቃል፡፡

> *[‹‹ታላቁ የኦሮሞ ሕዝቦች ፍልሰት››]… (አማርኛ ተናጋሪውን ጨምሮ) የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦችን ከጥንታዊ መሬቶቻቸው ያፈናቀለ ነበር፡፡*

ከፍልሰቱ በፊት የኦሮሞ ሕዝቦች የሚኖሩት በደቡባዊው የኢትዮጵያ ጫፍ እንደነበረ ይታመናል፡፡ ከዚያ በኋላ ወደሰሜንና ወደመሐል በብዛት በመፍለስ እስከምእራቡና ምስራቁ የአገሪቱ ጫፎች ሊሰፍሩ ችለዋል፡፡[28]

ፍልሰቱ (አማርኛ ተናጋሪውን ጨምሮ) የተለያዩ ቋንቋ ተናጋሪ ሕዝቦችን ከጥንታዊ መሬቶቻቸው ያፈናቀለ ነበር፡፡ ወረራው ትግራይ፣ አማራ (ወሎ)፣ በጌምድር (ጐንደር)፣ ዳሞት፣ ጐጃም፣ ሸዋ፣ ወሊጋ ወዘተ… ድረስ መዝለቁ ይታወቃል፡፡[29]

በዚህም ምክንያት የኦሮሞ ሕዝቦች ለመጀመሪያ ጊዜ በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብቅ ያሉት በ16ኛው ክፍለ ዘመን ነበር፡፡[30] ከዚያ በኋላም የኦሮሞ ሕዝቦች ከአማርኛ ተናጋሪዎችና ከሌሎቹ የአገሪቱ ሕዝቦች ጋር ተቀላቅለው ተዋልደዋል፡፡

የኦሮሞ ሕዝቦች በመጀመሪያ አርብቶ አደር የነበሩ ሲሆን ቀስ በቀስ በአንድ ቦታ ላይ ሰፍረው በእርሻ ላይ ሊሰማሩና ክርስትና ሃይማኖትን ሊከተሉ ችለዋል፡፡ የተወሰኑት በአርብቶ አደርነት ቀጥለው ከጊዜ በኋላ ወደእስልምና ሃይማኖት ተለውጠዋል፡፡ ቀሪዎቹ ባሕላዊ እምነቶችን ይዘው መቀጠላቸው ይታወቃል፡፡

> ***የአህመድ ግራኝ ወረራና ከዚያም የተከተለው ታላቁ የኦሮሞ ሕዝቦች ፍልሰት የክርስቲያኑን መንግስት ከማዳከማቸውም በላይ አገሪቱን ወደዘመነ መሳፍንት መርተዋታል፡፡***

የአህመድ ግራኝ ወረራና ከዚያም የተከተለው ታላቁ የኦሮሞ ሕዝቦች ፍልሰት የክርስቲያኑን መንግስት ከማዳከማቸውም በላይ አገሪቱን ወደዘመነ መሳፍንት መርተዋታል፡፡ ማዕከላዊው መንግስት በመዳከሙ ምክንያት መሳፍንቶች የየራሳቸውን ግዛቶች ለመያዝ የቻሉበት ይህ ዘመን በታሪክ ‹‹ዘመነ መሳፍንት›› በመባል ይታወቃል፡፡ ይህን ክፍፍል አስቁመው የቀድሞውን ግዛት አንድነት የማስከበሩን ሥራ የጀመሩት አፄ ቴዎድሮስ ሲሆኑ ከዚያም በኋላ አፄ ዮሃንስና አፄ ምኒልክ ቀጥለውታል፡፡

የአህመድ ግራኝን ወረራ ከዚያም ታላቁን የኦሮሞ ሕዝቦች ፍልሰት ተከትሎ በ18ተኛው ክፍለ ዘመንም የአገሪቱ ሰለሞናዊ አገዛዝ ተዳክሞ መቆየቱ ይታወቃል፡፡ ከዚህ በመነሳት ኢትዮጵያን ወደጥንት ታላቅነቷ ለመመለስ (ማለትም በታላቁ የኦሮሞ ሕዝቦች ፍልሰት ምክንያት ይዞ ለማቆየት ያልተቻሉትን የአገሪቱ ክፍሎች እንደገና ለመያዝና ለማጠቃለል) በሚል እንቅስቃሴ በ19ኛው ክፍለ ዘመን አፄ ምኒልክ ጦርነት ጀመሩ፡፡ ኢትዮጵያ አሁን ያላትን አጠቃላይ ስፋት ያገኘችውም በተለይ በአፄ ምኒልክ ጊዜ በተደረገው ጦርነት

ምክንያት መሆኑ ይታወቃል፡፡ አፄ ምኒልክ ይህን ሲያደርጉ ኦሮሞዎችን ከማፈናቀል (ማለትም ኦሮሞዎች በፍልሰት የያዟቸውን ቦታዎች በኃይል አስለቅቆ ከማስመለስና ከፍልሰቱ በፊት ወደነበሩበት ቦታ ከመግፋት) ይልቅ ከመሪዎቹ አስተዳደሩን እየነጠቁ ኦሮሞዎችን ከሰሜናዊው ባሕልና ሃይማኖት ጋር እንዲዋሃዱ ለማድረግ ሞክረዋል፡፡

አፄ ምኒልክ የአገሪቱን ግዛት ለማስፋት ጦርነት ማካሄዳቸው ይታወቃል፡፡ አህመድ ግራኝም በኢትዮጵያ እስላማዊ መንግስት ለመመስረት ጦርነት አካሂደዋል፡፡ አፄ ቴዎድሮስ ደግሞ ዘመነ መሳፍንትን አስቀርተው ማዕከላዊ መንግስት ለመመስረት ጦርነት አድርገዋል፡፡ እነዚህ ጦርነቶች የሚመሳሰሉበት አንድ ዋና ነገር አለ፡፡ ይህም ጦር ያነሱት ወገኖች የአገሪቱን የፓለቲካ ስልጣን በመቆጣጠር የየአካባቢዎቹን መሪዎች አስገብረው ትልቅና ጠንካራ አገር የመመስረት ዓላማ የነበራቸው መሆኑ ነው፡፡ የኦሮሞ መሪዎች ሕዝብ ለማፍለስ ያደረጉት ጦርነት ግን ከወቅቱ የክርስቲያንና የሙስሊም የጦር መሪዎች እቅድ የተለየ ነበር፡፡ ዓላማቸው ሰፋፊ መሬቶችን መያዝና መቆጣጠር እንጂ በወቅቱ (በተለያዩ የጦር መሪዎች የተያዙትን አካባቢዎች አንድ አድርጎ) ትልቅ አገር መመስረትም ሆነ አንድ ሃይማኖት ማስፋፋት እንዳልነበረ ይወሳል፡፡

> *… የክርስቲያኑም ይሁን የሙስሊሙ እንዲሁም የኦሮሞ መሪዎች ሌላውን ሲወርሩ ከአንድ ባህል እና/ወይም ሃይማኖት እንዲዋሃዱ የማስገደድ (assimilation) አዝማሚያ የነበራቸው ቢሆንም የሌሎች ብሔሮች ተወላጆችን በዘረኝነት ከፖለቲካ ስልጣንም ሆነ ከተቀባይነት አላገለሉም ነበር፡፡*

የወቅቱ የኦሮሞ የጦር መሪዎች ሌላው ጐረቤት ሕዝብ ላይ የሚዘምቱትን ያህል እርስ በርስም (በተለያዩ የኦሮሞ ጐሳዎች መካከል) ሰፋፊ መሬቶችን ለመያዝ ትንቅንቅ ያደርጉና ይፎካከሩ እንደነበረ የታሪክ ፅሐፊዎች አመልክተዋል፡፡[31]

በሌሎች አገራት ታሪክ እንደታየው በኢትዮጵያም የተደረጉት ጦርነቶች ዋና ዓላማ የፖለቲካ ስልጣን መያዝና ግዛት ማስፋት ነበር፡፡

ጦርነት በየትኛውም መልኩ አስከፊ ገጽታ ያለውና ጥፋት የሚያስከትል ነው፡፡ስለሆነም እነዚህ ጦርነቶች በሙሉ ከባድ እልቂቶችን አስከትለዋል፡፡ ሆኖም ጦርነቶቹ በጠባብ ዘረኝነት ላይ የተመረኮዙ አልነበሩም፡፡ በወቅቱ ከነበረው እውነታ አንፃር የክርስቲያኑም ይሁን የሙስሊሙ እንዲሁም የኦሮሞ መሪዎች ሌላውን ሲወርሩ ከአንድ ባህል እና/ወይም ሃይማኖት እንዲዋሃዱ የማስገደድ (assimilation) አዝማሚያ የነበራቸው ቢሆንም የሌሎች ብሔሮች ተወላጆችን በዘረኝነት ከፖለቲካ ስልጣንም ሆነ ከተቀባይነት አላገለሉም ነበር፡፡

ይህም ማለት ለመዋሃድ ፈቃደኛ እስከሆነ ድረስ የማንኛውም ብሔር ተወላጅ በብሔሩ ምክንያት ልዩነት ሳይደረግበት ሹመት ማግኘት ይችል ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት የተለያዩ ብሔሮች ተወላጆች የሆኑ ኢትዮጵያውያን በኢትዮጵያ ምስረታ ላይ ለመሳተፍ ችለዋል፡፡ ለዚህም ነው በአፄ ምኒልክ ዘመነ መንግስት የተካሄደው የአድዋ ጦርነት ድል ሊሳካ የቻለው በሁሉም ኢትዮጵያውያን አስተዋጽኦ መሆኑ በሰፊው የሚነገረው፡፡

## 1.2. <u>የኢትዮጵያ የቀድሞ መንግስታትና የብሔር ጥያቄ</u>

ከጥንት ከአክሱም ዘመነ መንግስት ጀምሮ በተስፋፋው የኢትዮጵያ የክርስቲያን አገዛዝ የየትኛውም ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ኢትዮጵያውያን የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖትን እስከተቀበሉና ራሳቸውን ከሰሜናዊው ባህል ጋር እስካዋሃዱ (become assimilated) ድረስ እንደማንኛውም ኢትዮጵያዊ የፖለቲካ ስልጣን ከመያዝ የሚያግዳቸው አልነበረም፡፡[32] ለምሳሌ ከኦሮሞ ሕዝብ ፍልሰት በኋላ በተለይም የየጁ ኦሮሞ ስርዎ መንግስት ከንጉሶቹ የላቀ ስልጣን እንደነበረው አይዘነጋም፡፡[33]

አፄዎቹና ሹማምንቶቹ (በቋንቋ፣ በባሕል፣ በሃይማኖትና በተለያዩ መስኮች) ልዩነት ያላቸውን ኢትዮጵያውያን ሲያስተዳድሩ የነበረው በዋናነት ከሰሜናዊው ባሕል ጋር እንዲዋሃዱ በማድረግ፣ በመሾምና በጋብቻ በማስተሳሰር ነበር፡፡ ሹመት ለመስጠት የተጠቀሙባቸው ዋና መስፈርቶች ለንጉሳዊው አገዛዝ ያለ ታማኝነት እና ለሥራው ብቁ መሆን እንጂ ብሔር (ዘር) አልነበረም፡፡

አፄ ኃይለ ስላሴ የመሠረቱት ማዕከላዊ መንግስት አገራዊ አንድነትን ለማምጣት የተጠቀመው ዘዴ ነበረ፡፡ ይህም ዘዴ ብሔራዊ የጦር ሠራዊት፣ አገራዊ ኢኮኖሚ፣ የተሻሻሉ የመገናኛ ዘዴዎች እና (አማርኛ ቋንቋን በመንግስት ተቋማትና በትምህርት ቤቶች ጥቅም ላይ ያዋለ) ብሔራዊ የሆነ ባሕልን ማቀንቀን ነበር፡፡[34]

አፄ ኃይለ ስላሴ ስልጣን ላይ በቆዩበትም ሆነ ከዚያ በፊት በነበረው ጊዜ የአንድን አገር አንድነት ለመጠበቅና ለመበልጸግ አንድ የመንግስት የሥራ ቋንቋ አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ነበር፡፡ (አውሮፓዊዮችን ጨምሮ) በርካታ አገሮችም በታሪካቸው ተመሳሳይ ሂደት ያለፉ መሆናቸው ይታወቃል፡፡ በሌላ በኩል የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ጳጳሳት ለንጉሶቹ ስልጣን ቡራኬ እየሰጡ ሕዝቡ እንዲገዛላቸው ያደርጉ የነበረ ሲሆን ቤተክርስቲያኗም በበኩሏ የተለያዩ ጥቅሞችን ከንጉሶቹ ታገኝ ነበር፡፡

አፄ ኃይለ ስላሴን አውርዶ ስልጣን የተቆጣጠረው ወታደራዊ መንግስትም የአንድ ፓርቲ አመራር በማስፈን ማዕከላዊ አስተዳደርን መቀጠሉ ይታወሳል፡፡ የተለየ አመለካከት የነበራቸው ወይም የወታደራዊው መንግስት የስልጣን ተቀናቃኝ ሊሆኑ እንደሚችሉ የታሰቡ ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች በኃይል እርምጃ ይወገዱ ነበር፡፡ እንደማንኛውም አምባገነናዊ አገዛዝ ደርግም ያተኮረው ስልጣኑን ይዞ መቆየት ላይ ቢሆንም ከዚያ ባለፈ የአገሪቱን የግዛት አንድነት የመጠበቅ አላማም ነበረው፡፡

በመላው አገሪቱ የመደብ ጭቆና በመስፋፋቱ ባላባቶች የመሬት ባለቤቶች ሆነው አብዛኛው ሕዝብ የእነርሱ ጭሰኛ ነበረ፡፡ በመሆኑም በወቅቱ ለኢትዮጵያ አንድነትና ብልጽግና እንቅፋት ተብሎ በዋናነት የተፈረጀው የፊውዳሉ ስርዓት ነበር፡፡ ደርግ በይፋ የፊውዳል የመደብ ክፍሉ እንዲጠፋና በጥቂቶች ተይዞ የነበረው መሬትም በመንግስት ተወርሶ ለሕዝቡ እንዲከፋፈል አድርጓል፡፡ ይህም በኢትዮጵያ ታሪክ ሥር ነቀል ለውጥ ያመጣ እርምጃ ነበር፡፡

ከአፄ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት በተለየ ሁኔታ በደርግ አገዛዝ ዘመን የሁሉም ብሔረሰቦችና ባሕሎች እኩልነት ታውጆ ነበረ፡፡ ከዚህም በተጨማሪ በዚያው የአገዛዝ ዘመን የእስልምና ሃይማኖት በይፋ እውቅና ከማግኘቱም በላይ ከአማርኛ በተጨማሪ በሌሎች የአገሪቱ ቋንቋዎች የሕትመት፣ የመገናኛ ብዙሃን ስርጭትና ትምህርት ተስፋፍቷል፡፡[35]. ይህ በእንዲህ እንዳለ አማርኛ በአገር አቀፍ ደረጃ የይፋ የመግባቢያ ቋንቋ ሆኖ ማገልገሉን ቀጥሏል፡፡

አማርኛ ለአገሪቱ (የተለያዩ ቋንቋዎች ተናጋሪ) ህዝቦች መግባቢያነት ሲያገለግል የቆየው በአፄ ቴዎድሮስና በአፄ ዮሃንስ እንዲሁም ከእነዚያ ዘመነ መንግስታት በፊትና በኋላ ነው፡፡ ይህም የሚያሳየው የትግርኛ፣ የኦሮምኛም ሆነ የአማርኛ ተናጋሪ ወገኖች የአገሪቱን የፖለቲካ ስልጣን ቢይዙም በዋናነት ብሔራዊ ቋንቋ አድርገው ለዘመናት የተጠቀሙት አማርኛ ቋንቋን እንደነበረ ነው፡፡ ይህም ቋንቋ የማንነት መገለጫ ብቻ ሳይሆን የመግባቢያ አገልግሎትም ጭምር እንዳለው ያሳያል፡፡

### 1.3. <u>የብሔር ጭቆና በኢትዮጵያ?</u>

በአፄዎቹ የአገዛዝ ዘመናት ስልጣን የመያዝ መስፈርቱ የብሔር ማንነት አልነበረም፡፡ በመንግስት የተከለከሉ ቋንቋዎችና ሃይማኖቶችም አልነበሩም፡፡ ሆኖም ይፋ የሆነ

የመንግስት ሃይማኖት ስለነበረ ከዚህ ውጭ ለነበሩት የኢትዮጵያ ሕዝቦች አገዛዙ ምቹ ነበረ ለማለት አያስደፍርም፡፡ በተጨማሪም በአገሪቱ ከ80 በላይ የሚሆኑ ቋንቋዎችን የሚናገሩ ዜጐች ቋንቋን የማዳበር መብት አለመከበሩ ቅሬታን መፍጠሩ አልቀረም፡፡

ይህ ሁኔታ በዚህ ዘመን ተቀባይነት ያለው አይደለም፡፡ ምክንያቱም በአሁኑ የዓለም የስልጣኔ ደረጃ የሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች መከበር ጠንካራ ድጋፍ ያለው ከመሆኑም በላይ የእነዚህ መብቶች መከበር በአገሪቱ ዘላቂ ሠላም እንዲሰፍን የሚያግዝ መሆኑ በመታወቁ ነው፡፡

> ***ደርግ ስልጣን በጨበጠበት ጊዜ ... አገሪቱ ከሶሻሊዝም ውጭ የሆነ ርዕዮተ ዓለም መከተል በማትችልበት ደረጃ ላይ ደርሳ ነበር፡፡***

በኢትዮጵያ የመብት ጥያቄ ጠንክሮ መነሳት የጀመረው በአፄ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ሰፍኖ የቆየው የፊውዳል ስርዓት በመጠኑ ካፒታሊስታዊ ለውጦችን ማምጣት እየጀመረ በነበረበት ጊዜ ነበር፡፡ በዚህ ለውጥ ምክንያት የተማረ የሰው ኃይል በብዛት በማስፈለጉ በንጉሰ ነገስቱ ውሳኔ መሠረት በአገሪቱ ከፍተኛ ትምህርት ከመስፋፋቱ ጋር ተያይዞ ነው፡፡ የተማሪዎች ንቅናቄም የተጀመረው በዚህ ወቅት ነበር፡፡

ደርግ ስልጣን በጨበጠበት ጊዜ ደግሞ አገሪቱ ከሶሻሊዝም ውጭ የሆነ ርዕዮተ ዓለም መከተል በማትችልበት ደረጃ ላይ ደርሳ ነበር፡፡ የዚህም ምክንያት ይህ ርዕዮተ ዓለም (የአገሪቱን ምሁራን ጨምሮ) በአጠቃላይ በወጣቶቹ ዘንድ ከፍተኛ ተቀባይነትን አግኝቶ የነበረ በመሆኑ ነው፡፡

በወቅቱ ለኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ መፍትሄው ሶሻሊዝም እንደነበረ በሰፊው ታምኖ ነበረ፡፡ በዚህም መሠረት በአገሪቱ ሥር የሰደደውን የፊውዳል ስርዓት መገርሰስና ከጭቆና ነፃ የሆነ አመራር ማስፈን አስፈላጊ መሆኑ ታምኖበት ነበር፡፡ በደርግ ጊዜ የመደብ ልዩነት

የፈጠረው የፊውዳል ስርዓት እንዲገረሰስ ተደርጓል፤ ይፋ የሆነ የመንግስት ሃይማኖት እንዳይኖር ተደርጓል፤ የብሄረሰቦች ባሕል እንዲከበር ስራ ተሰርቷል፡፡ ሆኖም ደርግ አምባገነናዊ አገዛዝ በማስፈኑ ዜጎች መብቶቻቸውን ማስከበር የቻሉበት ምቹ ሁኔታ አልነበረም፡፡

በአጭሩ በአፄዎቹም ሆነ በደርግ ዘመነ መንግስት መሪዎቹ ፍጹም ስልጣን የነበራቸው በመሆኑ ዜጎች (ከብሄር ጋር የተያያዙትን ጨምሮ) ሌሎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶቻቸውን ለማስከበር የማይችሉበት ሁኔታ ላይ ነበሩ፡፡

### 1.4. <u>በኢትዮጵያ ሰፍኖ ለቆየው የጭቆና አገዛዝ የወቅቱ የአገሪቱ ልሂቃን የሰጡት ምላሽ</u>

የፖለቲካ ሳይንስ ምሁር የሆኑት ዶ/ር መረራ ጉዲና ‹‹Contradictory Interpretations of Ethiopian History: The Need for a New Consensus›› በሚለው ጽሑፋቸው ላይ እንደገለጹት በኢትዮጵያ የነበረውን ጭቆና ተከትሎ በ1950ዎቹ እና 1960ዎቹ አመታት የአገሪቱ የተለያዩ ተፎካካሪ ልሂቃን የኢትዮጵያን ታሪክና የየራሳቸው ብሔረሰቦች በዚህ ታሪክ ውስጥ የነበራቸውን ቦታ በሚመለከት እጅግ የተለያዩ ትርጓሜዎችን መስጠት መጀመራቸውን ይገልፃሉ፡፡

ይህም ማለት የበርካታ ተፎካከሪ ብሔር-ተኮር ልሂቃንን የፖለቲካ ጥቅሞች ለማስጠበቅ ተብሎ የኢትዮጵያ ታሪክ እንደገና እንዲፃፍ መደረጉን ይጠቁማሉ፡፡[36]

ብሔር-ተኮር ልሂቃኑ ከራሳቸው የፖለቲካ ዓላማዎችና ምኞቶች በመነሳት በተለይም የ19ነኛውን ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ታሪክ የተለያዩ ትርጓሜዎች ሰጥተውታል፡፡ ልዩነታቸው ታሪኩን የሚተረጉሙበት መንገድና ለችግሩ የሚሰጡት መፍትሔ ላይ ሲሆን

ፀሐፊው እንዳተቱት እነዚህ ልሂቃን በወቅቱ በዋናነት ያንፀባረቋቸው ሶስት ዓይነት አመለካከቶች የሚከተሉት ናቸው፤

1) ዳግመኛ የመዋሃድ ወይም የመዋሃድ (reunification and unification) አመለካከትን በወቅቱ ሲደግፉ የነበሩት ልሂቃን በዜጎች ላይ አንድ ቋንቋ፣ አንድ ባሕልና አንድ ሃይማኖት መጫን አስፈላጊ እንደነበረ መከራከራቸው ተመልክቷል፡፡
2) የመስፋፋት (expansion) አመለካከትን የሚደግፉት ደግሞ በአብዛኛው ማርክሲስቶች የነበሩ (በኢትዮጵያ ተማሪዎች ንቅናቄ የተሳተፉ) ምሁራን ሲሆኑ የብሔር ጭቆና ቀርቶ በአገሪቱ የብሔሮች እኩልነት እንዲኖር አቋም የያዙ ናቸው፡፡ በእነዚህ ልሂቃን ጨቋኝ ብሔር ተብሎ የተፈረጀው የአማራ ብሔር ሲሆን ተጨቋኞቹ ደግሞ የትግሬ፣ የኦሮሞና ሌሎች ብሔሮች ነበሩ፡፡ እንደመፍትሔ ያቀረቡትም በማርክሳዊው አቋም መሠረት የብሔሮች መብት እስከመገንጠል እንዲከበር ነበር፡፡
3) የቅኝ መገዛት (colonization) አመለካከት ደግሞ ኢትዮጵያ ቅኝ ገዢ ስለሆነች የአገሪቱ ፖለቲካዊ ችግሮች መፍትሔ የሚሆነው መገንጠል ብቻ መሆኑን የሚደግፍ ነበር፡፡ ይህ ጥያቄ በዋናነት የመጣው በኤርትራ፣ በኦጋዴንና በአንዳንድ የኦሮሞ ልሂቃን በተመሩት ብሔር-ተኮር እንቅስቃሴዎች ነበር፡፡

የመጀመሪያው አቋም በአሁኑ ወቅት ተቀባይነት ሊኖረው አይችልም፡፡ ምክንያቱም የዜጎች የባሕል፣ የቋንቋ፣ የሃይማኖትና ሌሎች ልዩነቶች ምንጊዜም ስለሚኖሩ የሁሉም ዜጎች መብቶች የተከበረበት አገር ካልተመሰረተ በአገሪቱ ዘላቂ ሠላም ለማስፈን አይቻልም፡፡

ሁለተኛው (ማርክሳዊው) አቋም በሚቀጥለው ንዑስ ርዕስ ስር ይብራራል፡፡

ሶስተኛው (ማለትም የቅኝ ግዛት ክርክሩ) አቋም ብዙም አሳማኝ እንዳልነበረ በርካታ ምሁራንና የታሪክ ሰዎች ይስማማሉ፡፡[37] ብሔር ተኮር ልሂቃኑ በአገር ውስጥ የነበረውን የጭቆና ስሜት በወቅቱ ከነበረው ዓለም አቀፋዊ እድል ጋር በማገናኘት ድጋፍ ለማግኘት ጥረዋል፡፡ ዓለም አቀፋዊ እድል የሚባለው በዓለም አቀፍ ደረጃ የእኩልነት መብት መከበር በወቅቱ ሰፊ ተቀባይነት ማግኘቱ እንዲሁም የተባበሩት መንግስታት ድርጅትና የቀድሞው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት አፍሪካን ከቅኝ ግዛት የማውጣት እንቅስቃሴ መጀመራቸው ነው፡፡[38]

ይህ የብሔር ተኮር ልሂቃኑ አቋም በተለይም በአውሮፓውያን የውጭ ኃይሎች ቅኝ ግዛት ስር ወድቀው የነበሩትን የአፍሪካ አገሮች ነፃ ለማውጣት ከተደረገው እንቅስቃሴ ተጠቃሚ ለመሆን ታልሞ የተፈበረከ ይመስላል፡፡

## 1.5. <u>አማራ ጨቋኝ ብሔር ሌሎቹ የኢትዮጵያ ብሔሮች ተጨቋኝ ብሔሮች</u>?

በሟቹ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ የተመራው ህወሃት ስልጣን ከመያዙ በፊት ዋና ዓላማው ትግራይን መገንጠል ነበር፡፡ ይህንንም ለማስፈጸም የቅኝ ግዛቱን ክርክር ማንሳቱ ይታወቃል፡፡ ሆኖም የኢትዮጵያን የመንግስት ስልጣን ከጠቀለለ በኋላ በሁለተኛው (ማርክሳዊው) አመለካከት ስር የወደቀ ይመስላል፡፡

ከዚህ ዓላማው አንፃር ህወሃት የኢትዮጵያን ስልጣን የጠቀለለው ለጥቅሙ ሲል ነው እንጂ ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪ በመሆኑ አልነበረም፡፡ ለዚህም ነው የብሔር ጥያቄን የሚመለከተውን የማርክሳዊና ሌኒናዊ አቋም በቀጥታ ከስታሊን በመውሰድ አገሪቱ ላይ የጫነው፡፡

ከተማሪዎቹ ንቅናቄ የተገኙት ማርክሲስት ልሂቃንም ሆኑ ህወሃት ጨቋኝ ብሔር ብለው የፈረጁት የአማርኛ ቋንቋ ተናጋሪውን ነበር፡፡ በእርግጥ በኢትዮጵያ አንድ ብሔር ሌሎችን ብሔሮች ጨቁኗል?

ይህን ጥያቄ ዶ/ር ተሻለ ጥበቡ በሰፊው መልሰውታል፡፡[39] እንደእርሳቸው አመለካከት አንድ ብሔር ሌላን ብሔር ጨቆነ የሚባለው የጨቋኙ ብሔር ሰዎች በሙሉ የተከበሩላቸው መብቶች ለሌሎች ብሔር ሰዎች ፈጹም የተከለከሉ ሲሆኑ እና የዚያ ብሔር ሰዎች ከሌላው የተለየ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ ወዘተ ጥቅም ያገኙ ከሆነ ነው፡፡ ሆኖም አማርኛ ተናጋሪዎች ከሌሎች የተለየ ያገኙት ጥቅም አልነበረም፡፡

*[በቀድሞ የኢትዮጵያ መንግስታት] አማርኛ ተናጋሪዎች ከሌሎች የተለየ ያገኙት [ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ] ጥቅም አልነበረም፡፡*

ፀሐፊው የሰጡት ምሳሌ አለ፡-

በአፓርታይድ ስርዓት የነጮችን የበላይነት ለማስጠበቅ ሲባል አንድ ሰው ጥቁር በመሆኑ ብቻ ለነጮች የተረጋገጡትን መብቶች ይነፈጋል፡፡ ትልቁ ትኩረት የዘር (የብሔር) ልዩነት ማድረግ ላይ ነበር፡፡ ማንኛውም ጥቁር በምንም ዓይነት እንደነጮቹ በፖለቲካ ምርጫ መሳተፍ፣ የፖለቲካ ስልጣን መያዝ፣ ከነጭ ጋር መጋባት ወዘተ አይፈቀድለትም ነበር፡፡ይህ ዘረኛ ስርዓት በቀድሞ ጊዜ በአሜሪካ፣ በደቡብ አፍሪካና በአውስትራሊያ የታየ ነበር፡፡

በአንፃሩ በኢትዮጵያ ለአማርኛ ተናጋሪው ወገን ብቻ የተፈቀዱና ለሌሎች የተከለከሉ መብቶች አልነበሩም፡፡ አንድ ሰው ‹‹አማራ›› ባለመሆኑ (ለምሳሌ ትግሬ ወይም ኦሮሞ በመሆኑ) ምክንያት ‹አማራ› ተብለው የተፈረጁት ሕዝቦች የነበሯቸውን መብቶች ከመጠቀም አልታገደም፡፡ ለአብነት ያህል ያ ዜጋ በብሔሩ ምክንያት የፖለቲካ ስልጣን ከመያዝ፣ "አማራ" ተብለው ከተፈረጁት ንጉሳዊ ቤተሰቦችም ሆነ ተራ ዜጎች ጋር ከመጋባት አይታገድም ነበር፡፡ ለምሳሌ አፄ ኃይለ ስላሴም ሆኑ ባለቤታቸው እቴጌ መነን ኦሮሞ ነበሩ፡፡

በኢትዮጵያ (በፊውዳል ስርዓቱ ወቅት) የላይኛው መደብ ሰዎች ያንን ከፍተኛ ደረጃ ሲያገኙ የነበረው በዘር በሚተላለፍ ውርስ ብቻ አልነበረም፡፡ ምክንያቱም ነገስታቱ

ባለስልጣን ሲሾሙ የሚያተኩሩት ታማኝነትና ችሎታ ላይ እንጂ ብሔር ላይ አልነበረም፡፡[40]

> *… ለዘመናት በአገሪቱ ሰፍኖ የቆየው ጭቆና [ብሔር-ነክ] ጭቆና ብቻ አልነበረም፡፡…በዚህ ሁኔታ ብሔር- ተኮር ልሂቃኑ የብሔር ጭቆናን ብቻ ነጥለው ማየታቸው ተገቢ አይደለም፡፡*

ይህ ለብሔር ልዩነት ትኩረት ያለመስጠት ባህል በኦሮሞዎች ዘንድም በሰፊው ታይቷል፡፡ የኦሮሞ መሪዎች በሚስፋፉበት ጊዜ መሪዎቹ አሸናፊ በነበሩባቸው ቦታዎች ኦሮሞ ያልነበሩትን ኢትዮጵያውያን ከማግለል ይልቅ ከባህላቸው ጋር በማዋሃድ ቁጥራቸውን ያበዙ እንደነበረ የኢትዮጵያ ታሪክ ያሳያል፡፡[41] ሆኖም ይህ ማለት በአገራችን ቋንቋዎችንና ባሕሎችን የማዳበርግ መብቶች በተገቢው መንገድ ተከብረው ነበር ማለት አይደለም፡፡

እዚህ ላይ መረሳት የሌለበት ሌላ ነጥብ አለ፡፡ ይህም ለዘመናት በአገሪቱ ሰፍኖ የቆየው ጭቆና ከብሄር ጋር የተያያዘ ጭቆና ብቻ አልነበረም፡፡ ከዚያ በተጨማሪ የመደብ፣ የፆታ፣ የሃይማኖትና የመሳሰሉት ጭቆናዎችም እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ በዚህ ሁኔታ ብሔር-ተኮር ልሂቃኑ የብሔር ጭቆናን ብቻ ነጥለው ማየታቸው ተገቢ አይደለም፡፡ በተጨማሪም ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ችግሮች ሁሉ መፍትሔው የብሔሮችን የቡድን መብቶች ማስከበር ነው የሚለው አቋማቸው የችግሮቹን ውስብስብነት ያገናዘበ አይደለም፡፡

የአገሪቱ የቀድሞ መሪዎች በሙሉ ገደብ የለሽ ስልጣን ስለነበራቸውና በዘመናዊ መልኩ ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶችን ሊያስከብሩ ባለመቻላቸው ወይም ባለመፈለጋቸው ምክንያት (የየትኛውም ብሔር ተወላጅ የሆኑ) ዜጎች ለዘርፈ ብዙ ጭቆናዎች ተጋልጠው ቆይተዋል፡፡ ዜጎች ለዘመናት ከጭቆናዎቹ ሊላቀቁ ያልቻሉት ድምፃቸውን እንዳያሰሙ ሲታፈኑ በመቆየታቸው ነበር፡፡

በተለይ ቀረብ ባለው በደርግ ዘመነ መንግስት በየጊዜው በሚወሰዱት የጭካኔ እርምጃዎች ምክንያት ዜጎች ከፍተኛ ፍርሃት ውስጥ በመግባታቸው በሰላማዊ መንገድ መብት ለማስከበር የሚቻልበት ሁኔታ አልነበረም፡፡ ስለሆነም ዜጎች ብሶታቸውን መተንፈሻና መፍትሔ ማግኛ መንገድ በማጣታቸው በግፍ ፀጥ እንዲሉ ተደርገዋል፤ የቻሉት ከአገር ተሰድደዋል ወይም ነፍጥ የያዙ ቡድኖችን ተቀላቅለዋል፡፡

ከእነዚህ ቡድኖች አንዱ የሆነው ህወሃት በለስ ቀንቶት የኢትዮጵያን የፖለቲካ ስልጣን ሲቆጣጠር ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም የኢትዮጵያ ችግሮች ብቸኛ መፍትሔ እንደሆነ በማመልከት ይህ አቋሙ ሕግ ሆኖ እንዲወጣ አድርጓል፡፡ ህወሃት ብሔርን መሠረት ያደረገውን ፌደራላዊ አደረጃጀት የወሰደው ከስታሊናዊው ንድፈ ሃሳብ ነበር፡፡

## 2. ብሔር ተኮር ፌደራሊዝምን ወደኢትዮጵያ ማን አመጣው? ለምን?

በዚህ ርዕስ ስር ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም በኢትዮጵያ መንግስት ውስጥ እንዴት ቦታ እንዳገኘና መነሻውስ ምን እንደነበረ በአጭሩ ለመግለጽ ይሞከራል፡፡

ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም የኢትዮጵያ መንግስት አደረጃጀት መሠረት እንዲሆን የተወሰነው ከወታደራዊው ደርግ ስርዓት መውደቅ በኋላ (የትግራይ ሕዝብ ነፃ አውጪ ነኝ በሚለው) በህወሃት ቀመር ነበር፡፡

### 2.1. የ1960ዎቹ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ንቅናቄ

የህወሃት መቋቋም የሚያያዘው የማህበራዊ ፍትሕ ጥያቄዎችን አጉልቶ ካወጣው የዩኒቨርሲቲ[42] ተማሪዎች ንቅናቄ ጋር ነው፡፡ ይህ ንቅናቄ በ1950ዎቹ መጨረሻና በ1960ዎቹ መጀመሪያ ዓመታት የተከሰተ ነው፡፡

ይህ የሥር ነቀል ለውጥ አራማጅ (radical) ተማሪዎች ንቅናቄ ለአገራችን ዘርፈ ብዙ ችግሮች ዋነኛ ተጠያቂ የሆኑት ፊውዳሊዝምና ኢምፔሪያልዝም መሆናቸውን የሚያምንና ማርክሳዊው ርዕዮተ ዓለም ጠንካራ ተጽዕኖ ያሳደረበት ንቅናቄ ነበር፡፡ ዋና ዓላማውም የአፄ ኃይለ ስላሴን መንግስት ፊውዳላዊ የመደብ ጭቆና ማስወገድ ነበር፡፡

በወቅቱ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ከነበሩ በርካታ ኢትዮጵያውያን እንደምንሰማው በዚያን ጊዜ የነበረው ጥያቄ ማን የበለጠ አብዮተኛ እንደነበረ እንጂ ይህን ማርክሳዊ- ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም እንደመፍትሔ ያልተቀበለ ተማሪ ማግኘት አዳጋች እንደነበረ ይገልፃሉ፡፡ ያ ጊዜ በዓለም አቀፍ ደረጃም ቢሆን የርዕዮተ ዓለሙ ተቀባይነት እያደገ የመጣበት ነበር፡፡

> *በንቅናቄው ወቅት ማንኛውም ተማሪ አብዮተኛ ለመባል ... ብሔር ብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል መብት ሊኖራቸው ይገባል የሚለውን የወቅቱ የማርክሳዊ-ሌኒናዊ አቋምም የግድ መቀበል ነበረበት፡፡*

በዚያ ወቅት ተማሪዎቹ  በአፄ ኃይለ ስላሴ የመንግስት ስርዓት ላይ ተቃውሞአቸውን በግልጽ ይናገሩ ነበር፡፡ ማህበራዊ ፍትህ እንዲሰፍን ለማድረግና የመደብ ጭቆናን ለማስወገድ እንደ ‹‹መሬት ላራሹ!›› ያሉ መፈክሮችን በመያዝ ከፍተኛ እንቅስቃሴ ማድረጋቸው ይታወቃል፡፡ እንቅስቃሴው የንጉሰ ነገስቱን ስርዓት ለመገርሰስ ትልቅ ሚና የተጫወተ ቢሆንም ወታደራዊው ደርግ የመንግስትን ስልጣን ሊቆናጠጥ ችሏል፡፡

የተማሪዎቹ ንቅናቄ በዋናነት ማርክሳዊውን የመደብ ትግል የሚመለከት ርዕዮተ ዓለማዊ አመለካከት ላይ አተኩሮ የነበረ ሲሆን ከጊዜ በኋላ የብሔር ጥያቄንም ጨምሮ ወደማካተቱ አዘንብሏል፡፡ በንቅናቄው ወቅት ማንኛውም ተማሪ አብዮተኛ ለመባል ማሟላት የሚጠበቅበት በማርክሳዊ ርዕዮተ ዓለም ማመን ብቻ አልነበረም፡፡ ከዚያ በተጨማሪ ብሔር

ብሔረሰቦች የራስን ዕድል በራስ የመወሰን እስከመገንጠል መብት ሊኖራቸው ይገባል የሚለውን የወቅቱ የማርክሳዊ-ሌኒናዊ አቋምም የግድ መቀበል ነበረበት፡፡[43]

በወቅቱ የተማሪዎች ንቅናቄ ውስጥ የነበሩ በርካታ ተማሪዎች እንደሚናገሩት ከሆነ ተማሪዎቹ የመደብ ትግልን በሚመለከት የማርክሳዊው ርዕዮተ ዓለም ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሮባቸው ነበር፡፡ ያለማጋነን ወጣቶቹ ከልባቸው አጥንተውትም ሆነ በተባራሪ እውቀት፣ በዩኒቨርሲቲው የነበረው ከፍተኛ አብዮታዊ ስሜት ርዕዮተ ዓለሙ ላይ ሙጭጭ እንዲሉ (to be obsessed) አድርጓቸው ነበር፡፡

በተለይ ዋለልኝ መኮንን የተባለ የንቅናቄው ተሳታፊ በወቅቱ የፃፈው ጽሑፍ ብሔር ተኮር የሆኑ የፖለቲካ ድርጅቶች እና እንቅስቃሴዎች ያነሳሳ እንደነበረ ይነገርለታል፡፡ ጽሑፉም የአፄው አገዛዝ አገራዊ ብሔርተኝነት ትክክለኛ ብሔርተኝነት እንዳልነበረና በአማራ ወይም በተወሰነ ደረጃ በአማራና በትግሬ የበላይነት ላይ የተመሰረተ መሆኑን ይገልፃል፡፡[44] ለዚህም እንደመፍትሔ የሚጠቁመው ሁሉም ብሔረሰቦች በእኩልነት የሚሳተፉባት በትክክል ብሔራዊ የሆነች አገር መገንባትን ነው፡፡[45]

ሆኖም በንቅናቄው ላይ የራስን እድል በራስ የመወሰን ጉዳይ ጠንክሮ እንዲገባና በተለይም የመገንጠል ጥያቄ ተቀባይነት እንዲያገኝ የተደረገው (ኤርትራን የመገንጠል ዓላማ ለማሳካት ቆርጠው በተነሱ) በአክራሪ የኤርትራ ብሔርተኛ ተማሪዎች ጠንካራ የማምታታት እንቅስቃሴ ምክንያት መሆኑንና በርካታ ተማሪዎች በየዋህነትና በወጣትነት የአፍላነት ስሜት ከመደብ ትግሉ ጋር የነበረውን ቅራኔ ባለመገንዘብ እንደገቡበት ይናገራሉ፡፡ ከዚህም በላይ በንቅናቄው ላይ የነበረው የኤርትራ ብሔርተኞች ተጽእኖ ጉዳይ እጅግ ዘግይቶ እንደገባቸው ያስረዳሉ፡፡

ይህ የወጣት ‹‹አብዮታዊ›› ተማሪዎች ንቅናቄ የትግራይ ተማሪዎችን ማህበርም ይዞ ነበር፡፡ ማህበሩ ያተኮረው የትግራይን ሕዝብ ባሕላዊና ፖለቲካዊ ጥቅሞች ማስከበር ላይ ነበር፡፡[46] ህወሃት የተቋቋመውም ይህን የማስፈፀም ጠንካራ ስሜትና ፍላጐት በነበራቸው የማህበሩ አባላት እንደነበረ ይነገራል፡፡

### 2.2. <u>የህወሃት አቋም</u>

መሠረታቸው የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎቹ ንቅናቄ የነበረና የወቅቱን የአፄ ኃይለ ስላሴን መንግስት ከዚያም የደርግን መንግስት የሚቃወሙት ንቅናቄዎች በአመዛኙ ግራ ዘመም እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ ህወሃትም ከዚህ አላመለጠም፡፡ በእርግጥም ከንቅናቄው በኋላ ኢትዮጵያ ውስጥ የተቋቋሙት አብዛኞቹ የፖለቲካ ፓርቲዎች በዚያ ንቅናቄ ውስጥ ባለፉ ልሂቃን (elites) መሆኑን ማስተዋል ይቻላል፡፡

ህወሃት የተቋቋመው ወታደራዊው ደርግ ስልጣን ከያዘ በኋላ ሲሆን ትግራይ ራሷን የቻለች ብሔር በመሆኗ የራሷን እድል በራሷ የመወሰንና ከኢትዮጵያ የመገንጠል መብት እንዳላት የሚያመለክት አቋም ይዞ ነበር፡፡ ስለሆነም አንቅስቃሴውን ያጠናከረው (የማርክሳዊና ሌኒናዊ ርዕዮተ ዓለም በዋናነት ባተኮረበት) በመደብ ትግል ጉዳይ ላይ ተመርኩዞ የብሔር ጥያቄን በማጉላት ነበር፡፡

የዚያን ጊዜ ወቅታዊ ሁኔታ የሚያውቁ አንዳንድ ሰዎች የሚናገሩት ነገር አለ፡፡ ይህም ህወሃት የትጥቅ ትግሉን ሲጀምር ብሔርን ለቅስቀሳ ለመጠቀም የወሰነው ደርግ (ከተቃዋሚዎቹ የበለጠ ሶሻሊስት መሆኑን ለማሳየት) በፊውዳል ስርዓቱ ላይ ስር ነቀል እርምጃዎችን ከመውሰዱ ጋር በተያያዘ ነው፡፡ ማለትም ህወሃት (ደርግ በይፋ የያዘውን) ያንኑ ከመደብ ትግል ጋር የተያያዘ የሶሻሊስት ርዕዮተ ዓለም ተጠቅሞ ለመቀስቀስ አስቸጋሪ ስለሆነበት የብሔር ጥያቄን ለማካተት መወሰኑን ይጠቁማሉ፡፡ በተጨማሪም

ህወሃት ደርግ ስልጣኑን እንደማያጋራ ወይም በሰላም እንደማይለቅ በማወቁ ስልጣን ለመያዝ የግድ የትጥቅ ትግል መጀመር ነበረበት፡፡ ለዚህም ብሔር ተኮር ቅስቀሳ ውጤታማነቱ የተሻለ እንደሚሆን ማመኑ ይነገራል፡፡ (በወቅቱ አብዛኛው ተቃዋሚ ‹‹ሶሻሊስት ነኝ›› ይል ስለነበረ በሶሻሊስት ቡድኖች መካከል አለመግባባት የተፈጠረበት ዋና ምክንያት ሁሉም ወገን በየፊናው የመንግስትን ስልጣን ራሱ ለመያዝ በመፈለጉ መሆኑ ይታመናል፡፡)

> *ህወሃት... ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ራሷን የቻለች የትግራይ ሪፐብሊክ የተባለች አገር የማቋቋም ዓላማ...[ነበረው]፡፡ ከዚህ ዓላማ ጋር የሚጋጭ ... አመለካከት ሲያራምዱ የነበሩት አባላት በሚቹ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊና በተከታዮቻቸው... ከህወሃት እንዲገለሉ ወይም እንዲወገዱ [ተደርገዋል]...*

ህወሃት በ1968 ዓ.ም. ያወጣው ማኒፌስቶው የሚያመለክተው ከኢትዮጵያ ተገንጥላ ራሷን የቻለች የትግራይ ሪፐብሊክ የተባለች አገር የማቋቋም ዓላማ እንደነበረው ነው፡፡ በተለያዩ ምክንያቶች ራሳቸውን ከህወሃት ያገለሉ የቀድሞ አባላት[47] እንደመሰከሩት ከሆነ ደግሞ ከዚህ ዓላማ ጋር የሚጋጭ የተለየ ሀሳብ የነበራቸው (ማለትም ትግራይ ራሷን በራሷ የምታስተዳድር የኢትዮጵያ አካል ሆና መቀጠል እንዳለባት የሚከራከሩ) አባላት እንደነበሩ፤ ሆኖም በአመዛኙ ይህን አይነት አመለካከት ሲያራምዱ የነበሩት አባላት በሚቹ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊና በተከታዮቻቸው[48] በተለያዩ ዘዴዎች ከህወሃት እንዲገለሉ ወይም እንዲወገዱ መደረጋቸው በእነዚሁ የቀድሞ የህወሃት አባላት ተገልጿል፡፡

የሆነው ሆኖ የህወሃት ዓላማ ትግራይን መገንጠል ነበረ፡፡ ህወሃት የአንድ ብሔር ነፃ አውጪ ነኝ የሚል ድርጅት ቢሆንም ስልጣን በኃይል ሲይዝ (በተለይ ለኢኮኖሚያዊ ጥቅሙ ሲል) ኢትዮጵያን ሙሉ በሙሉ ለመግዛት ወስኗል፡፡ ይህን የወሰነው ግን ጥቅሙ እስከተጠበቀ ድረስ አገሪቱን በብሔር ከፋፍሎና አንድነቷን አዳክሞ ለመግዛት ነው፡፡

በሕዝቡ ላይ ጥርጣሬ የሚፈጥረውም ለአንድ ብሔር ብቻ ተቆርቋሪ ሆኖ መቅረቡና የተለያዩ ብሔሮች ያሏቸውን ዜጎች እርስ በርስ ለማጋጨት የሚያደርገው ጥረት ነው፡፡

ህወሃት ኢትዮጵያን ከተቆጣጠረ በኋላ እንደጠበቀው ጥቅሙን እያገኘ ባይሆን ኖሮ ምን ያደርግ ነበር? የህወሃት ዓላማ ግልጽ ነው፡፡ ኢትዮጵያ እስከተመቸችው ድረስ ስልጣኑን መከታ በማድረግ የቻለውን ሃብት ማካበት፤ ካልተመቸው ደግሞ ትግራይን መገንጠል ነው፡፡

በዚህ ዓላማው ምክንያት ምንጊዜም ቀሪው የኢትዮጵያ ክፍል ተበታትኖ በትናንሽ ደካማ መንግስታት ቢተካ ደንታ አይሰጠውም፡፡ ምናልባትም ህወሃት የኢትዮጵያን መበታተን እንደጥቅም እንጂ እንደጉዳት ላያየው ይችላል፡፡ ከሰፊና ጠንካራ ኢትዮጵያ ይልቅ በመጠን ከሞላ ጎደል ከትግራይ ጋር ወደሚመጣጠኑ ወይም ወደሚያንሱ ትናንሽ አገሮች የተበታተነች ፣ የባሕር ወደብ አልባና የበለጠ ድሃ የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠሩ በህወሃት እንደስኬት መቆጠሩ አይቀርም፡፡ ኢትዮጵያ የባሕር በር እንዳይኖራት ያደረገው ህወሃት መሆኑ ምንጊዜም ቢሆን አይረሳም፡፡[49]

## 2.3. ህወሃት አቋሙን (ከጥቅሙ አንፃር አይቶ) የኢትዮጵያ ሕግ ስለማድረጉ

በ1983 ዓ.ም. የህወሃት እና የሻዕቢያ የጋራ የትጥቅ ትግል የደርግን ወታደራዊ መንግስት ለመገርሰስ ቻለ፡፡[50] ከዚያም ኢትዮጵያን ለሁለት ከፍለው የመንግስትን ስልጣን ተካፈሉ፡፡ ከ23 ዓመታት በላይም እስካሁን ድረስ የኢትዮጵያንና የተገነጠለችውን ኤርትራን የመንግስት ስልጣን የተቆጣጠሩት ህወሃትና ሻዕቢያ ናቸው፡፡ ከአሁን በኋላም ለረጅም ጊዜ ሥልጣኑን ጨብጠው ለመቆየት በየፊናቸው እየሰሩ መሆናቸው ይታወቃል፡፡

አንዱ ዋና ልዩነታቸው ህወሃት ብሔር (ዘር) ላይ ያተኮረ አደረጃጀትን ለመጫን ቆርጦ መነሳቱና ሻዕቢያ ግን አገራዊ ብሔርተኝነት (ሕብረ ብሔራዊነትን) ማቀንቀኑ ነው፡፡

ህወሃት ይህን አቋም የያዘው (1) ትግራይን የመገንጠል ዓላማ ስለነበረው፣ እና (2) ስልጣን ከያዘ (በትግራይ ሰፊ የቋንቋ ልዩነት ባለመኖሩ) ትግርኛ ቋንቋ የትግራይ ብሔራዊ ቋንቋ እንዲሆን ማድረግ በተነፃፃሪነት እንደሚቀል በማሰቡ ምክንያት ነበር፡፡ ሻዕቢያ ደግሞ በኤርትራ ሰፊ የቋንቋና የሃይማኖት ልዩነቶች እንዳሉ ስለሚያውቅ የህወሃት ዓይነቱ የማንነት ልዩነት ላይ ያተኮረ ፖለቲካ እንደሚጎዳው አስቀድሞ በመገንዘቡ ነበር፡፡

ህወሃት ትግራይን ራሷን የቻለች አገር የማድረግ ዓላማ የነበረውና የታገለውም ይህን ብሔር ‹‹ነፃ አወጣለሁ›› ብሎ ቢሆንም አንድም ደርግን ለመጣል በሌሎች የአገሪቱ ክፍሎች ጭምር መታገል ስለነበረበት በሌላ በኩል ደግሞ (እድሉን ስላገኘ) ትግራይ ላይ ብቻ ስልጣን ከመያዝ ኢትዮጵያን ሙሉ ለሙሉ መያዙ (በተለይ ከኢኮኖሚ አንፃር) የሚጠቅመው መሆኑን በማመዛዘን ትግሉ ትግራይ ላይ እንዳይቋጭ አድርጓል፡፡

*… ህወሃት በኢትዮጵያ ኢሕአዴግ የሚባል የፖለቲካ ፓርቲ በማቋቋም ፓርቲው የአገሪቱን የተለያዩ የብሔር ጥቅሞች የሚወክሉ ስብስቦችን የያዘ ለማስመሰል ሞክሯል፡፡*

(የደርግ ስርዓት መውደቂያ ሲቃረብ) ህወሃት በኢትዮጵያ ኢሕአዴግ[51] የሚባል የፖለቲካ ፓርቲ በማቋቋም ፓርቲው የአገሪቱን የተለያዩ የብሔር ጥቅሞች የሚወክሉ ስብስቦችን የያዘ ለማስመሰል ሞክሯል፡፡ ሆኖም ኢሕአዴግን የፈጠረውም ሆነ የሚቆጣጠረው ህወሃት መሆኑ የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡ በዚህም ምክንያት ኢሕአዴግ የኢትዮጵያ ሕዝቦችን በሙሉ እንደሚወክል የፖለቲካ ፓርቲ ሊታይ አልቻለም፡፡

በሽግግሩ መንግስት ወቅት ቻርተርም ሆነ ከዚያ በኋላ በወጣው የ1987ቱ የፌደራል ሕገ መንግስት ላይ (የህወሃት ብሔር ተኮር ፌደራሊዝምን በኢትዮጵያ ላይ የመጫን) ዓላማ ይህ ነው የሚባል ክርክር ወይም ማሻሻያ ሊደረግበት ሳይችል ሕግ ሆኖ ወጥቷል፡፡ አምባገነኑ

ህወሃት/ኢ.ሕአዴግ ይህንን ያደረገው በአብዛኛው የራሱን ደጋፊዎች በማሰባሰብ ሕዝብን በሚገባ ባላሳተፈ ሁኔታ ወታደራዊ የበላይነቱን ተጠቅሞ በማስወሰን ነበር፡፡

በሽግግሩ መንግስት ጊዜ በተደረገው የይስሙላ ሕገ መንግስት የማጽደቅ ሂደት ላይ ሕብረ ብሔራዊ ፓርቲዎች እንዲገለሉ ተደገው የነበረ ሲሆን ብሔር ተኮር የፖለቲካ ፓርቲዎች (አብዛኞቹ የህወሃትን አቋም ወደሕግ ለመቀየር ሲባል በአጭር ጊዜ ውስጥ የተቋቋሙ መሆናቸው የሚነገርላቸው) ግን ከመበረታታቸውም በላይ ያላግባብ ብቸኛ ተሳታፊዎች እንዲሆኑ መደረጋቸው አይዘነጋም፡፡

በ1987ቱ የፌደራል ሕገመንግስት ላይ ከ80 በላይ ለሆኑት የኢትዮጵያ ብሔር ብሔረሰቦች በሙሉ የመገንጠል መብት መረጋገጥ የሚያሳየው ከጊዜ በኋላ በህወሃት ውስጥ አመራሩን የተቆናጠጡት ትግራይን የመገንጠል አላማ የነበራቸው የሚቹ የመለስ ዜናዊን ቡድን አቋም የሚያሳይ እንደሆነ (ቀድሞ የህወሃት መሪ የነበሩት) የዶ/ር አረጋዊ በርሄ ጽሁፍም[52] ይገልፃል፡፡ ከህወሃት/ኢ.ሕአዴግ አምባገነንነት አንፃር ሁሉን ያሳተፈ ውይይትና ምክክር ሳይደረግ (ወይም በይስሙላ ምክክር) ፓርቲው የሚፈልገውን ዓይነት ሕግ የማውጣቱ ጉዳይ ብዙም የሚገርም አይደለም፡፡[53]

## 2.4. <u>ህወሃት ብሄር ተኮር የፌደራል አደረጃጀትን ለምን መረጠ</u>

እንደሚታወቀው አምባገነኑ ህወሃት/ኢ.ሕአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ስልጣኑን በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለሌሎች ለማጋራትም ሆነ ካልተመረጠ ስልጣኑን ለማስረከብ ምንም ዓላማ አልነበረውም፤ አሁንም የለውም፡፡ የይስሙላ ምርጫዎችን የሚያካሂደውም ምዕራባውያን መንግስታት ለኢትዮጵያ የሚያደርጉትን እርዳታ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ከመመስረት ጋር ስለሚያያይዙት (በአገሪቱ ቀስ በቀስ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚሰፍን በማስመሰል) እነዚህን መንግስታት ለማጭበርበር መሆኑ ይታወቃል፡፡

አምባገነኑ ህወሃት/ኢሕአዴግ ለሚወስናቸው ውሳኔዎች ዋናው መመዘኛው፣ ውሳኔው ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችለው መሆን ወይም አለመሆኑ ነው፡፡ ተቀባይነት አግኝቶ ስልጣን ላይ ለመቆየት ደግሞ ቢያንስ አንድ ትልቅ ችግር አለበት፡፡ ይህም ፓርቲው (ህወሃት) ወከልኩ የሚለው ከ6 በመቶ የማይበልጡትን የአገሪቱ ዜጐች ብቻ ነው፡፡ ለዚህም ነው በብሔር የተከፋፈለ ፌደራላዊ ስርዓት አገሪቱ ላይ በመጫን፣ ራሱ የሚቆጣጠራቸው የሌሎች ብሔሮች የፖለቲካ ፓርቲዎችን[54] ለይስሙላ አደራጅቶ አገሪቱን ለመግዛት የወሰነው፡፡

አምባገነኑ ህወሃት/ኢሕአዴግ ከሁለት አስርት አመታት በላይ ዜጐችን በብሔር ከፋፍሎ በመግዛት ጠንካራ ተቃዋሚ እንዳይመጣበት ለመከላከልና የራሱን የስልጣን እድሜ ለማራዘም ጥረት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡ ይህ የህወሃት ዜጐችን በብሔር (በዘር) የመከፋፈል ዓላማ በሰፊው የሚታመንና በበርካታ ፀሐፊዎችም የተፃፈ ነው፡፡[55]

የአንድ አገር ሕዝቦችን በዘር እንዲከፋፈሉ (እርስ በርስ እንዳይስማሙ) አድርጐ መግዛት ከዚህ በፊትም እንደ ጣሊያንና እንግሊዝ ያሉ የአውሮፓ ቅኝ ገዢዎች የተጠቀሙበት ዘዴ መሆኑ በታሪክ በሰፊው ተዘግቧል፡፡ የከፋፍሎ መግዛት ዋና ዓላማ ቅኝ ተገዢዎቹ ሕዝቦች በጋራ አምጸው ድል እንዳያደርጉ መከላከል ነው፡፡ አምባገነኑ ህወሃት/ኢሕአዴግ ለመከላከል የሚሞክረውም የዚህ ዓይነት የጋራ አመጽ መጥቶበት ከስልጣኑ እንዳይለይ ነው፡፡

ሟቹ አቶ መለስ ዜናዊ የአገሪቱን አንድነት ለመጠበቅ የሚቻለው ይህን (የብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ የመገንጠልን መብት የሚደነግግ) ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም በመከተል ብቻ መሆኑን በወቅቱ መናገራቸው ይታወሳል፡፡ ሆኖም ይህን ምክንያት የሰጡት በይፋ በሚነገሩ ምክንያቶች ላይ ከፋፍሎ መግዛት የህወሃት ዓላማ መሆኑ በይፋ ስለማይነገር (ማለትም ይህ ድብቅ ዓላማው መደበቅ ስላለበት) እንጂ ብቸኛው አማራጭ በመሆኑ አልነበረም፡፡

## 2.5. የህወሃት/ኢሕአዴግ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም

### 2.5.1. የ1987ቱ ሕገ መንግስትና ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም

በ1987ቱ ሕገመንግስት መግቢያ ላይ ‹‹ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች›› በነፃ ፍላጐታቸው ሕገመንግስቱን በተወካዮቻቸው አማካኝነት እንዳጸደቁት ተመልክቷል፡፡ ሆኖም እያንዳንዱን ብሔር የሚወክሉ በነፃ የተደራጁ ቡድኖችም ሆኑ ዴሞክራሲያዊ አካሂድ ባልነበሩበት ሁኔታ የአገሪቱ ‹‹ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች›› በተወካዮቻቸው አማካኝነት በነፃ ፍላጐታቸው ሕገመንግስቱን አፀደቁ መባሉ አሳማኝ አይደለም፡፡

እውነታው ሌላ ነው፡፡ የፌደራል ሰነዶች እንደሆኑ ተደርገው እየታተሙ ስራ ላይ የሚውሉት የገዢው ፓርቲ (ህወሃት/ኢሕአዴግ) ሰነዶች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡[56]

ሕገመንግስቱን ያጸደቁት (መነሻው ላይ ከነበረውና በሂደት ራሱን ካገለለው ከኦነግ[57] በስተቀር) ህወሃት የፈጠራቸውና የሚቆጣጠራቸው ብሔር ተኮር ፓርቲዎች ነበሩ፡፡ እነርሱም ህወሃት የወሰነውን ከማጽደቅና የበላይነቱን ከማስጠበቅ በስተቀር ሌላ ይህ ነው የሚባል ተግባር እንደሌላቸው ይታወቃል፡፡

ህወሃት/ኢሕአዴግ ስልጣን ከተቆጣጠረ በኋላ ኢትዮጵያዊነት (ዜግነት) የባለመብትነት መለያ እንዲሆን አልወደደም፡፡ በመሆኑም በምትኩ (በስታሊን ንድፈ ሃሳብ መሠረት) ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የመብት ባለቤቶች ሆነዋል፡፡

> ***የፌደራል ሰነዶች እንደሆኑ ተደርገው እየታተሙ ስራ ላይ የሚውሉት የገዢው ፓርቲ (ህወሃት/ኢሕአዴግ) ሰነዶች እንደሆኑ ይታወቃል፡፡***

የሕገ መንግስቱ መግቢያና አንቀጽ 8 እንደሚያመለክቱት የኢትዮጵያ የሉዓላዊ ስልጣን ባለቤትነትና በዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ተወካዮችን የመምረጥ መብት የተሰጣቸው የኢትዮጵያ ብሔሮች፣

ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ናቸው፡፡ ማለትም የመብቱ ባለቤቶች ግለሰብ ዜጐች ሳይሆኑ የብሔር ቡድኖች ናቸው፡፡

የኢትዮጵያን ሕገ መንግስት ከሌሎች የአፍሪካና የዓለም ሕገ መንግስቶች የተለየ የሚያደርገው በተለይ አንቀጽ 39 ነው፡፡ አንቀጹ ለማንኛውም ብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እስከመገንጠል መብቱ ያለገደብ እንዲጠበቅ ደንግጓል፡፡

ሕገ መንግስቱ ላይ የተቀመጡት ‹‹ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች›› የሚሉት ሃሳቦች የርዕዮተ ዓለምና የአገላለጽ ጉድለቶች አሉባቸው፡፡ ለዚህም ዋናው ምክንያት እነዚህ ሃሳቦች የሶቪየት አመለካከቶችን ከሚያንፀባርቁት ከስታሊንና ከሌኒን ጽሑፎች ጋር ጠንካራ ቁርኝት ያላቸው በመሆኑ ነው፡፡[58]

> *…‹‹ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች›› ለሚሉት ሃሳቦች ሕገ መንግስቱ ግልጽ ትርጓሜ አልሰጠም፡፡ በተጨማሪም በብሔር፣ በብሔረሰብና በሕዝብ መካከል ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ አልተገለፀም፡፡*

የሕገ መንግስቱ አንቀጽ 39 ‹‹ብሔር፣ ብሔረሰብ፣ ሕዝብ›› ማለት ‹‹ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባሕል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ ሊግባቡ የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣ የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣ የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በአብዛኛው በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ›› ማህበረሰቦች መሆናቸውን ይገልፃል፡፡

ስለሆነም ‹‹ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች›› ለሚሉት ሃሳቦች ሕገ መንግስቱ ግልጽ ትርጓሜ አልሰጠም፡፡ በተጨማሪም በብሔር፣ በብሔረሰብና በሕዝብ መካከል ያለው ልዩነት ምን እንደሆነ አልተገለፀም፡፡  ኢትዮጵያ ውስጥ ብሔር ማነው? ብሔረሰብ ማነው? ሕዝብ

ማን ነው? ማን ምን እንደሆነ እንዲሁም የትኛው የአገሪቱ መሬት እንደሚገባው የሚወስነውስ ማነው?

የአገሪቱ መሬት የማይሸጥ የማይለወጥ የኢትዮጵያ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች የጋራ ንብረት እንደሆነ ሕገ መንግስቱ ደንግጓል፡፡[59] ይህም ማለት መሬት በመንግስት እጅ ነው፤ የመንግስት ስልጣንም በህወሃት እጅ ስለሆነ ወሳኙ ህወሃት መሆኑ አያከራክርም፡፡

በተግባር የብሔር፣ ብሔረሰብና ሕዝብን ማንነት በሚመለከት የወሰነውና እየወሰነ ያለው ህወሃት መሆኑ ይታወቃል፡፡ ይህም የሆነው የፌደራል ክልሎቹ አከላለል በብሔር ላይ የተመሰረተ እንዲሆን ያደረገውና የየክልሉን ወሰን የከለለው ህወሃት በመሆኑ ነው፡፡ በተጨማሪም የሕገ መንግስት አንቀፆች/ ሃሳቦች ትርጓሜ ካስፈለጋቸው በጉዳዮቹ ላይ የመጨረሻ ውሳኔ መስጠት የሚችለው እንዲሁም የክልሎችን ወሰን በሚመለከት ክልሎቹ ካልተስማሙ የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጠው የፌደሬሽኑ ምክር ቤት ነው፡፡[60] በተግባር የዚህን ምክር ቤት አባላት የሚመለምለውና የሚቆጣጠረው ህወሃት መሆኑ ይታወቃል፡፡

በሕወሃት ቀመር መሠረት የኢትዮጵያ ፌደራል መንግስት የተዋቀረው በክልሎች ሲሆን ክልሎቹ የተዋቀሩበት መስፈርት የሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነትና ፈቃድ መሆኑን ሕገ መንግስቱ ያመለክታል፡፡[61] ህወሃት/ኢሕአዴግ በሕገ መንግስቱ መሠረት ዘጠኝ ክልሎች ቢያዋቅርም ክልሎቹ በዴሞክራሲያዊ  ውይይት የተፈጠሩ አለመሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ነው፡፡

ህወሃት/ኢሕአዴግ ያዋቀራቸው ክልሎች የሚከተሉት ናቸው፡- የትግራይ፣ የአፋር፣ የአማራ፣ የኦሮሚያ፣ የሱማሌ፣ የቤኒሻንጉል/ ጉሙዝ፣ የደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች፣ የጋምቤላ ሕዝቦች እና የሀረሪ ሕዝብ ክልሎች፡፡[62] ከዚህ ጋር በተያያዘ በእነዚህ ክልሎች

ውስጥ የተካተቱት ብሔር፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች በማንኛውም ጊዜ የየራሳቸውን ክልል የማቋቋም መብት እንዳላቸውም በሕገ መንግስቱ ተመልክቷል፡፡

### 2.5.2. ህወሃትና የብሔር ተኮር ፌደራሊዝም አተገባበር

አማራ፣ ኦሮሚያና ደቡብ[63] ክልሎችን ጨምሮ ከትግራይ ክልል በስተቀር ሌሎቹ በህወሃት ቀመር የተከፋፈሉ ናቸው፡፡ የትግራይ ክልል በንጉሡም ሆነ በደርግ ጊዜ የታወቀ የአገሪቱ ክፍል (ጠቅላይ ግዛት በኋላም ክፍለ ሃገር) እንደነበረ ይታወቃል፡፡ በህወሃት/ኢሕአዴግ የስልጣን ዘመን የተቀየረው አንዱ ዋና ነገር ቀድሞ በጎንደርና በወሎ ክፍለ ሃገራት ስር ይገኙ የነበሩትን ቦታዎች ወደትግራይ በኃይል በማጠቃለል ትግራይ ቀድሞ ከነበረችው የሰፋች እንድትሆን መደረጉ ነው፡፡

የትግራይ መስፋት የክርክር ነጥብ ሊሆን የቻለበት ዋናው ምክንያት *ክልሎቹ በብሔር እንዲዋቀሩ መደረጉ በራሱ* ‹‹የትግራይ ወይም የሌላው›› ወይም ‹‹የኛና የነሱ›› የሚል ስሜት የሚፈጥር በመሆኑ ነው፡፡ በተለይም ደግሞ ህወሃት አማራ ክልል የሚል ጥቅል ስያሜ የሰጣቸው ጎጃም፣ ጎንደር (በቀድሞ አጠራሩ በጌምድር) ፣ ወሎና ሸዋ *እያንዳንዳቸው* ልክ እንደትግራይ ታሪካዊ የሆነና በንጉሡም ሆነ በደርግ ጊዜ የታወቁ የአገሪቱ ጠቅላይ ግዛቶች በኋላም ክፍለ ሃገሮች እንደነበሩ ይታወቃል፡፡ ይህ ቢሆንም በአብዛኛው አማርኛ ተናጋሪ ህዝቦች አለባቸው በሚል ምክንያት በግዴታ የአማራ ክልል እንዲባሉ አድርጓል፡፡

ህወሃት ደርግን ለመጣል ባደረገው የትጥቅ ትግል ወቅት ለትግራይ ሕዝብ ቅስቀሳ ሲያደርግ የነበረው በዋናነት በዘውግ ብሔርተኝነት ላይ ተመስርቶ ሲሆን በተለይም ፀረ-አማራ ፕሮፓጋንዳን በከፍተኛ ሁኔታ ይነዛ እንደነበረ ይታወቃል፡፡[64]

ህወሃት ከጅምሩ ዋና ጠላቱ አድርጎ የፈረጀው ‹አማራ› ብሎ የሚጠራውን አማርኛ ተናጋሪ ሕዝብ ነው፡፡ ይህ አመለካከቱ አሁንም ያልተቀየረ በመሆኑ ከህወሃት ቅንጣት ታህል ለዚህ ሕዝብ የመቆርቆር ስሜት አይጠበቅም፡፡ እንደውም በተቃራኒው ህወሃት በአማርኛ ተናጋሪው ሕዝብ ላይ የቻለውን ያህል ጉዳት ለማድረስ እንደሚተጋ ይታወቃል፡፡[65] ህወሃት በዚህ ጥላቻው ምክንያት በአማርኛ ተናጋሪዎች ላይ የአንድን አገር የመንግስት ስልጣን ከያዘ ቡድን የማይጠበቁ ከባድ በደሎችን አድርሷል፡፡[66]

ህወሃት የትግራይ ችግሮች ሁሉ መንስኤ አማራ እንደሆነ በማቅረብ በዚህ ዙሪያ ቅስቀሳ አድርጎ ትግሉን የሚቀላቀሉለት ሰዎች ለመመልመል ብዙ ደክሟል፡፡ በታሪክ ከፍተኛ የባህልና የሃይማኖት ትስስር ያለውን የትግራይንና የአማራን ሕዝብ ለማቃቃር ያልፈነቀለው ድንጋይ የለም፡፡

*በአፄ ምኒልክ ዘመን በርካታ የትግራይና የኦሮሞ ነፍጠኞች እንደነበሩ... ይታወቃል፡፡ ህወሃት ግን የሀሰት ፀረ-አማራ ፕሮፓጋንዳውን ለመንዛት ሲል ይህን ሃቅ ለማዳፈን ሞክሯል፡፡*

ስልጣን ከያዘም በኋላ አማርኛ ተናጋሪውን ሕዝብ በአጠቃላይ ነፍጠኛ፣ ትምክህተኛ ወዘተ እያለ አንገቱን እንዲደፋ ለማድረግ ሞክሯል፡፡ ለመሆኑ ነፍጠኛ የነበረው አማርኛ ተናጋሪው ብቻ ነበር? በአፄ ምኒልክ ዘመን በርካታ የትግራይና የኦሮሞ ነፍጠኞች እንደነበሩ ይታወቃል[67]፡፡ ህወሃት ግን የሀሰት ፀረ-አማራ ፕሮፓጋንዳውን ለመንዛት ሲል ይህን ሃቅ ለማዳፈን ሞክሯል፡፡

በሌላ በኩል በአብዛኛው ኦሮምኛ ተናጋሪዎች አሉባቸው የተባሉ ቦታዎች በህወሃት/ኢ.ሕአዴግ አገዛዝ ‹‹ኦሮሚያ ክልል›› የሚል ጥቅል ስም ተሰጥቷቸዋል፡፡ ሆኖም እንደሌሎቹ ክልሎች ሁሉ በኦሮሚያ ክልልም ስልጣኑን በተግባር የተቆጣጠረው ህወሃት (ኦሕዴድ/ኢ.ሕአዴግ ብሎ በፈጠረው ፓርቲ በኩል) መሆኑ ይታወቃል፡፡

(ከህወሃት ቁጥጥር ሥር ወጥቶ) ራስን በራስ የማስተዳደር ከዚያም አልፎ ቀደም ሲል በኦነግ ልሂቃን ሲቀነቀን የነበረው የመገንጠል ጥያቄ ገንፍሎ ይወጣል በሚል ስጋት ህወሃት ለረጅም አመታት በኦሮምኛ ተናጋሪዎች ላይ የኃይል እርምጃዎችን ሲወስድ ቆይቷል፡፡ ህወሃት የመንግስት ስልጣኑን ይዞ ለመቆየትና ተቃውሞውን በእንጭጩ ለመቅጨት ሲል በርካታ ኦሮምኛ ተናጋሪ ኢትዮጵያውያንን አስሯል፤ የተወሰኑትንም ገድሏል፡፡ የኃይል ሚዛኑ እስኪቀየር ድረስ ይህ ሁኔታ ባለበት እንደሚቀጥል ይታመናል፡፡

*ህወሃት/ኢሕአዴግ ላዋቀራቸው ብሔር ተኮር ክልሎች መንግስታት የይስሙላ ጥቃቅን ስልጣኖች ቢሰጥም የአገሪቱን ዋና ዋና የፖለቲካ ስልጣኖች በሙሉ [ተቆጣጥሯል]…*

ህወሃት/ኢሕአዴግ ላዋቀራቸው ብሔር ተኮር ክልሎች መንግስታት የይስሙላ ጥቃቅን ስልጣኖች ቢሰጥም የአገሪቱን ዋና ዋና የፖለቲካ ስልጣኖች በሙሉ የተቆጣጠረው በመሆኑ በሕገ መንግስቱ መሠረት ብሔር ተኮሩን ፌደራሊዝም እየተገበረው አይደለም፡፡[68] በተጨማሪም የየክልሎቹ ኢኮኖሚም በፌደራል መንግስቱ ድጎማ ላይ ጥገኛ በመሆኑ ክልሎቹ ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ ነው ሊባል አይችልም፡፡[69]

በሕዝብ ቁጥር ብዛት ከሌሎች በከፍተኛ ሁኔታ የሚበልጡት የኦሮምኛና የአማርኛ ተናጋሪ ዜጎችም ሆኑ የሌሎቹ የአገሪቱ ብሔሮች ተወላጆች የሆኑ ዜጎች (በዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሚመሯቸውን መምረጥ እንዳይችሉ) በግዴታ ‹‹አውራ ፓርቲ ነኝ›› በማለት ህወሃት/ኢሕአዴግ ሁሉንም በብሔር ያዋቀራቸውን ክልሎች በጉልበት እየገዛ ይገኛል፡፡

ህወሃት/ኢሕአዴግ በቀድሞዋ ሶቪየት ሕብረት የኮሚዩኒስቱ ፓርቲ የተጫወተውን ሚና በአገራችን እየደገመ ይገኛል፡፡ ዓላማውም ስልጣን የከዳው ጊዜ አገሪቱ እንድትገነጣጠል ጥርጊያ መንገድ ማዘጋጀት ነው፡፡ በምርጫ ሰሞን ህወሃት/ኢሕአዴጎች ‹‹እኛ ካልገዛን አገሪቱ ትበታተናለች፡፡›› የሚሉትም ለዚህ ነው፡፡

ህወሃት በህገ መንግስቱ ላይ እንደተደነገገው ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያላሰፈነ በመሆኑ ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም በኢትዮጵያ ሕዝብ ላይ የተጫነው ያለሕዝቡ ፍላጎት ነው፡፡ የእያንዳንዱ የአገሪቱ ብሔሮች ተወላጆች በብሔር ተደራጅተው በዴሞክራሲያዊ መንገድ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም እንዲሰፍን ጥያቄ አላቀረቡም፡፡[70] ከማንኛውም ዓይነት የዜጎች ማንነቶች መካከል ብሔርን (በተለይም ቋንቋን) መርጦ የተለየና ትልቅ ትኩረት እንዲሰጠው ያደረገው ህወሃት ነው፡፡

> *… በህወሃት ዘመን የመጣው ስር ነቀል ለውጥ በርካታ የአገር ውስጥ ቋንቋዎች በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በመንግስት ተቋማት በይፋ በጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረጉ ነው፡፡…[ለውጡ] ፍትሐዊና ተቀባይነት ሊያገኝ የሚገባው ነው፡፡ ሆኖም… ተግባራዊ የሆነው የፌደራል ክልሎችን በብሔር ቡድን በመከፋፈል መሆኑ ትልቅ ድክመት ነው፡፡*

በሌላ በኩል ከደርግ ዘመን በተሻለ ሁኔታ በህወሃት ዘመን የመጣው ስር ነቀል ለውጥ በርካታ የአገር ውስጥ ቋንቋዎች በመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት እና በመንግስት ተቋማት በይፋ በጥቅም ላይ እንዲውሉ መደረጉ ነው፡፡

እንደ አማራ፣ ትግራይና ኦሮሚያ ክልሎች ያሉት በአብዛኛው አንድ ቋንቋ ተናጋሪ የሆኑ ሕዝቦች የሚኖሩባቸው ክልሎች እነዚህን ቋንቋዎች በይፋ እንዲጠቀሙ ሲደረግ እንደጋምቤላና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ባሉት (በአብዛኛው አንድ ቋንቋ የሚናገሩ ዜጎች የሌሉባቸው) ክልሎች ደግሞ ለመግባቢያ በምርጫቸው አማርኛን በመጠቀም ላይ ይገኛሉ፡፡[71] የፌደራሉ መንግስት የሥራ ቋንቋም አማርኛ መሆኑ ተደንግጓል፡፡[72]

ይህ የኢትዮጵያን የተለያዩ ቋንቋዎች የሚመለከት ለውጥ ፍትሐዊና ተቀባይነት ሊያገኝ የሚገባው ነው፡፡ ሆኖም ለውጡ ተግባራዊ የሆነው የፌደራል ክልሎችን በብሔር ቡድን በመከፋፈል መሆኑ ትልቅ ድክመት ነው፡፡

## 3. በአምባገነኑ ህወሃት/ኢሕአዴግ የተጫነብን ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ውጤቶች

በዚህ ርዕስ ላይ የምናየው የህወሃት/ኢሕአዴግ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም የአገሪቱን ሕዝቦች የዜግነት መብቶች ከማስከበር፣ ዘላቂ ሰላም ከማስፈንና የአገሪቷን የግዛት አንድነት ከማስጠበቅ አኳያ ያሉትን ጥቅሞችና ጉዳቶች ነው፡፡

### 3.1. የህወሃት/ኢሕአዴግ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ውጤቶች

#### 3.1.1. የብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ዓለም አቀፍ ተሞክሮዎች

ህወሃት የሚያራምደው ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም የስታሊንን ንድፈ ሃሳብ መሠረት ያደረገ ነው፡፡ ይህ ንድፈ ሃሳብ በዋናነት በሥራ ላይ የዋለው አሁን በኢትዮጵያ ላይ የተጫነው ዓይነት በዘር (በብሔር) የተከፋፈለ የመንግስት ሥርዓት ሰፍኖባት ቆይታ ከዚያም በፈራረሰችውና ወደ አስራ አምስት ራሳቸውን የቻሉ አገሮች በተበታተነችው በቀድሞዋ ሶቪየት ሕብረት ነበር፡፡ ከሶቪየት ሕብረት በተጨማሪ ይህ የብሔር ፌደራሊዝም የተሞከረባቸው ሶሻሊስት የነበሩት ዩጐዝላቪያና ቼኮዝሎቫኪያ ሲሆኑ እነዚህም አገሮች ተመሳሳይ የመበታተን ዕጣ ደርሶባቸዋል፡፡

ታዲያ ይህን የአገር መበታተን ያስከተለና ስኬታማ ሊሆን ያልቻለ የሶሻሊስት ንድፈ ሃሳብ ነው (በሟቹ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር መለስ ዜናዊ የተመራው) ህወሃት አገራችን ኢትዮጵያ ላይ የጫነባት፡፡ በሟቹና በተከታዮቻቸው በኩል የኢትዮጵያ ብሔራዊ ደህንነትና የግዛት አንድነት እንደጠቃሚ ጉዳዮች የማይታዩ መሆናቸውን ከሚያሳብቁት ምክንያቶች አንዱ ይህ ጉዳይ ነው፡፡

የአገርን ጥቅም ከመጠበቅ አንፃር እንደህወሃት ሕዝብ በጥርጣሬ የሚያየው የመንግስት ስልጣን የተቆናጠጠ ቡድን በኢትዮጵያ ታሪክ ተሰምቶ አይታወቅም፡፡ ህወሃት ለአገሪቱ

የሚቆረቆር አመራር ቢሆን ኖሮ ብሔር ተኮር አወቃቀሩ በተጠቀሱት አገሮች ላይ ይህን ዓይነት የመበታተን ውድቀት ማስከተሉን እያወቀ በአገሪቱ  በሥራ ላይ አያውለውም ነበር፡፡

የህወሃት ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም በተለይም የአገርን አንድነት ከማስከበር አንፃር ተመራጭ አይደለም፡፡  ህወሃት የሚያራምደው ይህ የስታሊን ንድፈ ሃሳብ ተግባራዊ የተደረገባቸው አገሮች ልምዶች የሚያሳየን  በብሔር  ተከፋፍሎ  መገንጣልንና  ከዚያ ጋር  የተያያዙ  ጦር  የሚያማዝዙና  ማለቂያ  የሌላቸው  ችግሮችን ሊያስከትል እንደሚችል ነው፡፡

ብሔር  ተኮር  አደረጃጀቱ  በራሱ  ወደአገር  መገንጣል  የሚመራ መሆኑ ይታወቃል፡፡ ህወሃት ግን ይህን ዓይነት አደረጃጀት በአገሪቱ ላይ ከመጫኑ በተጨማሪ እሳት ላይ ቤንዚን የማርከፍከፍ ሥራም ሲሰራ ቆይቷል፡፡ ይህም የተለያዩ ብሔሮች ባሏቸው ዜጎች መካከል አለመተማመንና ጥላቻ እንዲኖር በርትቶ የሚሰራ በመሆኑ ከተሳካለት የሚመጣው ውጤት እጅግ ጉጂ እንደሚሆን ከወዲሁ ለመገመት ይቻላል፡፡

### 3.1.2. <u>የህወሃት/ኢሕአዴግ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ያስከተላቸው ውጤቶች</u>

የህወሃት ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም በርካታ አሉታዊ ውጤቶችን አስከትሏል፡፡ ከእነዚህም መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

1. <u>ዜጎች ያለፍላጎታቸው ብሔር መምረጥ እንዲኖርባቸው ማስገደዱ፡-</u>

የብሔር ማንነት በቅርብ ጊዜ የተፈጠረ ነገር አለመሆኑ ይታወቃል፡፡ ሆኖም በተለያዩ የዓለም አገራት ዘመናዊ የመንግስት አስተዳደር እስከመጣበት ጊዜ ድረስ በአመዛኙ ተለዋዋጭ (fluid) እና ሌሎችን የማያገልል ነበር፡፡[73]

ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ግን የኢትዮጵያን ዜጐች የሚከፍለው በብሔር ቡድኖች ነው፡፡ እነዚህ የብሔር ቡድኖችም በራሳቸው የተሟላና ከሌላ ቡድን ጋር ምንም የጋራ ነገር የሌላቸው[74] መሆኑን ታሳቢ ያደርጋል፡፡ በየትኛውም ቦታ ተቋማዊ እውቅና (pervasive institutionalization) እና የላቀ ትኩረት የተሰጠው የብሔር ልዩነት ነው፡፡ ይህ የብሔር ተቋማዊ አደረጃጀት ዜጐች የግድ የአንድ ብሔር ማንነት እንዲኖራቸው ግፊት ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

በተለያዩ ምክንያቶች ራሳቸውን በአንድ ብሔር ወስነው የማያዩ በርካታ ዜጐች አሉ፡፡ ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም እነዚህ ዜጐች ያለፍላጐታቸው በብሔር አጥር እንዲታጠሩና ከሌሎች ማንነቶቻቸው ይልቅ በዋናነት ወይም ሙሉ በሙሉ የብሔር ማንነታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ያስገድዳቸዋል፡፡

የአንድ አገር ዜጐች ብሔራዊ ማንነት (ዜግነት) ቅድሚያ ተሰጥቶት የሁሉም የእኩልነት መብት ከተከበረ በኋላ ለየትኛው ማንነታቸው[75] የበለጠ ትኩረት እንደሚሰጡ መወሰን ያለባቸው ዜጐች ራሳቸው ናቸው እንጂ መንግስት መሆን የለበትም፡፡ በተለይም በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ውስጥ የዚህ ዓይነቱ የህወሃት ተግባር ተቀባይነት የለውም፡፡

2. <u>ብሔር (ከሌሎች የዜጐች ማንነቶች ተነጥሎ) ይፋ የሆነ ብቸኛ የበላይነት የተሰጠው በመሆኑ ዜጐች በአመዛኙ የብሔር ልዩነታቸው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ ማድረጉ</u>፡-

እንደማንኛውም አገር ዜጐች ኢትዮጵያውያንም (በተፈጥሮም ሆነ በአካባቢያዊ ተጽዕኖ) የተለያዩ ማንነቶች አሏቸው፡፡ ከማንነቶቻቸው መገለጫዎች መካከል ዘር፣ ቋንቋ፣ ሃይማኖት፣ ፆታ፣ መደብ፣ ጐሳ፣ አካባቢ፣ ቀለም፣ መልክ፣ ወዘተ ይገኙበታል፡፡

ህወሃት ከማንኛውም ዓይነት የዜጎች ማንነቶች መገለጫዎች መካከል ብሔርን (በተለይም ቋንቋን) መርጦ የተለየ ትኩረት በመስጠት ዜጎች የሚከፋፈሉበት ዋና መስፈርት እንዲሆን አድርጎታል፡፡

በዚህም ምክንያት ብሔር (በተለይም ቋንቋ) በማህበራዊውም ሆነ በፖለቲካዊው የአገሪቱ ሕይወት ውስጥ ግንባር ቀደም ትኩረት አግኝቷል፡፡ ይህም ህወሃት ስልጣን በያዘባቸው ባለፉት ሁለት አስርት አመታት ዜጎች ለብሔር (ለቋንቋ) ልዩነታቸው ትልቅ ቦታ እንዲሰጡ ገፋፍቷል፡፡

የብሔር ማንነት ከሌሎች ማንነቶች የተለየ ትኩረትና ተቋማዊ የበላይነት ሲሰጠው በዜጎች መካከል ‹‹የኛ›› እና ‹‹የነሱ›› የሚል ከፋፋይ የሆነ ስሜት እንዲዳብር ያደርጋል፡፡ በህወሃት ልዩነትን የማበረታታት ከፍተኛ ተቋማዊ እንቅስቃሴ ምክንያት ይህ ‹‹እኛ›› እና ‹‹እነሱ›› የሚል የመከፋፈል ስሜት ከዚህ በፊት በኢትዮጵያ ባልነበረበት ሁኔታ ውጤቱ መታየት ጀምሯል፡፡[76] ይህም ‹‹የኛ›› ተብሎ ከተፈረጀው ብሔር ውጭ ያለው ኢትዮጵያዊ በብሔር የተለየ ስለሆነ በጥርጣሬ እንዲታይና እንዲገለል የሚጋብዝ ነው፡፡

ምሳሌ ለመጥቀስ ያህል፣ ህወሃት ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ በርካታ ኢትዮጵያውያን ባለሃብቶች መዋዕለ ንዋያቸውን በንግድም ሆነ በኢንዱስትሪ ዘርፍ ላይ ለማፍሰስ ሲዘጋጁ ይህ ብሔር ተኮር አደረጃጀት እንቅፋት ሆኖባቸዋል፡፡ በብሔር ልዩነት ምክንያት ባለሃብቶቹ (የሥራ ዘርፋቸው) የተሻለ ትርፋማ መሆኑን በሚያምኑበት ማንኛውም የአገሪቱ ክፍል በነፃነት መሥራት የማይችሉበት ሁኔታ ተፈጥሯል፡፡ አንድ ኢትዮጵያዊ ባለሃብት የመረጠው ክልል/ዞን/ወረዳ የተወከለው ከባለሃብቱ ብሔር በተለየ ሌላ የብሔር ቡድን ከሆነ በነፃነት የመስራት መብቱና የራሱም ሆነ የንብረቶቹ ደህንነት የማይጠበቅበት ሁኔታ መፈጠሩ በተግባር ሲታይ ቆይቷል፡፡

ይህ ክፍፍል ለረጅም አመታት በዚህ መልኩ ቀጠሎ ለመጪው ትውልድ ከተላለፈ የአገሪቱን ዜጎች አንድነት የማክሰም አደጋ ሊያስከትል እንደሚችል ይታመናል፡፡

3. **<u>ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም የብሔር ቡድኖችን እስከመገንጠል መብት ስለሚሰጣቸው ትብብርና ሰጥቶ መቀበልን አለማበረታታቱ፡-</u>**

ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም በዜጎች የብሔር ልዩነት ላይ የሚያተኩር ከመሆኑም በላይ ዜጎችን በብሄር ቡድኖች በመክፈል ቡድኖቹ የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን፣ እስከመገንጠል ድረስ መብት ሰጥቷቸዋል፡፡ የብሔር ቡድኖች የመገንጠል መብት በሕገ መንግስቱ መደንገጉ በራሱ (በተለይም የግል ጥቅማቸውን በሚያስቀድሙ ብሔር ተኮር ልሂቃን በኩል) መገንጠል እንደዋና አማራጭ እንዲታይ ያደርገዋል፡፡

ይህም ከሌሎቹ የብሔር ቡድኖች ጋር ችግሮችን ለመፍታትና ውሳኔ የሚያስፈልጓቸውን ጉዳዮች ሰፋ አድርገው ከማየትና የጋራ መፍትሔ ከመፈለግ ያግዳቸዋል፡፡ ትኩረታቸው (ሙሉ በሙሉ ካልሆነ እንኳን) በአመዛኙ በየራሳቸው የብሔር ቡድን ወይም ልሂቃን ጥቅም ላይ ብቻ ስለሚሆን የትብብርና ሰጥቶ የመቀበል ዘዴዎችን ለመጠቀም ፍላጎት አይኖራቸውም፡፡

ለምሳሌ የነዳጅ ሃብት በአንዱ የኢትዮጵያ ክፍል ቢገኝ በመጀመሪያ አንዱ የብሔር ቡድን ሃብቱ የሚገባው ለኔ ብቻ ነው ሊልና ሌላ (ወይም ሌሎች) ተጎራባች የብሔር ቡድኖችም ተቀናቃኝ ሆነው ሊቀርቡ ስለሚችሉ ማለቂያ የሌለው ግጭት ይከሰታል፡፡ ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም አገራዊ ብሔርተኘነትን (ማለትም ከሌሎች የአገሪቱ ዜጎች ጋር በፍትሐዊ መንገድ መካፈልን) ስለማያበረታታ ከሃብቱ የሚገኘውን ጥቅም በጠባብነት በብሔር ቡድን ደረጃ ለማስቀረትና ሃብቱን ለብቻ ይዘው ለመገንጠል እንዲያስቡ ይገፋፋቸዋል፡፡

ይህ በሕገ መንግስቱ የተረጋገጠ የብሔር ቡድን መብት ከህወሃት/ኢሕአዴግ ዓላማ ጋር ተጣምሮ ሲታይ የአገሪቱን አንድነት ሊያናጋ የሚችል ውጤት አለው፡፡

እንደሚታወቀው ህወሃት/ኢሕአዴግ ኢትዮጵያን በሙሉ የተቆጣጠረው ለኢኮኖሚ ጥቅሙ እንጂ የአገሪቱን ችግሮች ለመፍታት አይደለም፡፡ በዚህም ምክንያት ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ የብሔር ልዩነትን ከምንም በላይ ሲያበረታታና በተቻለ መጠን አገራዊ ብሔርተኝነትን ሲያጣጥል ቆይቷል፡፡ (ይህን የጠባብ ብሔርተኝነት አቋሙን ለጊዜው እንዲቀይር ያስገደዱት ሁለት አጋጣሚዎች[77] የነበሩ መሆናቸው ባይዘነጋም አሁንም በአመዛኙ ከዚህ አመለካከት የተላቀቀ አይደለም፡፡)

4. **ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ከመነሻው የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ በመሆኑ ዘላቂ ሰላም የሚያሰፍን መፍትሔ ሊሰጥ አለመቻሉ፡-**

በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ብሔርን በሚመለከት ሶስት አይነት ዋና ዋና አመለካከቶች አሉ፡፡ የመጀመሪያው ኘሪሞርዲያሊዝም ሲሆን በ1940ዎቹ ታዋቂ የነበረ ነው፡፡ በዚህ አመለካከት መሠረት ብሔር በተፈጥሮ የተገኘ[78] እና የማይቀየር[79] እንደሆነ በወቅቱ ታምኗል፡፡ ሆኖም ይህ አመለካከት በማስረጃ ያልተደገፈ በመሆኑ ከዚያ ጊዜ በኋላ የተለያዩ ንድፈ ሃሳብ አመንጪዎች ነቅፈውታል፡፡[80] በአሁኑ ጊዜ በግልጽ ኘሪሞርዲያሊስቱን አመለካከት የያዙ ማህበራዊ ሳይንቲስቶች እምብዛም የሉም፡፡[81]

ሁለተኛው አመለካከት ኢንስትሩመንታሊዝም የሚባል ሲሆን ብሔር በተፈጥሮ የተሰጠ ሳይሆን የልሂቃንን ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ርዕዮተዓለማዊ ጥቅሞችን ለማስጠበቅ በየጊዜው የሚፈጠር (እና እንደገና የሚፈጠር) መሆኑን የሚገልጽ ነው፡፡[82]

ሶስተኛውና በአሁኑ ዘመን በሰፊው ተቀባይነት ያገኘው አመለካከት ደግሞ ኮንስትራክቲቪዝም የሚባለው ነው፡፡ ይህ አመለካከት የኘሪሞርዲያሊዝም ተቃራኒ ሲሆን

ብሔር በተፈጥሮ የተወሰነ ሳይሆን እንደማህበራዊ ሁኔታዎች የሚለዋወጥ መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡[83]

ህወሃት በ1987ቱ ሕገ መንግስት ብሔርን (በተለይም ቋንቋን) ዋናው የፌደራል ክልሎች የሚከፋፈሉበት መስፈርት አድርጎታል፡፡ መስፈርቱን ያስቀመጠበት መንገድ የሚያሳየው ሕገ መንግስቱ የሚያራምደው ፕሪሞርዲያሊስታዊውን አመለካከት መሆኑን ነው፡፡

ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም፣ እያንዳንዱ የብሔር ቡድን በተፈጥሮ በአንድ አካባቢ ተሰባስቦ፣ በግልጽ በተከለለ ክልል ውስጥ እንደሚኖር ታሳቢ ያደርጋል፡፡በብሔሮች መካከል ወሰን[84] ያደራጀ ተቋማዊ ማዕቀፍ እንዲፈጠርም አድርጓል፡፡[85] ይህ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ ስህተት ነው፡፡

*ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም… የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ ስህተት ነው፡፡*

ምክንያቱም ከ80 በላይ መሆናቸው የሚነገርላቸው ብሔሮች ተወላጆች የሆኑት ዜጎች ሁሉ የሚኖሩት በየብሔር ክልሎቻቸው ወይም የብሔር አቻዎቻቸው በብዛት በሚኖሩባቸው ቦታዎች አይደለም፡፡ በርካታ የአገሪቱ ዜጎች ከጥንት ጀምሮ ለዘመናት በፈቃደኝነትም ሆነ በግዴታ ወደተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች ሲፈልሱ የቆዩ በመሆናቸውና በተለያዩ ብሔሮች ተወላጆች መካከል በተደረጉና በሚደረጉ መዋለዶች ምክንያት በአንድ ‹‹የብሔር ክልል›› ውስጥ አይገኙም፡፡

ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ዜጎችን በብሔር ቡድን በመከፋፈል ለልዩነታቸው ከፍተኛ ትኩረት መስጠት (የተለያዩ ብሔሮች ተወላጆች) የሆኑ ዜጎች እርስ በርስ የሚያደርጓቸው ግንኙነቶች ሠላማዊ እንዳይሆኑ ከፍተኛ አስተዋጽኦ አድርጓል፡፡ ዜጎች በብሔር ቡድን ተከፋፍለው በጥቅም እንዲጋጩ የሚያደርግ ሁኔታም ፈጥሯል፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝቦች በዜግነታቸው ብቻ በአገሪቱ የትኛውም ክፍል የመኖርና የመስራት (በሕግ የተደነገገ) መብት[86] ቢኖራቸውም (ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም እስካለ ድረስ) ይህ መብት በተግባር ሊከበር አይችልም፡፡ አንዲት አገር ይህን መሠረታዊ የዜጎች መብት ካላስከበረች የዜጎች አገራዊ ስሜት ይቀዘቅዛል፡፡ ምክንያቱም በብሔር (በዘር) ምክንያት የሚገለሉባቸውን የአገሪቱ ክፍሎች ‹‹አገሬ›› ብለው ሊመለከቷቸው አይችሉም፡፡

*[የዜጎች በአገሪቱ የትኛውም ክፍል የመኖርና የመስራት መብት በተግባር ካልተከበረ] የዜጎች አገራዊ ስሜት ይቀዘቅዛል፡፡ምክንያቱም በብሔር (በዘር) ምክንያት የሚገለሉባቸውን የአገሪቱ ክፍሎች ‹‹አገሬ›› ብለው ሊመለከቷቸው አይችሉም፡፡*

በተቋማዊው የብሔር ክፍፍል ምክንያት ሠላም የደፈረሰባቸው በርካታ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ ለምሳሌ ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ሥራ ላይ ከዋለ በኋላ ዜጎች ለበርካታ ትውልዶች ሲኖሩባቸው የነበሩባቸውን የአገሪቱ ክፍሎች ለቀው እንዲወጡና ወደ ‹‹ብሔር ክልላቸው›› እንዲመለሱ እየታዘዙ ሲፈናቀሉ ታይቷል፡፡[87] ብሔር ተኮር ልሂቃን ታሪክን እንደተመቻቸው እየተረጐሙና እየቀየሩ የራሳቸውን ብሔር ቡድን ‹‹ነባር›› በማለትና ሌሎችን ዜጎች ‹‹መጤ›› በማለት ለማግለልና ከቀዬ ለማፈናቀል ብዙ ጥረት እንደሚያደርጉ ይታወቃል፡፡ በአንዳንድ የአገሪቱ ክፍሎች የተለያዩ የብሔር ቡድኖች የየብሔሮቻቸውን ወሰኖች ለማካለል ሲሞክሩ ብርቱ ግጭቶች መከሰታቸው[88] ደግሞ ሌላ ምሳሌ ነው፡፡

5. <u>ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም የክልል መንግስት ማቋቋምን በተመለከተ የብሔሮችን እኩልነት ሊያስከብር አለመቻሉ</u>፡-

ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ተፈፃሚ ሊሆን የማይችልበት አንዱ ዋና ምክንያት በኢትዮጵያ ያሉት ብሔሮች ከ80 በላይ ቢሆኑም 80 የክልል መንግስታት በማቋቋም ሁሉንም በዚህ ረገድ እኩል ማድረግ የማይቻል መሆኑ ነው፡፡

ይህ የማይቻልበት አንዱ ምክንያት የብሔሮቹ ቁጥር እጅግ በመብዛቱ ከፌደራል መንግስቱ ጋር ግንኙነት ለማድረግ ከፍተኛ አስተዳደራዊ ጫና የሚፈጥርና ለሥራ አስቸጋሪ መሆኑ ነው፡፡ ሌላው ደግሞ በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ አብዛኛው ብሔር ከአንድ ሚሊዮን ሕዝብ በታች ያለው በመሆኑና የያዘው መሬት መጠንም አነስተኛ በመሆኑ ራሱን የቻለ ክልላዊ መንግስት ለማቋቋም የማይመች በመሆኑ ነው፡፡ ለዚህም ነው ህወሃት/ኢሕአዴግ በርካታ ብሔሮችን በክልል መንግስትነት ሳይሆን ከዚያ በታች በሆኑት በዞንና በወረዳ ደረጃ እንዲዋቀሩ ለማድረግ የተገደደው፡፡

ህወሃት/ኢሕአዴግ ለትግራይ ያሰበው ሞዴል ለ80ዎቹም ብሔሮች ሊሰራለት አልቻለም፡፡ በአገሪቱ ለዘመናት ተንሰራፍተው ከቆዩት ጭቆናዎች ሁሉ የብሔር ጭቆናን ብቻ ነጥሎ የተለየ ትኩረት በመስጠት፣ የኢትዮጵያ ችግሮች ሁሉ ብቸኛ መፍትሔ የብሔር ቡድኖች ‹‹ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት እስከመገንጠል›› እንደሆነ የደመደመውም ጉዳዩን ከትግራይ አንፃር አይቶ ነው ለማለት ያስደፍራል፡፡

ምክንያቱም አብዛኞቹ የብሔር ቡድኖች በሕዝብና በመሬት መጠን አነስተኛ በመሆናቸው ለእነዚህ የብሔር ቡድኖች መገንጠል በምንም ሁኔታ የሚጠቅማቸው መፍትሔ ሊሆን አይችልም፡፡ በተጨማሪም ግልጽ የሆነ የብሔር ክልል ወሰን ለመከለል ሲሞከር ከአጐራባች ብሔር ቡድኖች ጋር ትልቅ ግጭት ውስጥ የሚገባ በመሆኑ ዘላቂ ሠላም ለማስፈን እጅግ አዳጋች ይሆናል፡፡

ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም በዚህ ረገድ ለሁሉም ብሔሮች በእኩልነት ሊፈፀም አለመቻሉ የሚያሳየው ነገር አለ፡፡ ይህም ህወሃት/ኢሕአዴግ የአገሪቱን ዘርፈ ብዙ የችግር ምንጮች በሚገባ መርምሮ ተገቢ መፍትሔ ለመስጠት ሳይሆን በወታደራዊ የበላይነቱ በመመካት የራሱን ፍላጐት በአገሪቱ ዜጐች ላይ ለመጫን ያደረገው መሆኑ ግልጽ ይሆናል፡፡

6. **ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ብሔራዊ ቋንቋን በሚመለከት ተገቢ ምላሽ አለመስጠቱ፡-**

በኢትዮጵያ ውስጥ አማርኛ ከሌሎች ቋንቋዎች የበለጠ ተጠቃሚነት ያገኘ በመሆኑ የአማራ ብሔር ከሌላው የበላይነት እንዳለው ብዙ ጊዜ ይታሰባል፡፡ ሆኖም ትክክለኛው አመለካከት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ የበላይነት ያገኙ የሕብረተሰብ ክፍሎች (የየትኛውም ብሔር ተወላጅ ቢሆኑ) ለረጅም ዘመናት አማርኛን ሲገለገሉበት የቆዩ መሆኑ ነው፡፡[89]

ህወሃት በአማርኛ ተናጋሪው ላይ ካለው ከፍተኛ ጥላቻ አንፃር አማርኛ ቋንቋን የፌደራል መንግስቱ የሥራ ቋንቋ ማድረጉ ቢገርምም ይህን ለማድረግ ያስገደደው ጠንካራ ምክንያት ይታወቃል፡፡ ትግራይን የመገንጠል ዓላማውን ለጊዜው ገለል አድርጎ (የተለያዩ ቋንቋዎች የሚነገሩባትን አንዲት) ኢትዮጵያን በሙሉ እየገዛ ስለሆነ አገሪቱን ለማተዳደር የግድ በአገር አቀፍ ደረጃ መግባቢያ የሆነ ቋንቋ አስፈልጎታል፡፡ የቋንቋ አንዱ ዋና ተግባር የሆነውን የመግባቢያነት አገልግሎት ሊሰጥለት የቻለው ቋንቋ አማርኛ ሆኖ በመገኘቱ በፌደራል ደረጃ የሥራ ቋንቋ ሊያደርገው ተገድዷል፡፡

ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም 80 በብሔር ቡድን የተከፋፈሉ ክልላዊ መንግስታትን ማቋቋም እንደማይችለው ሁሉ 80ዎቹንም ቋንቋዎች በሙሉ እኩል የአገሪቱ ዜጎች በአገር አቀፍ ደረጃ ለመግባባት የሚጠቀሙባቸው ቋንቋዎች ሊያደርጋቸው አይችልም፡፡ እያንዳንዱ ዜጋ 80 ቋንቋዎችን እንዲማር ለማድረግ ካለመቻሉም በላይ የፌደራል ተቋማት ሰነዶች በሙሉ በእነዚህ ሁሉ ቋንቋዎች በአንድ ጊዜ ሊወጡ አይችሉም፡፡ ይህ እንኳን እንደኢትዮጵያ ባሉ ድሃ አገሮችና በበለፀጉት አገሮችም ሊተገበር አይችልም፡፡

ምክንያቶቹም የሰው ልጅ አቅምና ጊዜ ውስንነት፣ የማስተርጎምና ተያያዥ ወጪዎች ከፍተኛነት፣ በየቋንቋው በሚታተሙት የፌደራል ሰነዶች መካከል የትርጉም ልዩነቶች

ሲፈጠሩ የየትኛው ቋንቋ ትርጓሜ ተቀባይነት እንደሚኖረው መወሰን አስቸጋሪ ስለሚሆን ወዘተ... ናቸው፡፡

በመሆኑም አገር አቀፍ የመግባቢያ ቋንቋ ሲታሰብ (የተለያዩ ብሔሮች ተወላጆች የሆኑት) የአገሪቱ ዜጐች እርስ በርስ የሚግባቡበትን ቋንቋ መምረጥ ያስፈልጋል፡፡ ህወሃት አማርኛን ለመምረጥ የተገደደው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

7. **ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም በየክልሎቹ ውስጥ ያሉትን አናሳ ብሔሮች መብቶች ሊያስከብር አለመቻሉ፡-**

በሕገ መንግስቱ ‹‹ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች›› የራሳቸውን እድል በራሳቸው የመወሰን መብት እስከመገንጠል መከበር እንዳለበት ተደንግጓል፡፡ በህወሃት/ኢሕአዴግ በተደጋጋሚ እንደሚገለጸው ከሆነ ይህ የተደረገው ብሔርን መሠረት ያደረገ የእርስ በርስ ጦርነት በአገሪቱ እንዳይከሰት ለመከላከል ነው፡፡ ሆኖም ይህ መብት ከ80 በላይ ለሆኑት የአገሪቱ ብሔሮች በሙሉ ሊረጋገጥ አልቻለም፡፡

ከእነዚያ ብሔሮች ሁሉ የየራሳቸውን አብላጫ ድርሻ (majority) የያዙ ክልሎች ያገኙት 5ቱ[90] ብቻ ናቸው፡፡ እነዚህ ክልሎች ደግሞ በአገር አቀፍ ደረጃ ካለው የብሔር ልዩነት ጋር ሲነፃፀር በብሔር የበለጠ ተመሳሳይ የሆኑ ዜጐችን ቢያቅፉም በውስጣቸው (በክልል ደረጃ አናሳ የሆኑ) በርካታ የሌሎች ብሔሮች ተወላጆችን ይዘዋል፡፡

እነዚህ ዜጐች በብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ምክንያት በክልል ደረጃ አብላጫ ድርሻ (majority) ባለው የብሔር ቡድን ለኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መገለል ተጋልጠዋል፡፡[91] ጭቆናው የሚፈጸምባቸው ዜጐች የእኩልነት መብቶቻቸው እስኪከበሩ ድረስ በማንኛውም

ጊዜ አጋጣሚውን ሲያገኙ ንቅናቄ ማድረጋቸው ስለማይቀር አገሪቱ ዘላቂ ሠላም ሊሰፍንባት አይችልም፡፡

8. <u>ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም የአገሪቱ ሃብት ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን የሚያደርገው በብሔር መስፈርት በመሆኑ በብሔር ቡድኖች መካከል ግጭትን መፍጠሩና ማባባሱ</u>፡-

በብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም መሠረት መሬትም ሆነ ሌሎች የሃገር ሃብቶች ወደሕዝቡ የሚደርሱትና ውሳኔዎች የሚወሰኑበት ዋናው መስፈርት ብሔር መሆኑ ይታወቃል፡፡ በዚህ ምክንያት አብዛኞቹ ብሔር ተኮር ልሂቃን ከአገር አቀፉ (ከፌደራሉ) በጀት የበለጠ ድርሻ ለማግኘት ሲሉ ከቻሉ የየራሳቸውን ክልላዊ መንግስት ለማቋቋም ካልቻሉም በዞን ደረጃ የብሔር ቡድን ለማደራጀት ጥረት ሲያደርጉ መቆየታቸው ይታወቃል፡፡[92]

በክልል ደረጃ የአገሪቱ ሃብት ክፍፍል ሲደረግ ብሔር ዋናው መስፈርት እንዲሆን በመደረጉ (በተለይም ተጐራባች ሆነው በሚኖሩ) በርካታ የብሔር ቡድኖች መካከል ግጭቶች እንዲፈጠሩና እንዲባባሱ መንስኤ ሆኗል፡፡[93] ከዚህም በላይ በየቦታው የመሬት ባለቤትነትን በሚመለከት በተጐራባች የብሔር ቡድኖች መካከል አለመግባባቶች በመኖራቸውና በተለይም አንዱ ቡድን ሌላውን ‹‹መጤ›› በማለት መሬቱና ሌሎቹ የአገሪቱ ሃብቶች እንደማይገባው የሚከራከር በመሆኑ በበርካታ የብሔር ቡድኖች መካከል መቃቃር እንደተፈጠረ ይታወቃል፡፡[94]

በአገሪቱ በግልጽ የተከለሉና በአብዛኞቹ ዜጐች ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው በብሔር የተደራጁ የክልል ወሰኖች (የተካለሉ ድንበሮች) የሉም፡፡ ስለሆነም የየብሔር ተኮር ልሂቃኑ ተቀናቃኝ የይገባኛል ጥያቄዎች በቀላሉ ሊፈቱ ስለማይችሉ ሠላምን የማደፍረስና ዜጐች ተስማምተው እንዳይኖሩ የማድረግ ውጤት እያስከተሉ ይገኛሉ፡፡

ለወደፊትም ቢሆን ለየትኛው የብሔር ቡድን የትኛው ክልል፣ ዞን ወይም ወረዳ እንደሚገባው መወሰን ቀላል አይሆንም፡፡ በመሆኑም የሃገር አቀፉን (የፌደራሉን) በጀት በብሔር ቡድን መከፋፈልም አደገኛ ይሆናል፡፡ ጉዳዩ ውስብስብና መፍትሔ ለመስጠት አስቸጋሪ በመሆኑ ሁሉንም ቡድኖች ሊያስደስት አይችልም፡፡ በዚህም ምክንያት ወደማያልቅ ግጭት የመምራት እድሉ ሰፊ ነው፡፡ ለጊዜው በወታደራዊ የበላይነቱ ምክንያት ህወሃት/ኢሕአዴግ ይህን በተመቸው መልኩ ቢወስንም በግዴታ እንጂ ሁሉንም በሚያስማማ መልኩ ስላልሆነ ዘላቂ ሠላም መስፈኑ ያጠራጥራል፡፡

9. <u>**ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም አገራዊ ብሔርተኝነት እንዳይዳብር የሚያደርግ መሆኑ፡-**</u>

ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም አገሪቱን በብሔር ቡድኖች የሚከፋፍል በመሆኑ ከሁሉም የላቀ (ዜጎችን በሙሉ የሚያካትት) አገራዊ ብሔርተኝነት እንዳይዳብር እንቅፋት ይሆናል፡፡ እያንዳንዱ የአገሪቱ ዜጋ አንዱን የብሔር ቡድን እንዲመርጥ ያስገድዳል፡፡ በመሆኑም ዜጎች ያለመገለልና ያለስጋት ሊኖሩ የሚችሉት ምናልባት የብሔር (የቋንቋ) ቡድናቸው በያዘው ቦታ ብቻ እንጂ በአገራቸው ግዛት በሙሉ ሊሆን አይችልም፡፡

በአጭሩ ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ዜጎች እንዲሰማቸው የሚያደርገው በብሔር የመከፋፈል ስሜት ነው እንጂ በዜግነታቸው (በኢትዮጵያዊነታቸው) ምክንያት አንድ የመሆን ስሜት አይደለም፡፡ ህወሃት ከመነሻው ሲታገል የነበረው ይህን የመከፋፈል ስሜት ለማበረታታትና የዜግነትን ስሜት ለማክሰም መሆኑ ይታወቃል፡፡

የብሔር ቡድን ክፍፍል (በተለይም በተቋማዊ መልኩ) መበረታታቱ ከቀጠለ ዜጎች የተወሰነውን የአገሪቱ ክፍል ብቻ የራሳቸው አድርገው ለማየት ይገደዳሉ፡፡ የተወሰኑት ደግሞ በታሪክ የአያት የቅድመ-አያቴ መሬት ብለው የሚያስቧቸውን አካባቢዎች ያላግባብ

እንደተነጠቁ በማሰብ በእነዚያ አካባቢዎች የሚኖሩትን ዜጐች እንደጠላት እንዲያዩዋቸውና አጋጣሚ ሲያገኙ በኃይል መሬቶቹን ለማስመለስ እንዲጥሩ ያደርጋል፡፡ ሌሎቹ ደግሞ በተለያዩ ምክንያቶች የትኛውም የብሔር ቡድን ከለላ ስለማይሰጣቸው በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ተቀባይነት ማግኘት ያለመቻል እጣ ይገጥማቸዋል፡፡

በአጠቃላይ ዜጐች (በብሔር ልዩነት ምክንያት) በተመቻቸውና በፈለጉት የአገራቸው ክፍል በነፃነት የመንቀሳቀስ፣ የመሥራት፣ የመኖር ወዘተ… መብቶታቸው ካልተከበሩ የአገሪቱ ዜጐች መሆናቸው ትርጉም አልባ ይሆናል፡፡

## 3.2. የብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ተጠቃሚው ማነው?

ህወሃት/ኢሕአዴግ ስልጣን ከያዘበት ጊዜ ጀምሮ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የማስፈንም ሆነ ለሁሉም የብሔር ቡድኖች ክልሎችን መስርቶ ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበትን ሁኔታ የማመቻቸት ፍላጐት አልነበረውም፡፡ ለኢትዮጵያም ተቆርቋሪ ባለመሆኑ ለችግሮቿ ዘላቂ መፍትሔ ለመስጠት አላሰበም፡፡ ትልቁ ዓላማው ስልጣን ላይ መቆየትና ስልጣን ላይ እስካለ ድረስ የቻለውን ያህል ሃብት ማካበት ነው፡፡

በመሆኑም የብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ዋነኛው ተጠቃሚ አምባገነኑ ህወሃት/ኢሕአዴግ ነው፡፡ ምክንያቱም ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ህወሃት ሕዝቡን ከፋፍሎ በመግዛት በስልጣኑ ላይ የሚመጣውን የጋራ አመጽ ለመግታትና የስልጣን ዘመኑን ለማራዘም ይጠቅመዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ተጠቃሚ የሚሆኑት ብሔር ተኮር ልሂቃን ወይም አክቲቪስቶች ናቸው፡፡ እነዚህ ልሂቃን የብሔር ልዩነትንና ክፍፍልን የሚያበረታቱት በአመዛኙ የግል ጥቅም ለማግኘት ሲሉ ነው፡፡ ደጋፊዎቻቸውን በአገር አቀፍ ደረጃ ከማሰባሰብ ይልቅ በብሔር

ደረጃ ማድረጉ (በተነፃፃሪነት) የሚቀል በመሆኑ ስልጣን የማግኘት እድላቸውን የሚያሰፉት በዚህ መልኩ ወደታች በመውረድ ነው፡፡

የተወሰኑ ጥቅመኛ ያልሆኑና የብሔር ጭቆና ከልባቸው ያሳሰባቸው ብሔር ተኮር ልሂቃንም መኖራቸው ይታወቃል፡፡ እነዚህ ልሂቃን በብሔር ቡድን የመገንጠል ዓላማ ሊኖራቸውም ላይኖራቸውም ይችላል፡፡

የመገንጠል ዓላማ ካላቸው መገንጠል ዘላቂ ሠላም የሚያመጣ መፍትሔ አለመሆኑን ከወዲሁ ቢረዱት መልካም ነው፡፡ ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታ[95] እና ዜጎች በአጠቃላይ ከሚያገኙዋቸው ጥቅሞች አንፃር፣ በብሔር ቡድን ተከፍሎ መገንጠል በአንድ አገር ውስጥ ተከባብሮ ከመኖር የተሻለ መፍትሔ አይደለም፡፡[96]

(የተለያዩ ብሔሮች ተወላጆች የሆኑ) ዜጎች በአንድ አገር ውስጥ አብረው መኖራቸው የተሻለ አማራጭ መሆኑን የሚያምኑት ልሂቃን ደግሞ መገንዘብ ያለባቸው ነገር አለ፡፡ ይህም በብሔር ልዩነት ላይ ተመስርቶ አድሎና መገለልን ያሰፈነው ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ጐጂ ስለሆነ ውድቅ መደረግ እንዳለበት ነው፡፡[97]

## 4. <u>ለኢትዮጵያ የሚበጁ ብሔር ተኮር ያልሆኑ አማራጮች</u>

የህወሃት/ ኢሕአዴግ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም የአገሪቱን ሕዝቦች የዜግነት መብቶች ከማስከበር፣ ዘላቂ ሰላም ከማስፈንና የአገሪቱን የግዛት አንድነት ከማስጠበቅ አኳያ ጐጂ መሆኑ በዝርዝር ተመልክቷል፡፡ ስለዚህ ለኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪካዊ ችግሮች መፍትሔ ሊሆኑ የሚችሉ ሌሎች ብሔር ተኮር ያልሆኑና ለሌሎች ዓይነት የዜጎች ጭቆናዎች ጭምር ምላሽ የሚሰጡ አማራጮችን መጠቀም አስፈላጊ ይሆናል፡፡

## 4.1. የሌሎችን አገሮች ልምዶችና የአገራችንን ታሪክ ስናጤን አስገዳጅ አንድነትም ሆነ አስገዳጅ ልዩነት ዘላቂ ሠላም የሚያሰፍን መፍትሔ የማይሰጡ መሆናቸው

መጀመሪያ ከችግሮቹ እንነሳ፡፡ የብሔር ጭቆናን በሚመለከት ሁለት ጽንፈኛ አካሄዶች አሉ፡፡ አንደኛው በአፄዎቹ ዘመን መንግስት ከኦርቶዶክስ ቤተክርስትያን ጋር የነበረው የጥቅም ግንኙነትና የአገሪቱን ቋንቋዎች የማዳበር መብት የማይሰጥ አቋም ነው፡፡

በሌላኛው ጠርዝ ደግሞ የህወሃት/ኢሕአዴግ አቋም የሆነው አንድ አገር የብሔር ቡድኖች ስብስብ ብቻ እንደሆነ የሚጠቁምና የብሔር ቡድኖቹም ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር መብት እስከመገንጠል ድረስ ሊከበርላቸው ይገባል የሚል ነው፡፡ ይህም እያንዳንዶቹ የብሔር ቡድኖች ከተመቻቸው በአንድ አገር ስር ራሳቸውን በራሳቸው እያስተዳደሩ እንዲቀጥሉ፤ ካልተመቻቸው ተገንጥለው የራሳቸውን አገር እንዲመሰርቱ ለማድረግ የታቀደ ነው፡፡

የመጀመሪያው አስገዳጅ አንድነትን፣ ሁለተኛው ደግሞ አስገዳጅ ልዩነትን መፍትሔ አድርገዋል፡፡ የኢትዮጵያን ተጨባጭ ሁኔታ ስናየው ሁለቱም አመለካከቶች ተገቢ መፍትሔ የማይሰጡ ከመሆናቸውም በላይ ጊዜ ያለፈባቸው ናቸው፡፡

በአፄዎቹ ዘመናት አንድ ቋንቋ በአገር አቀፍ ደረጃ ለመግባባት እንዲያገለግላቸው የግድ ስለነበረና ስልጣናቸውም ተቀባይነት እንዲያገኝላቸው የሚያደርጉት ሃይማኖትን በመጠቀም (ፈጣሪ መረጠን በማለት) ስለነበረ እንዲሁም የዘመኑ የስልጣኔና የንቃተ ሕሊና ደረጃ ከዚህ የተሻለ ዜጎችን የማያገል ሊሆን ባለመቻሉ ነበር፡፡ ጉዳቱም የተለያዩ ማንነቶች ያላቸውን ዜጎች መንግስት በመረጠው መስፈርት መሠረት እንዲዋሃዱ ማስገደዱ ነው፡፡ ይህ ሁኔታ በዚህ ጽሑፍ ውስጥ ‹‹አስገዳጅ አንድነት›› ተብሏል፡፡

የህወሃት ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ደግሞ የዚህ ተቃራኒ ሲሆን ከስታሊን ማርክሳዊና ሌኒናዊ አመለካከት የመነጨ ነው፡፡ ይህም የዜጎች የብሔር ማንነት (ከሌሎች ማንነቶች ተነጥሎ) የተለየና ተቋማዊ የሆነ ወሳኝ ቦታ እንዲሰጠው አድርጓል፡፡ ስለሆነም የአንድ አገር ዜጎች የሚያመሳስሏቸውን ነገሮች ወደጎን በመተው ልዩነታቸው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ፣ በየብሔር ቡድኖቻቸው ተወስነው እንዲቀሩና ከቡድን ውጭ የሆኑትን ሌሎች ዜጎች እንዲያገልሉ ያደርጋል፡፡

> *ዜጎች ከሚመሳሰሉባቸው ጉዳዮች ይልቅ ልዩነታቸውን የሚያጎላ ስርዓት … ተከፋፍሎ የመውደቅ እንጂ አገርን የማጠናከር ውጤት ሊኖረው አይችልም፡፡*

ህወሃት/ኢሕአዴግ ባለው የስልጣን ጥማት ምክንያት አላደረገውም እንጂ የብሔር ቡድኖች ራሳቸውን በራሳቸው እንዲያስተዳድሩ በተግባር ቢፈቅድም ኖሮ ይህ አድልዎ መፈፀሙ አይቀርም ነበር፡፡

በዚህ ጉዳይ ላይ በተደጋጋሚ የምትጠቀሰው ሱማሌ እንኳን በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በባህል ተመሳሳይ የሆኑ ዜጎቿ በጎሳ ተከፋፍለው ተበታትነዋል፡፡ በዚህም ምክንያት አገሪቱ ለረጅም ጊዜ በተለያዩ የጎሳ አለቃዎች የምትገዛና ሠላሟ የደፈረሰ መሆኗ ይታወቃል፡፡ ይህ የሚያሳየን ልዩነትን ከማጉላት ይልቅ ዜጎች የሚመሳሰሉባቸውና የጋራ ጥቅም የሚያስገኙላቸው ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ የሚያደርግ ስርዓት አስፈላጊ መሆኑን ነው፡፡

ከዜጎች ማንነቶች መካከል አንዱን መርጦ ልዩ ትኩረት መስጠት (ለምሳሌ በሱማሌ የጎሳ ልዩነት፣ በኢትዮጵያ የብሔር ወይም የቋንቋ ልዩነት) ትልቅ ጉዳት አለው፡፡ ዜጎች ከሚመሳሰሉባቸው ጉዳዮች ይልቅ ልዩነታቸውን የሚያጎላ ስርዓት (በተለይም እንደህወሃቱ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ተቋማዊ ጥንካሬ ከተሰጠው) ተከፋፍሎ የመውደቅ እንጂ አገርን የማጠናከር ውጤት ሊኖረው አይችልም፡፡

አንድ አገር ራሳቸውን በቻሉ ተቋማዊ የብሔር ቡድኖች በይፋ ከተከፋፈለ ዜጎች ወደየራሳቸው የብሔር ቡድን እንዲያተኩሩና ማንነታቸውን በብሔራቸው ብቻ እንዲወስኑ ያደርጋቸዋል፡፡ በዚህም ምክንያት ‹‹የኛ›› የማይሉትን (ከብሔር ቡድናቸው ውጪ የሆነውን) ዜጋ ያገልሉታል፤ እንደሌላ አገር ሰውም ያዩታል፡፡ ስለሆነም አገራዊ ብሔርተኝነት ሊሰማቸው አይችልም፡፡

*ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ የሚጠቅመው ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ሳይሆን አገራዊ ብሔርተኝነት ላይ ያተኮረና የመዋሃድ ግፊት የማያደርግ ስርዓት ነው፡፡*

ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም አንዱን ብሔር ከአንዱ በመለየትና በማግለል ያልተገባ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅም ለማግኘት እንጂ በአገር አቀፍ ደረጃ ሁሉም ዜጎች ተከባብረውና መብቶቻቸውን አስከብረው በአገሪቱ ክፍሎች በሙሉ ያለገደብና ያለአድሎ እንዲኖሩ ሊያደርግ አይችልም፡፡ ይህ ባልሆነበት ሁኔታ ደግሞ ሕዝቦቹ የአንድ አገር ዜጎች መሆናቸው ምንም ፋይዳ አይኖረውም፡፡ ስለዚህ ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም በምንም ዓይነት የኢትዮጵያን ሕዝቦች ዘላቂ ጥቅም የሚያስከብር አይደለም፡፡

ለኢትዮጵያ ሕዝብ በአጠቃላይ የሚጠቅመው ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ሳይሆን አገራዊ ብሔርተኝነት ላይ ያተኮረና የመዋሃድ ግፊት የማያደርግ ስርዓት ነው፡፡

ይህን የሚደግፍ አንድ መሠረታዊ ምክንያት አለ፡፡ ይህም ከተበታተኑ ትናንሽ ክልሎች ወይም አካባቢዎች ይልቅ አንድ ሰፊ አገር ለነዋሪዎቹ ትልቅ ጥቅም ያስገኛል፡፡ አንድ አገር መሬቱ በሰፋ ቁጥር ሃብቱ እንደሚጨምር ግልጽ ነው፤ የሕዝቡ ቁጥርም ሲበዛ የበለጠ የሚሠራ ኃይል ይኖረዋል፡፡ ከዚህም በላይ የተለያዩ አካባቢዎች የተለያዩ ዓይነት የተፈጥሮ ሃብቶች ይኖራቸዋል፡፡ በአብዛኛው አንዱ ጋ ያለው ሌላው ጋ ያለመኖር እድሉ

ሰፊ ነው፡፡ በመሆኑም አካባቢዎቹ በሙሉ እርስ በርስ በተፈጥሮ ሃብትና በሰው ኃይል ከተደጋገፉ አገሪቱ የበለጠ ሃብት እንዲኖራትና እንድትበለጽግ ለማድረግ ያስችላል፡፡ በዚህ መልኩ በየትኛውም የአገሪቱ ክፍል ያለው ሃብት ለሁሉም ዜጎች የጋራ ብልጽግና ያገለግላል፡፡

ነገር ግን አገር ለማበልፀግ የሚያስፈልገው የመሬት መስፋትና የሰው ሃይል መብዛት ብቻ አይደለም፡፡ አገሪቱን ያለአድልኦና ለሁሉም ዜጎች እኩል ተቆርቋሪ በሆነ መንገድ በመምራት ዘላቂ ሰላም አስፍኖ የሚመራ ኃይል የግድ ያስፈልጋል፡፡ ያ ኃይል ከአስገዳጅ አንድነትም (ከማዋሃድ ግፊትም) ሆነ ከአስገዳጅ ልዩነት (ከብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም) የፀዳ ሆኖ፣ ዜጎችን በሙሉ በእኩልነት የሚያሳትፍ ዴሞክራሲያዊና ፌደራላዊ የሆነ ስርዓት ማስፈን ይገባዋል፡፡ ይህም ለዜጎች ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጥቅሞችን ከማስገኘቱም በላይ ዜጎች አገሪቱ ‹የኔ› ናት የሚል ጠንካራ ስሜት (strong sense of belongingness) እንዲሰማቸው ያደርጋል፡፡

## 4.2. <u>ለኢትዮጵያ ምን ዓይነት ፌደራሊዝም ያስፈልጋታል?</u>

ለኢትዮጵያ ፌደራላዊ የመንግስት ስርዓት እንደሚያስፈልጋት ብዙም አከራካሪ አይደለም፡፡ ሆኖም ምን ዓይነት ፌደራሊዝም የሚለውን በሚመለከት አማራጮችን መጠቆም ይቻላል፡፡

### 4.2.1. <u>በብሔር ቡድን ተከፋፍሎ መገንጠል ዘላቂ ሠላም ሊያሰፍን አለመቻሉ</u>

በኢትዮጵያ በብሔር ቡድን መገንጠል አዋጪ ያልሆኑባቸው የተለያዩ ምክንያቶች አሉ፡፡ በመጀመሪያ የተፈጥሮም ሆነ በስምምነት በግልጽ የተከለለ የብሔር ቡድኖች ወሰን የሌለ በመሆኑ የመገንጠል ጥያቄ ቢመጣ በብሔር ቡድኖች መካከል ማለቂያ የማይኖረው

የድንበር ግጭት መፈጠሩ አይቀርም፡፡ ስለሆነም መገንጠል ዘላቂ ሠላም ሊያሰፍን የሚችል አማራጭ አይደለም፡፡

በወታደራዊ ኃይል የበላይነት ምክንያት ያለዴሞክራሲያዊ ድርድር የሚካለሉ የብሔር ቡድኖች ወሰኖች ሊኖሩ ይችላሉ፡፡ ይህ በጉልበት የሚደረግ በብሔር ቡድን ድንበር የማካለል ሥራም ከውጥረት የተላቀቀ አይሆንም፡፡ ምክንያቱም ውሳኔውን የሚቃወሙት ወገኖች ሁኔታው ሲፈቅድላቸው እርምጃ ሊወስዱ ስለሚችሉ እንዲሁም ለብሔር ቡድኑ የተከለለው የአገሪቱ ክፍል የሚይዘው የዛን ብሔር ሰዎች ብቻ ባለመሆኑ ነው፡፡

በፍልሰትም ሆነ (የተለያዩ ብሔሮች ተወላጆች የሆኑ ዜጎች) እርስ በርስ በመዋለዳቸው ምክንያት በርካታ ኢትዮጵያውያን በአንድ የብሔር ክልል ወሰን ውስጥ ብቻ አይኖሩም፡፡ ስለሆነም በአንድ ክልል ውስጥ የአንድ ብሔር የበላይነት እንዲሰፍን ማድረግ፣ በክልሉ የበላይነት ካገኘው ብሔር ውጭ የሆኑትን ዜጎች ማግለል ነው፡፡

> *…[አንድ የብሔር ቡድንን የሚወክል ክልል ይገንጠል ቢባል] በክልሉ በይፋ የበላይነት ከተሰጠው ብሔር ውጭ የሆኑት ሰዎች ላይ ከቀዬ የማፈናቀልና እስከዘር ማጥፋት ሊደርሱ የሚችሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ በደሎች ሊፈጸሙባቸው ይችላሉ፡፡… መገንጠሉ የቆየ ምሬት ማብቂያ ሳይሆን የአዲስ ምሬት መጀመሪያ [ይሆናል]፡፡*

በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የማይተገበር በመሆኑ አንድ የአገሪቱ (የብሔር ቡድን) ክልል ይገንጠል ቢባል በውስጡ ያሉት (በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በዘርም ሆነ በሌላ የማንነት መለኪያዎች) አናሳ የሆኑት ዜጎች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች አይከበሩም፡፡ ይህም ማለት በክልሉ በይፋ የበላይነት ከተሰጠው ብሔር ውጭ የሆኑት ሰዎች ላይ ከቀዬ የማፈናቀልና እስከዘር ማጥፋት ሊደርሱ የሚችሉ ፖለቲካዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ በደሎች ሊፈጸሙባቸው ይችላሉ፡፡[98]

ክልሎቹ ራሳቸው የብሔር ልዩነት ያለባቸው በመሆናቸው በብሔር ቡድን የመገንጠል መብት ተቀባይነት ካገኘ አደገኛ ሁኔታ ይፈጠራል፡፡ ምክንያቱም መገንጠሉ የቆየ ምሬት ማብቂያ ሳይሆን የአዲስ ምሬት መጀመሪያ ስለሚሆን ነው፡፡[99]

ይህም ህወሃት/ኢሕአዴግ ስልጣን ከመያዙ በፊት የተለያዩ ኃይሎች ከደርግ ጋር ውጊያ ሲያደርጉ የነበሩባቸውን የማህበራዊ ፍትሕ ጥያቄዎች ያስታውሰናል፡፡ በአገር ደረጃ ለነበረው ጭቆና ዴሞክራሲያዊ መፍትሔ ስላልተገኘለት ምላሹ አገር አቀፍ የትጥቅ ትግል ነበር፡፡ በተመሳሳይ ሁኔታ (በብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም የሚቀነቀነው) በብሔር ቡድን የመገንጠል ጉዳይም ጭቆናን ስለማያስቀር (ቀደም ሲል አገር አቀፍ የነበረው የተቃውሞ የትጥቅ ትግል) ወደክልል ደረጃ ወርዶ እንዲጀመር ማድረጉና ሠላም ማደፍረሱ አይቀርም፡፡

ሌላው በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ በብሔር ቡድን መገንጠል ተመራጭ የማይሆንበት ምክንያት አብዛኞቹ የብሔር ቡድኖች በያዙት መሬት ስፋት እና/ወይም በሕዝብ ብዛት አነስተኛ በመሆናቸው ራሳቸውን የቻሉ አገሮችን መስርተው በዘላቂነት ለማቆየት አይችሉም፡፡ በመሆኑም በስራቸው የሚገኙት ሕዝቦች ይበልጥ ተጠቃሚ የሚሆኑት በሰፊ አገር ከሌላው ሕዝብ ጋር የእኩልነት መብት አግኝተው በመኖር ነው፡፡

በአጭሩ በብሔር ቡድን መከፋፈልም ሆነ መገንጠል ዘላቂ ሠላም የሚያመጣ መፍትሔ ባለመሆኑ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ፌደራሊዝም በብሔር ቡድን ተከፋፍሎ የመገንጠልን መብት የሚያረጋግጥ ሊሆን አይገባም፡፡

### 4.2.2. <u>የፌደራላዊው ስርዓት አባል የሚሆኑት የአገሪቱ ክፍሎች በምን መስፈርት ይከፋፈሉ?</u>

መንግስት የአንድን አገር ሕዝቦች የረጅም ጊዜ ፖለቲካዊ ስንጥቀቶች (cleavages) የመቅረጽ ትልቅ ሚና እንዳለው ይታወቃል፡፡[100] በኢትዮጵያም ከ20 ዓመታት በላይ የዘለቀው

የህወሃት/ኢ.ሕአዴግ አገዛዝ ብሔርን ብቸኛው የክልል መንግስታት ማዋቀሪያና የበጀትና የስልጣን ማከፋፈያ መስፈርት በማድረግ አገሪቱ የብሔር ቡድኖች ስብስብ ብቻ እንደሆነችና ዜጐቹም በዋናነት ከብሔር ቡድናቸው አንፃር የሚታዩበትን መንገድ ለመቅረጽ ሞክሯል፡፡ ይህ ስህተት የሆነ አካሄድ መስተካከል አለበት፡፡

የፌደራል መንግስት ስርዓቱ የአገሪቱን ሕዝቦች በየትኛውም ዓይነት የማንነት መስፈርት መከፋፈል የለበትም፡፡ ምክንያቱም በማንነት ላይ የተመሰረተ የሕዝቦች መከፋፈል ገለልተኛ (neutral) አቋም ሊያንጸባርቅ አይችልም፡፡ በእያንዳንዱ የአገሪቱ ክፍል አንደኛውን ማንነት መርጦ ያንን ማንነት ለያዙት ዜጐች ተቋማዊ ወገናዊነትን ማሳየቱ አይቀርም፡፡ ዜጐች ደግሞ በዘር፣ በቋንቋ፣ በሃይማኖት፣ በፆታና በመሳሰሉት ማንነቶቻቸው ልዩነት ምክንያት አድሎ ሊፈጸምባቸው አይገባም:: (በተለይም በዚህ በሰለጠነው በ21ኛው ክፍለ ዘመን ላይ) ይህ የህወሃት/ኢ.ሕአዴግ የብሔር (የዘር) አፓርታይድ ስርዓት የኢትዮጵያ መንግስት መገለጫ ሆኖ መቀጠል የለበትም፡፡

*የፌደራል መንግስት ስርዓቱ የአገሪቱን ሕዝቦች በየትኛውም ዓይነት የማንነት መስፈርት መከፋፈል የለበትም፡፡ ምክንያቱም በማንነት ላይ የተመሰረተ የሕዝቦች መከፋፈል ገለልተኛ (neutral) አቋም ሊያንጸባርቅ አይችልም፡፡*

በማንነት ላይ የተመሰረተን አድሎ (ቢያንስ በተቋማዊ መልኩ) ለማስወገድና ለአገሪቱ ብልጽግናን ለማምጣት የተሻለው መንገድ የተለያዩትን የአገሪቱ ክፍሎች (ከአቀማመጣቸው በመነሳት) በኢኮኖሚያዊ መስፈርት መከፋፈል ነው፡፡ ይህ መስፈርት ገለልተኛ በመሆኑ የአገሪቱ ዜጐች በሙሉ በመላው አገሪቱ ውስጥ የኢኮኖሚ፣ የፖለቲካ፣ የማህበራዊ፣ የባሕል እና ሌሎች መብቶቻቸው እኩል እንዲከበሩላቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡ ተቋማዊ

ክፍፍል የሚደረገው በአገሪቱ መሬት ላይ እንጂ የአገሪቱ ዜጎች ላይ አይሆንም፡፡ በዚህ ምክንያት ስርዓቱ ዜጎችን በማንነት ምክንያት የሚያገልል አይሆንም፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በብሔር ቡድን የተደረገው የክልሎች አደረጃጀት መፍረስ አለበት፡፡ የፌደራል መንግስቱ አባል ተብለው የተዋቀሩት የብሔር ቡድን ክልሎች በሙሉ ከኢኮኖሚያዊ መስፈርት አንፃር ታይተው አነስ ወዳሉ ክፍለ ሃገሮች ቢከፋፈሉ መልካም ነው፡፡ ክፍፍሉ ሲፈጸም በብሔር ቡድን መገንጠልን ላለማበረታታት በተቻለ መጠን ክፍለ ሃገሮቹን በመጠን ማሳነስ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ የክፍለ ሃገሮቹ ቁጥር ያለአግባብ በዝቶ ለማስተዳደር እንዳያስቸግር አመጣጥኖ መከፋፈል ግድ ይላል፡፡

በአጠቃላይ ስልጣንን ከፌደራሉ መንግስት ወደእነዚህ ክፍለ ሃገሮች መንግስታት በማሸጋገር ዜጎች መብቶቻቸውን በቅርበትና በተሻለ ፍጥነት ለማስከበር የሚችሉበት ፌደራላዊ የመንግስት ስርዓት ማዋቀር አስፈላጊ ነው፡፡

## 4.3. ለዘላቂ ሠላምና የዜጎች መብቶች መከበር ዴሞክራሲ አስፈላጊ ስለመሆኑ

የኢትዮጵያ ታሪክ እንደሚያሳየው የአገሪቱ ሕዝብ የሚመራውን መርጦ አያውቅም፡፡ በህወሃት/ኢሕአዴግም ሆነ በቀድሞዎቹ አምባገነናዊ አገዛዞች የአገሪቱ ሕዝቦች (የትግራይንም ጨምሮ) ለበርካታ ዓይነት ጭቆናዎች መዳረጋቸው አያከራክርም፡፡ የኢትዮጵያ ሕዝብ በታሪኩ ብሶቶቹን በግልጽ ተናግሮ በሠላማዊ መንገድ መፍትሔ የሚያገኝበት ሁኔታ አልነበረም፤ አሁንም የለም፡፡

ታሪካችን የሚያሳየን እስከዛሬ ድረስ ያሉት የኢትዮጵያ መሪዎች ስልጣን ገደብ የሌለው መሆኑንና የዜጎችን የመብት ጥያቄዎች ከማስተናገድ ይልቅ በኃይል የመግታት ወይም

የመደምሰስ እርምጃ የሚወስዱ መሆናቸውን ነው፡፡[101] የዚህ ዓይነት ምላሽ ወደእርስ በርስ ጦርነት መምራቱ የጊዜ ጉዳይ ብቻ መሆኑ ይታወቃል፡፡

በመሆኑም በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ የወደፊት እጣ የሚወሰነው ህወሃት/ኢሕአዴግ የተለዩ ሃሳቦችን ግንዛቤ ውስጥ አስገብቶ ፖለቲካዊ ውይይቶችን የሚፈቅድ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማስፈን ባለው ፍላጎት ላይ ነው፡፡ ሆኖም እስከሁን የዚህ ዓይነት ፍላጎት አላሳየም፡፡[102]

> *በአሁኑ ጊዜ የኢትዮጵያ የወደፊት እጣ የሚወሰነው ህወሃት/ኢሕአዴግ … ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ለማስፈን ባለው ፍላጎት ላይ ነው፡፡*

እንደህወሃት/ኢሕአዴግ ያለው የይስሙላ ዴሞክራሲ አደገኛ ነው፡፡ ምክንያቱም ከሌሎች አገሮች ልምዶች እንደታየው የአንድ አገር መንግስት በአንድ በኩል ሁሉንም ዓይነት የሕዝባዊ አመጽ እድሎች ለማፈን የሚያችል አምባገነንነት የሌለው ከሆነ፣ በሌላ በኩል ደግሞ ለዋና ዋና ብሶቶች መፍትሔ ለመስጠት የሚያስችል ዴሞክራሲያዊነትም ከሌለው፣ ከሌሎቹ ሁሉ በላቀ ሁኔታ የእርስ በርስ ጦርነት የመቀስቀስ አደጋ እንዳለበት ይታመናል፡፡[103]

ፖለቲካዊ ስርዓቱ አፋኝ ሲሆን የብሔር ግጭቶች ተደብቀው ይቆዩና አጋጣሚው ሲመች (ለምሳሌ የአገሪቱ መንግስት ሲዳከም) ከፍተኛ ብጥብጥና ሁከት ያስከትላሉ፡፡ ሆኖም የፖለቲካ ስርዓቱ የመደራጀት መብትን ከፈቀደ ብሔር ተኮር የሆነ ቅስቀሳ በዴሞክራሲያዊ ፖለቲካው የበላይነቱን ቢይዝም እንኳን ከብሔር ጋር የተያያዙ ግጭቶችና ሁከቶች በሠላማዊ መንገድ ፖለቲካዊ መፍትሔ ያገኛሉ፡፡[104]

ስለዚህ ሕዝቡ ከአፈናና ከጭቆና ተላቅቆ መብቶቹን ለማስከበር የሚችለው (በማንኛውም የማንነት መስፈርት አናሳ የሚባሉትን ጨምሮ የሁሉንም ዜጎች) መሠረታዊ ሰብዓዊ

መብቶችን የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በሥራ ላይ ከዋለ ብቻ ነው፡፡ በምንም መለኪያ ዘላቂ ሠላም ለማስፈን ከአምባገነናዊ ሥርዓት ይልቅ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የላቀ ሚና እንደሚጫወት ግልጽ ነው፡፡

> *ሕዝቡ ከአፈናና ከጭቆና ተላቅቆ መብቶቹን ለማስከበር የሚችለው… [የሁሉንም ዜጎች]… መሠረታዊ ሰብዓዊ መብቶችን የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በሥራ ላይ ከዋለ ብቻ ነው፡፡*

ዘላቂ ሠላም ለማስፈንና የዜጎችን መብቶች የሚያረጋግጥ ምቹ ሁኔታ ለመፍጠር የፌደራሉ ሥርዓት ዴሞክራሲያዊ መሆን እንዳለበት ይታመናል፡፡ ባደጉትና (እንደሕንድና ብራዚል በመሳሰሉት) በማደግ ላይ ያሉ አገሮች የሰፈነው ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ዜጎች ብሶቶቻቸውን የሚገልጹባቸውንና መፍትሔ የሚያገኙባቸውን ሠላማዊ መንገዶች በማመቻቸት ከጭቆናና አፈና የሚመነጩ የእርስ በርስ ጦርነቶችን ለመከላከል ተችሏል፡፡ ስለሆነም የዴሞክራሲያዊ ስርዓት አስፈላጊነት የሚታወቀው በንድፈ ሃሳብ ደረጃ ብቻ ሳይሆን በተግባር በታዩ የሌሎች አገሮች ልምዶች ጭምር ነው፡፡

ከዚህ የሚቀጥለው ጥያቄ ለአገሪቱ ምን ዓይነት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያስፈልጋታል? የሚለው ነው፡፡ ከፍተኛ የማንነት (በተለይም የቋንቋና የሃይማኖት) ልዩነቶች ባሉባቸው አገሮች ከዚህ ቀደም በፖለቲካ ሳይንቲስቶች የተሻሉ መፍትሔዎች ይሆናሉ የተባሉ ሃሳቦች ቀርበዋል፡፡

ከእነዚህ ውስጥ ሁለት ዋና ዋና ዝርዝር ሃሳቦች በዚህ ጽሑፍ ቀርበዋል፡፡ የመጀመሪያው በ1970 በላይፕሃርት የተዘጋጀው (እና ከዚያ በኋላ ማሻሻያ የተደረገበት) ኮንሶሲዬሺናሊዝም (consociationalism) ሲሆን ሌላኛው ደግሞ በሆሮዊትዝ የቀረበው ፖለቲካዊ የማነቃቂያ ዘዴ (ከዚያ በኋላ በራይሊ ተሻሽሎ ‹‹ሴንትራፔታሊዝም›› ተብሎ የተጠራው) ነው፡፡[105]

**<u>ኮንሶሲዬሺናሊዝም</u>**

ኮንሶሲዬሺናዊ ዴሞክራሲ የሚባለው ከአብላጫ ድምጽ ሕግ የሚለይ ሲሆን አራት ዋና ዋና ባሕሪያትን ያካትታል፡፡ እነርሱም፡- (1) የተለያዩ አመለካከቶች ያሏቸውን ዋና ዋና የሕብረተሰብ ክፍሎች በሙሉ የሚወክሉ የፖለቲካ መሪዎች ታላቅ ሕብረት፣ (2) በጣም አስፈላጊ የሆኑትን የአናሳ ቡድኖችን ጥቅሞች ለመጠበቅ (እንዲከበሩ ለማድረግ) የሚያስችል የጋራ ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት፣ (3) የተመጣጠነ የፖለቲካ ውክልና፣ የመንግስት ሥራ ሹመቶችና የበጀት ክፍፍል እንዲሁም (4) ለእያንዳንዱ የሕብረተሰብ ክፍል ከፍተኛ የራስን ጉዳይ በራስ የመወሰን ነፃነት ናቸው፡፡[106] በላይኘሃርት[107] አመለካከት መሠረት የመንግስት ስልጣን የማግኘት እድል አቋሞችን ለማለዘብና አስታራቂ ሃሳቦችን የመቀበል ፍላጐትን ለማነቃቃት ይረዳል፡፡

የኢትዮጵያ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም (በተግባር ባይፈጸምም በንድፈ ሃሳብ ደረጃ) ከኮንሶሲዬሺናዊ ዴሞክራሲ ጋር የሚመሳሰለው የብሔር ቡድኖች የራሳቸውን ጉዳይ በራሳቸው የሚወስኑበት መብት ላይ ማተኮሩና የብሔር ቡድኖቹ አንድ ጊዜ ከተመሰረቱ በኋላ ሊቀየሩ የማይችሉ መሆናቸውን ታሳቢ ማድረጉ ላይ ነው፡፡ የሚለየው ደግሞ ለአናሳ የብሔር ቡድኖች ተወካዮች ድምጽን በድምጽ የመሻር መብት (veto power) የማይሰጥ በመሆኑና (በንድፈ ሃሳብ ደረጃ) ስልጣን ለመጋራት በተደረገ ስምምነት በቅድሚያ ያልተወሰኑ ፓርቲዎች ወይም ቡድኖች የፖለቲካዊ ምርጫዎች ውጤት ላይ ተጽዕኖ ሊያደርጉ መቻላቸው ነው፡፡

ኮንሶሲዬሺናሊዝም ዴሞክራሲያዊ ተቃውሞን መዘንጋቱንና ከልክ በላይ ውስን (limited) ወደሆነ የመንግስት ዓይነት ማዘንበሉን እንዲሁም ሊንቀሳቀስ የማይችል (immobilism) መሆኑን የሚጠቁሙ በርካታ ነቀፌታዎች ቀርበውበታል፡፡[108]

ከእነዚህ ነቀፌታዎች በመነሳት በሆሮዊትዝም[109] ተጨማሪ ትችት ቀርቧል፡፡ ይህም ከባድ ክፍፍል ባለባቸው ቦታዎች (በቡድኖቹ መካከል የሚመሰረቱ) ታላቅ ሕብረቶችን ማቋቋም አይቻልም የሚል ሲሆን ምክንያቱም የዚህ ዓይነት ሕብረት ከሥር ከመሰረቱ የቡድን ጥቅሞች ተላልፈው ተሰጥተዋል የሚል የተቃውሞ ክስ እንዲቀርብ ማድረጉ የማይቀር በመሆኑ ነው፡፡

የኮንሶሲዬሺናዊ ዴሞክራሲ አመንጪ የሆኑት ላይፕሃርት ራሳቸው የቀድሞ ሥራቸው ላይ (ታላቅ ሕብረት የሚመሰርቱትን ቡድኖች አስቀድሞ መወሰን ተገቢ አይደለም በሚል) ትችት ካቀረቡ በኋላ በአሁኑ ጊዜ ከፍተኛ ተቀባይነት ባገኘው ኮንስትራክቲቪስት አመለካከት መሠረት አሻሽለውታል፡፡[110]

__ሴንትሪፔታሊዝም__

ሁለተኛው የመፍትሔ ሃሳብ በሆሮዊትዝ[111] የቀረበው ሲሆን ለዘብተኛ ብሔርተኝነትን ለማበረታታት በፖለቲካዊ የምርጫ ስርዓትም ሆነ በሌሎች የተለያዩ ተቋማት ፖለቲካዊ የማነቃቂያ ዘዴዎችን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን ይጠቁማል፡፡ የኮንሶሲዬሺናሊዝምን (በቡድኖች መካከል ሰጥቶ የመቀበልን ወይም አስታራቂ ሃሳብ የማምጣት ፍላጐትን ለማምጣት ያለመቻል) ድክመት ያርማል ተብሎ የታመነበትም ነው፡፡

ይህም የሚሆነው ፖለቲከኞች ለመመረጥ ሲሉ የሌሎችን ቡድኖች አባላት ድምጽ ለማግኘት የሚገፋፉበትን ሁኔታ በመፍጠር ነው፡፡ በተለይም የምርጫ ድምጾችን የማሰራጨት[112] መስፈርት ያለው፣ በአማራጭ ድምጽ የሚሰጥበት[113] እና (ከኮንሶሲዬሺናሊዝም በተለየ ሁኔታ) በተለያዩ ቡድኖች ደጋፊዎች መካከል የድምጽ ልውውጥ ማድረግን ታሳቢ የሚያደርግ (ብሔር ወይም ዘር የማይገድበው) የድምጽ አሰባሰብ ዘዴ[114] (electoral mechanism of vote pooling) በሥራ ላይ ማዋል አስፈላጊ መሆኑ ተመልክቷል፡፡[115]

የሴንትሪፔታሊዝም ዋና ድክመት የሚጠቀመው የአብላጫ ጽምጽ ስርዓት አናሳ ቡድኖችን ሊጉዳ ስለሚችል ነው፡፡ በመሆኑም ከዚህ ጋር በተያያዘ ተመጣጣኝ ውክልና (proportional representation) የሚሰጥበትን የምርጫ ስርዓት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባት ጠቃሚ ይሆናል፡፡

የላይኝሃርት የተሻሻለ ሥራ የሚያመለክተው (እንደ ኢትዮጵያ፣ ናይጄሪያና ዩጋንዳ ያሉ) ሰፊ የማንነት ልዩነቶችና አብላጫ ድምጽ (ያገኘ ተወዳዳሪ አሸናፊ የሚሆንበት) የምርጫ ሥርዓት (high ethnic fractionalization and majoritarian electoral systems) ያለባቸው አገሮች ለመንግስት ውድቀት የተጋለጡ ናቸው፡፡ በአንፃሩ እንደ ቤኒን ደቡብ አፍሪካና ሱሪናም ያሉት አገሮች እንደነ ኢትዮጵያ ሰፊ የማንነት ልዩነቶች ያሉባቸው ቢሆንም የሚከተሉት የምርጫ ስርዓት ተመጣጣኝ ውክልና ላይ የተመሰረተ በመሆኑ በስኬታማነት፣ በሠላምና መረጋጋት የተሻሉ እንደሆኑ ተነግሯል፡፡ ይህን ድምዳሜ ለማረጋገጥ የተወሰኑ ጥናቶችም ተካሂደዋል፡፡[116]

ኮንሶሲየሽናሊዝምም ሆነ ሴንትሪፔታሊዝም የየራሳቸው የሆኑ ድክመቶች ስላሏቸው አንዳቸውን በቀጥታ በኢትዮጵያ ሥራ ላይ ማዋል ተገቢ አይሆንም፡፡ በዚህም ምክንያት በፖለቲካዊ የምርጫ ስርዓቶቻቸው ዴሞክራሲያዊ የሆኑና እንደኢትዮጵያ ከፍተኛ የማንነት ልዩነቶች ያሉባቸውን አገሮች ምርጥ ምርጥ ልምዶች በሚገባ አጥንቶና ከአገሪቱ ተጨባጭ ሁኔታዎች ጋር አገናዝቦ በመወያየት ምን ዓይነት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ለኢትዮጵያ እንደሚበጅ መወሰንና ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ይሆናል፡፡

### 4.4. ፌደራሊዝሙ የቋንቋን ጉዳይ ምን መፍትሔ ይስጠው?

የኢትዮጵያ የሕዝብ ብዛት ሲታይ የኦሮሞና የአማራ[117] ‹‹ብሔሮች›› እያንዳንዳቸው የአገሪቱን ሕዝቦች ከ30 በመቶ በላይ የያዙ ሲሆን የሌሎቹ ብሔሮች ተወላጆች ቁጥር

በአንድ ላይ 35 በመቶ አካባቢ ይሆናል፡፡[118] ይህም የኦሮምኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች ብዛት ቀላል አለመሆኑን ያሳያል፡፡

በዚህም ምክንያት የኦሮምኛና የአማርኛ ቋንቋዎች ብሔራዊ የመግባቢያ ቋንቋዎች እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊና ፍትሐዊ ነው፡፡ በተጨማሪም ዜጐች እንደአቅማቸውና እንደፍላጐታቸው ሌሎቹን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እንዲማሩ የማበረታታትና አገልግሎቶቹንም ተደራሽ የማድረግ ሥራ መሠራት አለበት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች በሙሉ (በማናቸውም የአገሪቱ አካባቢዎች) በሚገኙ ትምህርት ቤቶችና ሌሎች ማህበራዊ ተቋማት ውስጥ ጥቅም ላይ የሚውሉበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል፡፡ ይህም የሚሆነው *በየትኛውም አካባቢ* የየቋንቋው ተናጋሪዎች ብዛትና ፍላጐት እየታየ ዜጐች በሚመርጡት ቋንቋ የማህበራዊ ተቋማትን አገልግሎት ለማግኘት እንዲችሉ በማድረግ ነው፡፡

## 5. ማጠቃለያ

የዚህ ጽሑፍ ዓላማ የህወሃት/ኢሕአዴግ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም ለኢትዮጵያውያን ምን ጥቅሞችን እንዳስገኘና ምን ጉዳቶችን እንዳስከተለ በአጭሩ ለመመርመርና ብሔር ተኮር ያልሆኑ ሌሎች አማራጮችን መጠቆም ነው፡፡

በኢትዮጵያ የፌደራሉ ሥርዓት አባል የሆኑት ክልሎች የተዋቀሩበት መስፈርት ብሔር (ዘር) ነው፡፡ ይህን መስፈርት ሕግ ያደረገው ህወሃት ሲሆን በሕዝብ ይሁንታ ሳይሆን በግዴታ ነው፡፡

ህወሃት ከመነሻው ትግራይን ከኢትዮጵያ የመገንጠል ዓላማ የነበረው <<የትግሬ ብሔር ነፃ አውጪ ነኝ>> የሚል ድርጅት ነበረ፡፡ ሆኖም በትጥቅ ትግል አሸናፊነቱ ምክንያት

የኢትዮጵያን የመንግስት ስልጣን ለመጠቅለል በቅቷል፡፡ ህወሃት የአገሪቱን ዘርፈ-ብዙ ችግሮች ከመፍታት ይልቅ በጠባብ ብሔርተኝነትና በኢኮኖሚ ጥቅሙ ላይ በማተኮሩ የአገርን ጥቅም ከማስጠበቅ አንፃር በርካታ ዜጐች በጥርጣሬ ያዩታል፡፡

ህወሃት አገሪቱን ለመግዛት እንዲመቸው ኢሕአዴግ የሚባል የብሔር ተኮር የፖለቲካ ፓርቲዎች ቅንጅትና በብሔር ቡድን የተመሠረቱ አጋር የፖለቲካ ፓርቲዎችን በማቋቋም አገር አቀፍ የብሔር ቡድኖች ውክልና ያለው ለማስመሰል ሞክሯል፡፡ ሆኖም እነዚህ ስብስቦች ህወሃት የመሠረታቸውና የሚቆጣጠራቸው የይስሙላ ፓርቲዎች መሆናቸው የአደባባይ ምስጢር ከመሆኑም በላይ የአገሪቱ ዋና ዋና ስልጣኖች የተያዙት በህወሃት መሆኑ ይታወቃል፡፡

አምባገነኑ ህወሃት/ኢሕአዴግ ለሚያሳልፋቸው ውሳኔዎች ዋና መመዘኛው የሚሰጠው ማንኛውም ውሳኔ ስልጣን ላይ ለመቆየት የሚያስችለው መሆን አለመሆኑ ነው፡፡

በመሆኑም ህወሃት ከማናቸውም የዜጐች ማንነቶች መካከል ብሔርን (በተለይም ቋንቋን) መርጦ የተለየና ትልቅ ትኩረት እንዲሰጠው አድርጓል፡፡ ይህን ያደረገውም የራሱን ዜጐችን ከፋፍሎ የመግዛት ዓላማ ለማሳካት እንጂ ዜጐች በዴሞክራሲያዊ መንገድ በብሔር ተደራጅተው የዚህ ዓይነት ስርዓት እንዲሰፍንላቸው ስለጠየቁ አልነበረም፡፡

ህወሃት የሚያራምደውና በስታሊን ንድፈ ሃሳብ ላይ የተመሰረተው ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም በሥራ ላይ የዋለባቸው (ሶሻሊስት) አገሮች ልምዶች የሚያሳየው አገርን በብሔር ቡድኖች ከፋፍሎ የመገነጣጠልና ማለቂያ የሌላቸው ብሔር ተኮር ግጭቶችን ማስከተሉ ነው፡፡

የብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ዋነኛ ተጠቃሚ አምባገነኑን ህወሃት/ኢሕአዴግን ሲሆን ሕዝቡን በብሔር ቡድን ከፋፍሎ ለመግዛት ስለሚያስችለው በዜጎች የጋራ አመጽ ምክንያት ስልጣኑን እንዳያጣ ለማድረግ ይጠቅመዋል፡፡ በሁለተኛ ደረጃ የሚጠቀሙት ደግሞ (በተለይም ስልጣን ለመያዝ የሚጓጉና) የግል ጥቅማቸውን የሚያሳድዱ ብሔር ተኮር ልሂቃን ወይም አክቲቪስቶች ናቸው፡፡

የህወሃት ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም በዜጎች ላይ ካስከተላቸው በርካታ አሉታዊ ውጤቶች መካከል ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

(1) ዜጎች ያለፍላጎታቸው ብሔር መምረጥ እንዲኖርባቸው በማስገደዱ ምክንያት ዜጎች ያለፍላጎታቸው በብሔር አጥር እንዲታጠሩና ከሌሎች ማንነቶቻቸው ይልቅ በዋናነት ወይም ሙሉ በሙሉ የብሔር ማንነታቸው ላይ እንዲያተኩሩ ማስገደዱ፣

(2) ብሔር (ከሌሎች የዜጎች ማንነቶች ተነጥሎ) ይፋ የሆነ ብቸኛ (ተቋማዊ) የበላይነት የተሰጠው በመሆኑ ዜጎች በአመዛኙ የብሔር ልዩነታቸው ላይ ብቻ እንዲያተኩሩ በማድረጉ በዜጎች መካከል ‹‹የኛ›› እና ‹‹የነሱ›› የሚል ከፋፋይ የሆነ ስሜት እንዲዳብርና ‹‹የኛ›› ከሚሉት የብሔር ቡድን ውጭ የሆኑትን ኢትዮጵያውያን እንዲያገልሉ ማድረጉ፣

(3) ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም የብሔር ቡድኖችን እስከመገንጠል መብት ስለሚሰጣቸው ትብብርና ሰጥቶ መቀበልን ባለማበረታታቱ ምክንያት (በተለይም የግል ጥቅማቸውን በሚያስቀድሙ ብሔር ተኮር ልሂቃን በኩል) መገንጠል እንደዋና አማራጭ እንዲታይ ከማድረጉም በላይ ውሳኔ የሚያስፈልጓቸውን ጉዳዮች ሰፋ አድርጎ ከማየትና የጋራ መፍትሔ ከመፈለግ ማገዱ፣

(4) ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም እያንዳንዱ የብሔር ቡድን በተፈጥሮ በአንድ አካባቢ ተሰባስቦ፣ በግልጽ በተከለለ ክልል ውስጥ እንደሚኖር ታሳቢ ያደርጋል፡፡ ይህ የአገሪቱን ተጨባጭ ሁኔታ ያላገናዘበ ስህተት በመሆኑ ዘላቂ ሠላም ሊያመጣ አለመቻሉ፣

(5) ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም የክልል መንግስት ማቋቋምን በተመለከተ የብሔሮችን እኩልነት ሊያስከብር አይችልም፡፡ ምክንያቱም በኢትዮጵያ ያሉት ብሔሮች ከ80 በላይ ቢሆኑም 80 የክልል መንግስታት በማቋቋም ሁሉንም በዚህ ረገድ እኩል ማድረግ የማይቻል መሆኑ፣

(6) ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ብሔራዊ ቋንቋን በሚመለከት ተገቢ ምላሽ አልሰጠም፡፡ ምክንያቱም የአገሪቱን 80 ቋንቋዎች በሙሉ እኩል የአገሪቱ ዜጎች በአገር አቀፍ ደረጃ ለመግባባት የሚጠቀሙባቸው ቋንቋዎች ሊያደርጋቸው አይችልም፡፡ ይህ እንኳን እንደኢትዮጵያ ባሉ ድሃ አገሮችና በበለፀጉት አገሮችም ሊተገበር አለመቻሉ፣

(7) ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም በየክልሎቹ ውስጥ ያሉትን አናሳ ብሔሮች መብቶች ሊያስከብር አይችልም፡፡ ምክንያቱም (በክልል ደረጃ አናሳ የሆኑት) ዜጎች በክልል ደረጃ አብላጫ ድርሻ (majority) ባለው የብሔር ቡድን ለኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መገለል ይጋለጣሉ፡፡ ይህም ሠላም የማደፍረስ ውጤት ማስከተሉ፣

(8) ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም የአገሪቱ ሃብት ለሕዝብ ተደራሽ እንዲሆን የሚያደርገው በብሔር መስፈርት በመሆኑ በብሔር ቡድኖች መካከል ግጭትን መፍጠሩ እንዲሁም ማባባሱ፣ እና

(9) ብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ከሁሉም የላቀ (ዜጎችን በሙሉ የሚያካትት) አገራዊ ብሔርተኝነት እንዳይዳብር ማድረጉ ናቸው፡፡

በመሆኑም የህወሃት/ ኢሕአዴግ ብሔር ተኮር ፌደራሊዝም የአገሪቱን ሕዝቦች የዜግነት መብቶች ከማስከበር፣ ዘላቂ ሰላም ከማስፈንና የአገሪቱን የግዛት አንድነት ከማስጠበቅ አኳያ ጎጂ ከመሆኑም በላይ (የትግራይን ጨምሮ የየትኛውም ብሔር ተወላጅ ለሆኑ) የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዘርፈ ብዙ ጭቆናዎች መፍትሔ ሊሆንም አይችልም፡፡

ከታሪክና ከልምድ መማር የምንችለው በኢትዮጵያ *አስገዳጅ አንድነትም* (ማለትም የማዋሃድ ግፊትም) ሆነ *አስገዳጅ ልዩነት* (ማለትም በብሔር ልዩነት ላይ የሚያተኩረው ስታሊናዊው የህወሃት ፌደራሊዝም) ጽንፈኛና ጊዜ ያለፈባቸው አካሄዶች ከመሆናቸውም በላይ ለዜጎች ጭቆናዎች ዘላቂ መፍትሔ የሚሰጡ አይደሉም፡፡

በሌላ በኩል የሱማሌ በጎሳ የመከፋፈል ልምድ የሚያሳየን ደግሞ (እንኳን ሰፊ የማንነት ልዩነቶች ባሉባቸው እንደኢትዮጵያ ባሉ አገሮች ይቅርና እንደሱማሌ በቋንቋ፣ በሃይማኖትና በባህል ተመሳሳይ የሆኑ ዜጎች እንኳን) ዜጎችን ከሚያመሳስሏቸው ነገሮች ይልቅ ልዩነቶቻቸው ላይ ማተኮር የአገርን ሠላምና አንድነት የሚያናጋ መሆኑን ነው፡፡ ሱማሌ በጎሳ ቡድኖች እንደተከፋፈለችው ሁሉ ኢትዮጵያም በብሔር ቡድኖች ከተከፋፈለች የእኛም አገር የሱማሌ እጣ እንደማይደርሳት ምንም መተማመኛ የለም፡፡ ውጤቱም አብሮ መውደቅ እንጂ አገርን ማጠናከር ሊሆን አይችልም፡፡

ኢትዮጵያውያን በሙሉ በአንድ አገር ውስጥ አብረው ቢኖሩ ከተፈጥሮ ሃብት፣ ከመሬት ስፋትና ከሕዝብ ቁጥር ብዛት አኳያ የተሻለ ተጠቃሚዎች ይሆናሉ፡፡ ወደትናንሽ አገሮች ከመበታተን ይልቅ የዚህ ዓይነቱ መደጋገፍ የተሻሉ የጋራ ጥቅሞችን ያስገኛል፡፡ የጋራ ብልጽግና የማምጣት እድሉም የሠፋ ይሆናል፡፡

ይህን ለማሳካት ደግሞ አገራዊ ብሔርተኝነት ላይ ያተኮረ፣ በዜጐች ላይ የመዋሃድ ግፊት የማያደርግ፣ ዜጐችን በማንነት ከፋፍሎ አድሎ የማያደርግ እንዲሁም የሁሉንም ዜጐች መሠረታዊ መብቶች በእኩልነት አስከብሮ ለመምራት የሚችል አገራዊ ኃይል ያስፈልጋል፡፡

ይህ ኃይል ዜጐችን በሙሉ የሚያሳትፍ ዴሞክራሲያዊና ፌደራላዊ የሆነ ስርዓት በማስፈን (የቋንቋ፣ የሃይማኖት፣ የፆታና የመሳሰሉትን ጨምሮ) የዜጐችን ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች በተግባር ማስከበር ይኖርበታል፡፡ በተጨማሪም ዜጐች የሚመሳሰሉባቸውና የጋራ ጥቅሞች የሚያስገኙላቸው ጉዳዮች ላይ እንዲያተኩሩ ሊያደርግ ይገባል፡፡

በኢትዮጵያ እስከዛሬ ያለው ዋናው ችግር ዜጐች ብሶታቸውን መተንፈሻና በሠላማዊ መንገድ መፍትሔ ማግኛ መንገድ ማጣታቸው ነው፡፡ የመሪዎቻችን ስልጣን ገደብ የለሽ ከመሆኑም በላይ መሪዎቹ  የመብት ጥያቄ ሲነሳ አይወዱም፡፡ ‹‹አርፋችሁ ተገዙ›› የሚለውን ፍላጐታቸውን ለማስረገጥ የኃይል እርምጃ ይወስዳሉ፡፡ በዚህም ፀጥ የሚለው በፍርሃት ፀጥ ይላል፣ የሚታሰረው ይታሰራል፣ የሚሞተው ይሞታል፣ የሚሰደደው ይሰደዳል፣ ሌላው ደግሞ ነፍጥ የያዙ ቡድኖችን ይቀላቀላል፡፡ ከእነዚህ ሌላ መንገድ የለም፡፡

ለኢትዮጵያ ታሪካዊ ችግሮች ሁሉ መፍትሔው የሚገኘው ከብሔር ጋር የተያያዘን ጭቆና ለብቻ በመነጠል ሳይሆን የጭቆናዎቹን ዓይነቶችና ውስብስብነት አገናዝቦ ለሁሉም ተገቢውን ምላሽ በመስጠት ነው፡፡ በመሆኑም በኢትዮጵያ ቢመሠረት ተመራጭ የሚሆነው ፌደራላዊ የመንግስት ሥርዓት በጥቅሉ የሚከተሉትን ቢያካትት መልካም ነው፡-

1. በብሔር ቡድን መከፋፈልም ሆነ መገንጠል ዘላቂ ሠላም የሚያመጣ መፍትሔ ባለመሆኑ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልጋት ፌደራሊዝም በብሔር ቡድን ተከፋፍሎ

የመገንጠልን መብት የሚያረጋግጥ ሊሆን አይገባም፡፡ ምክንያቱም በአገሪቱ የተፈጥሮም ሆነ በስምምነት በግልጽ የተከለለ የብሔር ቡድኖች ወሰን የሌለ በመሆኑ እንዲሁም በርካታ ዜጎች ‹‹በብሔር ክልላቸው›› ውስጥ ስለማይኖሩ የመገንጠል ጥያቄ ቢመጣ በብሔር ቡድኖች መካከል ማለቂያ የማይኖረው የድንበር ግጭትና እልቂት መፈጠሩ አይቀርም፡፡

2. የፌደራል መንግስት ስርዓቱ የአገሪቱን ሕዝቦች በየትኛውም ዓይነት የማንነት መስፈርት መክፈል የለበትም፡፡ ምክንያቱም በማንነት ላይ የተመሰረተ የሕዝቦች መከፋፈል ገለልተኛ (neutral) አቋም ሊያንጸባርቅ አይችልም፡፡ በምትኩ የተለያዩትን የአገሪቱ ክፍሎች (ከአቀማመጣቸው በመነሳት) በኢኮኖሚያዊ መስፈርት መከፋፈል የተሻለ ነው፡፡ ይህ መስፈርት ገለልተኛ በመሆኑ የአገሪቱ ዜጎች በሙሉ በመላው አገሪቱ ውስጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ፣ የባሕል እና ሌሎች መብቶቻቸው እኩል እንዲከበሩላቸው ሁኔታዎችን ያመቻቻል፡፡

3. ስልጣንን ከፌደራሉ መንግስት ወደእነዚህ ክፍለ ሃገሮች መንግስታት በማሸጋገር ዜጎች መብቶቻቸውን በቅርበትና በተሻለ ፍጥነት ለማስከበር የሚችሉበት ፌደራላዊ ስርዓት ማዋቀር አስፈላጊ ነው፡፡

4. ዜጎች ከአፈናና ከጭቆና ተላቅቀው መብቶቻቸውን ለማስከበር የሚችሉት ሰብዓዊ መብቶችን (በወረቀት ሳይሆን በተግባር) የሚያረጋግጥ ዴሞክራሲያዊ ስርዓት በሥራ ላይ ከዋለ ብቻ ነው፡፡ ምን ዓይነት ዴሞክራሲያዊ ስርዓት ያስፈልጋል የሚለው ከሌሎች አገሮች ልምዶች በመነሳትና የኢትዮጵያን ነባራዊ ሁኔታዎች በማገናዘብ በጥናትና በስምምነት ሊወሰን የሚችል ነው፡፡

5. ከቋንቋዎቹ ተጠቃሚዎች ብዛት አንፃር የኦሮምኛና የአማርኛ ቋንቋዎች ብሔራዊ የመግባቢያ ቋንቋዎች እንዲሆኑ ማድረግ አስፈላጊና ፍትሐዊ ነው፡፡ በተጨማሪም

ዜጐች እንደአቅማቸውና እንደፍላጐታቸው ሌሎቹን የኢትዮጵያ ቋንቋዎች እንዲማሩ የማበረታታትና አገልግሎቶቹንም *በየትኛውም* የአገሪቱ ክፍል ተደራሽ የማድረግ ሥራ መሠራት ይኖርበታል፡፡

## 6. ዋቢ ጽሑፎች


1. የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት (1987)
2. ጌታቸው ኃይሌ (1997)፣ የአባ ባሕርይ ድርሰቶች፡ ኦሮሞዎችን ከሚመለከቱ ሌሎች ሰነዶች ጋራ፣ አዲስ አበባ
3. Aalen, Lovise, 2002, Ethnic Federalism in a Dominant Party State:The Ethiopian Experience 1991-2000, Report 2002:2, Chr. Michelsen Institute *Development Studies and Human Rights*
4. Abraham, Kinfe 2004. Ethio-Eritrean History and the Ethio-Eritrean War: Liberation Struggle, Statehood and bilateral Political Economic Social and Diplomatic Relations EIIPD and HADAD London, Stockholm, New York
5. Aregawi Berhe, 2008, A Political History of the Tigray People's Liberation Front (1975-1991): Revolt, Ideology and Mobilisation in Ethiopia , Amsterdam
6. Arel, Dominique *Language Categories in Censuses: Backward- or Forward-Looking?* Census and identity [electronic resource] : the politics of race, ethnicity, and language in national census, 2002 http://site.ebrary.com/lib/princeton/Doc?id=10040861
7. Baseline Study for mapping Violent Conflict In Ethiopia, African Rally for Peace and Development, Nov. 2008 http://www.internal-displacement.org/8025708F004CE90B/(httpDocuments)/F1D70F09138C38B5C125760E00401F9C/$file/Conflict-Study-Ethiopia.pdf
8. Brubaker, Rogers 1996. *Nationalism Reframed: Nationhood and the National Question in the New Europe* Cambridge University Press
9. Cambridge Encyclopedia Vol. 55, http://encyclopedia.stateuniversity.com/pages/16445/Oromo.html
10. Chandra, Kanchan *Cumulative Findings in the Study of Ethnic Politics* APSA-CP Newsletter, vol. 12, Winter 2001, chap. 1, pp. 7-11
11. Eller, Jack and Coughlan, Reed. 1993. The Poverty of Primordialism: The Demystification of the Ethnic Attachments, Ethnic and Racial Studies (April 1993), pp. 183-202
12. Gudina, Merera 2003. Ethiopia: Competing Ethnic Nationalisms and the Quest for Democracy, 1960-2000 Shaker Publishing, Netherlands
13. Henze, Paul 2001. Eritrea's war : confrontation, international response, outcome, prospects Shama Books, Addis Ababa, Ethiopia
14. Horowitz, Donald L 2003. *The Cracked Foundations of the Right to Secede* Journal of Democracy, 2003, vol. 14, no. 2 (April), pp. 5-17
15. Horowitz, Donald L.1991. *Electoral Systems for a Divided Society* A Democratic South Africa? Constitutional Engineering in a Divided Society, 1991, chap. 5, pp. 163-203
16. Laitin, David 1985 *Hegemony and Religious Conflict: British Imperial Control and Political Cleavages in Yorubaland* Bringing the state back in (edited by Peter B. Evans, Dietrich Rueschemeyer, Theda Skocpol), pp. 285-316
17. Human Rights Watch World Report 1993
18. Lieberman, Evan 2009. Boundaries of contagion : how ethnic politics have shaped government responses to AIDS, Princeton, N.J. : Princeton University Press
19. Lijphart, Arendt 1977. *Consociational Democracy* Democracy in Plural Societies, pp. 25-103

20. Marcus, Harold 2002. A History of Ethiopia: Updated Edition, University of California Pres, Berkley and Los Angeles, California
21. National Atlas of Ethiopia, November 20th, 2007
22. Norris, Pippa (2009) "Consensus Institutions, Ethnic Fractionalization, and Good Governance: Reexamining the links" *Paper presented at the annual meeting of the International Studies Association, Hilton Hawaiian Village, Honolulu, Hawaii*, Mar 05, 2005 <Not Available>. 2009-11-01 http://www.allacademic.com/meta/p69408_index.html
23. Ofcansky, Thomas P and Berry, LaVerle, editors. *Ethiopia: A Country Study*. Washington: GPO for the Library of Congress, 1991 http://countrystudies.us/ethiopia/11.htm , (Library of congress).
24. Pankhurst, Richard 1997. The Ethiopian Borderlands: Essays in Regional History from Ancient times to the end of the 18th Century., the Red Sea Press, Inc, Lawrenceville, NJ
25. Reilly, Benjamin 2001. *Introduction: Democracy in Divided Societies* Democracy in divided societies [electronic resource] : electoral engineering for conflict management Rothchild, Donald and Philip G.
26. Roeder *Power Sharing as an Impediment to Peace and Democracy*, Sustainable Peace: Power and Democracy After Civil Wars, edited by Philip G. Roeder and Donald Rothchild, 2005, pp. 29-50
27. Sambanis, Nicholas 2001. *Do Ethnic and Non-Ethnic Civil Wars Have the Same Causes?* Journal of Conflict Resolution, 1002, vol. 45, no. 3, pp. 259-282
28. Teshale Tibebu, 1995, The Making of Modern Ethiopia (1896-1974), The Red Sea Press, Inc., NJ
29. Trimingham, J. Spencer, 1952, Islam In Ethiopia, Oxford University Press, UK
30. Turton, David eds 2006. Ethnic Federalism, the Ethiopian Experience in Comparative Perspective Addis Ababa University Press, Ethiopia
31. Varshney, Ashutosh, 2002, *Ethnic Conflict and Civic Life* http://site.ebrary.com/lib/princeton/Doc?id=10170068
32. Vaughan, Sarah 2003. Ethnicity and Power in Ethiopia,University of Edinburgh http://www.era.lib.ed.ac.uk/bitstream/1842/605/2/vaughanphd.pdf
33. Young, Crawford *Chapter 2: The Varieties of Cultural Pluralism* The Politics of Cultural Pluralism, 1975, chap. 2

---

[1] ሕዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ

[2] የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት (1987) አንቀጽ 46፣ የሕዝብ አሰፋፈር፣ ቋንቋ፣ ማንነት እና ፈቃድ ክልሎችን ማዋቀሪያ መስፈርት መሆኑን ይገልፃል፡፡

[3] Teshale Tibebu (1995) ገጽ xi

[4] በመጽሐፉ ከተገለጹት የጊዜ ሰሌዳዎች ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል፡፡ በአንድ በኩል የኢትዮጵያ ታሪክ ሶስት ሺህ አመታት የቆየ ነው የሚለውን የሚወስዱ ሲኖሩ በሌላ በኩል ደግሞ የኢትዮጵያ ታሪክ የመቶ አመት ታሪክ ነው፤ ታሪኩም መጀመር ያለበት አፄ ምኒሊክ ለኢትዮጵያ ዘመናዊ የሆነ ቅርጽ ከሰጧት በኋላ ነው የሚሉ አሉ፡፡

አንዳንድ የታሪክ ሰዎች የኢትዮጵያን ታሪክ ሲጽፉ አፄ ቴዎድሮስ የነገሱበትን ጊዜ የዘመናዊዋ ኢትዮጵያ ታሪክ መጀመሪያ አድርገው ይወስዳሉ፡፡ ሌላው የጊዜ ሰሌዳ ደግሞ በአፄ ኃይለ ስላሴ ዘመነ መንግስት ኤርትራ የኢትዮጵያ ፌደራል አባል ሆና ከተቀላቀለችበት ጊዜ የሚጀምር ነው፡፡

[5] ከዚህ ጽሑፍ ርዕስ ውስንነት አንፃር፣ ያደጉትም ሆነ በማደግ ላይ ያሉ አገራት የተፈጠሩት በጦርነት ስለመሆኑ በሰፊው ማቅረብ ባይቻልም ይህንን የሚያመለክቱ በርካታ ጽሑፎች መኖራቸው ይታወቃል፡፡

[6] Trimingham (1952) ገጽ 5፣ Marcus (1994) ገጽ 1 እና ተከታዩቹ ገፆች ስለአጀማመሩ ያብራራሉ፡፡

[7] Trimingham (1952) ገጽ 6

[8] ወደኤርትራ የሄዱ አገዎች የሚባሉት

[9] Trimingham (1952) ገጽ 6

[10] እዛው

[11] እዛው ገጽ 6-7

[12] እዛው ገጽ 32 - ሌሎች በአክሱም ስልጣኔ ላይ ከደቡብ አረቢያ ከፈለሱት ሕዝቦች በተጨማሪ ጥልቅ የባሕል ተጽእኖ የነበራቸው ግሪኮችና አይሁዶች ነበሩ፡፡

[13] እዛው - ከክርስቶስ ልደት በፊት በነበረው በ3ኛው ክፍለ ዘመን በተለይ ከየመን የመጡት ሀበሻቶች በኤርትራና በትግራይ ግዛታቸውን ማጠናከራቸው ይነገራል፡፡

[14] እዛው ገጽ 7

[15] የአክሱም ዘመነ መንግስት ሊዳከም የቻለበት አንዱ ዋና ምክንያት በአክሱም ቁጥጥር ስር የነበሩት የባህር ንግድ መንገዶች በሙስሊም ኃይሎች መያዛቸው ነበር፡፡ ሁለተኛው ዋና ምክንያት ደግሞ በወቅቱ አረማዊ (pagan) የነበሩት የቤጃና የሳሆ አርብቶ አደር ጐሳዎች የባህር ዳርቻዎችንና ከፍ ያሉ ሜዳማ ቦታዎችን መያዛቸው ባስከተለው የባሕር ንግድ መንገዶች አስተማማኝ አለመሆን ነበር፡፡ Trimingham (1952) ገጽ 47

[16] አማራ እዚህ ላይ ብሔር ሳይሆን የቦታ ስም ነው፡፡

[17] ሶማሌዎች በመጀመሪያ አሁን የእንግሊዝ ሶማሊላንድ በመባል ወደምትታወቀው ቦታ ተወስነው ሰፍረው ነበር፡፡

[18] ወደዋቢ ሽበሌ ሽለቆ

[19] Trimingham (1952) ገጽ 8

[20] እዛው ገጽ 6

[21] የኦርቶዶክስ ክርስትና ሃይማኖት ይፋ የሆነ የአክሱም ሃይማኖት የተደረገው በንጉስ ኢዛና ጊዜ በ4ተኛው ክፍለ ዘመን ነበር፡፡ ይህም የግሪክ ስልጣኔ በወቅቱ ከነበረው የበላይነት ጋር የተያያዘ ሲሆን አክሱም ከሜዲቴራኒያኑ ዓለም (ማለትም በወቅቱ በኦርቶዶክስ ክርስትና ተጽዕኖ ስር ከነበሩት ከግሪክ፣ ከግብጽ፣ ከባይዘንታይን ወዘተ) ጋር የባሕል ትስስር እንዲኖራት ማገዙ ይነገራል፡፡ ሆኖም በ7ተኛው ክፍለ ዘመን እስልምና (የተለያዩ ጐሳዎች በነበሯቸው) አረቦች መካከል ፖለቲካዊ አንድነትን ሊያመጣ ችሏል፡፡ ኢትዮጵያም በዚሁ ዘመን እስልምና ቀድሞ ከገባባቸው አገሮች መካከል አንዷ መሆኗ ይታወቃል፡፡ ታላቅ የነበሩት የባይዘንታይንና የፐርሺያ ግዛቶች ከመቶ አመታት በላይ የቆየ የእርስ በርስ ውጊያ ከማድረጋቸው ብዛት ተዳክመው በነበረበት በዚያ ወቅት አዲስ በነበረው የእስልምና ሃይማኖት አንድ የሆኑት አረቦች የፈፀሙት ኃይለኛ ጥቃት ግዛቶቹ እንዲወድቁ አድርጓል፡፡ ግብጽ፣ ሶሪያና ፍልስጤም በጦርነት ድል ተደርገው ከተያዙ በኋላ ሙስሊም ሃገሮች ሊሆኑ ችለዋል፡፡ በሱዳንም ከባድ ጦርነቶች ከተደረጉ በኋላ በ13ኛው ክፍለ ዘመን መጨረሻ ላይ ክርስትና ሃይማኖት በአገሪቱ እንዲጠፋ ተደርጓል፡፡ Trimingham (1952) ገጽ 41-45 በ16ተኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አስርት አመታት በርካታ በጦርነት ወደእስልምና የተቀየሩ አካባቢዎች (ለምሳሌ ግብጽ፣ ሶሪያ፣ ሰሜን አፍሪካ፣ የአረብ ባሕር ዳርቻዎች ወዘተ…) በኦቶማን ቱርኮች ቁጥጥር ስር ተደርገው በእስልምና ሃይማኖት የተሳሰረ የፖለቲካ አንድነት ለመፍጠር ተችሏል፡፡ Trimingham (1952) ገጽ 77

በኢትዮጵያ የእስልምና ሃይማኖት መስፋፋት የጀመረው ከ10ኛው ክፍለ ዘመን ጀምሮ ነበር፡፡ ይህም የሆነው የአክሱም የውጭ ንግድ መንገዶች በሙስሊም ኃይሎች በመያዛቸው እንዲሁም በክርስቲያኖቹና (በወቅቱ አረማዊ ወይም አይሁድ በነበሩት) አገዎች መካከል በነበረው የማያቋርጥ የእርስ በርስ ጦርነት ምክንያት የክርስቲያኑ መንግስት በመዳከሙ ነበር፡፡ (ከጊዜ በኋላ አገዎች በብዛት ወደ ኦርቶዶክስ ክርስትና እንዲቀየሩ መደረጉ ይወሳል፡፡) በወቅቱ የሙስሊም ኃይሎች በቀይ ባህርና በደጋማው ሜዳ መካከል በፍልሰት የሰፈሩትን አርብቶ አደር ሕዝቦች ቀስ በቀስ ወደ እስልምና በመቀየር በክርስቲያኑ መንግስት ላይ አደራጅተውበታል፡፡ ከዚያም እስልምና ወደሲዳማና ወደ ምስራቅ ሸዋ ዘልቆ እንዲገባ አድርገዋል፡፡ በ14ተኛው ክፍለ ዘመን የተወሰኑ የሳሆና የአፋር ቡድኖችና የሱማሌ ጐሳዎችም በአረቦች ወደእስልምና ሊቀየሩ ችለዋል፡፡ Trimingham (1952) ገጽ 60 በክርስቲያንና በሙስሊም መሪዎች መካከል ስልጣን ለመያዝ በሚደረጉ ግጭቶች ጊዜ በሁለቱም ወገን ሕዝቡ ሃይማኖቱን በጉልበት ከአንዱ ወደሌላው እንዲቀይር የተደረጉበት አጋጣሚዎች እንደነበሩ በታሪክ ተመልክቷል፡፡

[22] Trimingham (1952) ገጽ 65

[23] የአህመድ ግራኝ ጦርነት የተካሄደው እ.ኤ.አ. 1524-1543

[24] ‹‹አህመድ ግራኝ›› ሙሉ ስማቸው ኢማም አህመድ ኢብን ኢብራሂም አልጋዚ ነበር፡፡

[25] ኦቶማን ቱርኮች በዘመኑ በወታደራዊ አቅም ታላቅ ነበሩ፡፡ በሜዲቴራኒያንና ቀይ ባሕር አካባቢ የነበረውን ስልታዊ ጠቅሜታ ያለው አካባቢና የንግድ መስመሮችን ለመቆጣጠር የሙስሊም ቱርኮች ተቀናቃኝ የነበረችው ባለተመጣጣኝ ኃይል ካቶሊካዊ ክርስትናዊ ፖርቱጋል ነበረች፡፡

[26] ጠለቅ ብለው ማንበብ ለሚፈልጉ ስለኦሮሞ ሕዝብ ፍልሰት ከተፃፉ በርካታ ጽሑፎች ውስጥ ጌታቸው ኃይሌ (1997)፣ Pankhurst (1997): 284 ፣ Marcus (2002): 37፣ Henze (2001)፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ አትላስ፣ Trimingham (1952) ወዘተ … ማንበብ ይቻላል፡፡
[27] ታላቁ የኦሮሞ ሕዝብ ፍልሰት የተካሄደው እ.ኤ.አ. 1520-1660 (16ኛውና 17ኛው ክፍለ ዘመናት) ነበር፡፡
[28] Pankhurst (1997) ገጽ 278፣ Trimingham (1952) ገጽ 8
[29] Trimingham (1952) ገጽ 94፣ ተክለ ጻድቅ መኩሪያ (2000) ገጽ 94
[30] National Atlas of Ethiopia**, November 20th, 2007**
[31] Ofcansky and Berry 1991 http://countrystudies.us/ethiopia/11.htm
[32] ለምሳሌ ያህል አገውኛ ተናጋሪዎች የሆኑት የዛግዌ ስርዎ መንግስት ከአክሱም ዘመነ መንግስት በኋላ ስልጣን ይዟል፡፡ Marcus (2002) ገጽ 12
[33] Cambridge Encyclopedia Vol. 55, http://encyclopedia.stateuniversity.com/pages/16445/Oromo.html,
[34] Marcus (2002) ገጽ xvii
[35] Vaughan, (2003) ገጽ149
[36] Turton, David eds (2006) ገጽ 119 ላይ ያለው የዶ/ር መረራ ጉዲና Contradictory Interpretations of Ethiopian History: the Need for a New Consensus የሚል ጽሑፍ፡፡
[37] እዛው ገጽ 125፣ Abraham, Kinfe (2004) ገጽ 70
[38] Horowitz (2003) ገጽ 5-6
[39] ስለዚህ ጉዳይ በዝርዝር ለማንበብ Teshale Tibebu (1995) ገጽ 170 እና ተከታታይ ገፆች ያንብቡ፡፡
[40] አፄ ቴዎድሮስ ስለራሳቸው እንደተናገሩት ስልጣን የያዙት ከትቢያ ተነስተው እንጂ በዘር አይደለም፡፡ በአፄዎቹ ዘመን አማራ ያልሆኑ እንደጐጃሙ ፊታውራሪ ሃብተ ጊዮርጊስ ያሉት ባለስልጣኖች ሹመት ማግኘታቸው አይዘነጋም፡፡ በአጠቃላይ ድህነትም ሆነ አማራ አለመሆን ስልጣን ከመያዝ የሚያግድ ጉዳይ አልነበረም፡፡
[41] Teshale Tibebu (1995) ገጽ 172 የመሃመድ ሃሰንን ‹‹Oromo genius for assimilation›› በመጥቀስ
[42] ቀዳማዊ ኃይለ ስላሴ ዩኒቨርሲቲ (በኋላ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተባለው)
[43] Turton, David eds (2006) ገጽ 123 ያለው የዶ/ር መረራ ጉዲና Contradictory Interpretations of Ethiopian History: the Need for a New Consensus የሚል ጽሑፍ
[44] Vaughan, (2003) ገጽ 136
[45] እዛው - ገጽ 136
[46] እዛው - ገጽ 135
[47] ለምሳሌ ዶ/ር አረጋዊ በርሄ፣ አቶ አስገደ ገ/ስላሴ
[48] ከህወሃት መስራች አባላት መካከል አንዱ የሆኑትና በኋላም ከአመራር የተወገዱት ዶ/ር አረጋዊ በርሄ በፃፉት A Political History of the Tigray People's Liberation Front (1975-1991): Revolt, Ideology and Mobilisation in Ethiopia (2008) የሚል ጽሑፍ ገጽ 195 ላይ አቶ አባይ ፀሃዬ፣ አቶ መለስ ዜናዊ፣ አቶ ስብሃት ነጋ እና አቶ ስዩም መስፍን ይህን ትግራይን የመገንጠል አላማ በዋናነት ከሚያቀነቅኑት መካከል እንደነበሩ ገልፀዋል፡፡ በተጨማሪም አቶ ስብሃት ነጋ ሻዕቢያ የሄደበት ዓይነት መንገድ በመምረጥ ትግራይ የኢትዮጵያ ቅኝ ግዛት እንደነበረችና በዚህም ምክንያት ነፃ መውጣት እንዳለባት የሚሟገት አቋም በህወሃት እንዲያዝ ለማድረግ ሞክረው ሳይሳካላቸው መቅረቱን ጠቅሰዋል፡፡
[49] ህወሃት የአሰብን ወደብ ለሻዕቢያ አሳልፎ ሲሰጥ ከሻዕቢያ ጋር ጦር የሚያማዝዝ አለመግባባት ውስጥ እንደሚገባ በፍጹም አልገመተም ነበር፡፡ ስሌቱ የከሸፈው እዚህ ላይ ነበር፡፡ ኢትዮጵያ ባትመቸው ህወሃት ትግራይን ገንጥሎ ሊጠቀመበት ያሰበው የአሰብን ወደብ ነበር፡፡ ሆኖም ይህ አለመግባባት ሰዶ ማሳደድ ቀላል አለመሆኑን ከወዲሁ አስገንዝቦት አልፏል፡፡
[50] ህወሃትና ሻዕቢያ ለዚህ ድል የበቁት በበርካታ ምክንያቶች ነው፡፡ (በተለይ ሻዕቢያ ከአረቦች በሚያገኘው ከፍተኛ እርዳታ ከንጉሱ ጊዜ ጀምሮ የተጠናከረ ከመሆኑ አንፃር) ደርግን በጋራ መውጋታቸው ፣ በአገሪቱ የነበሩት ሕብረ ብሔራዊ ፓርቲዎች በደርግ በመሸነፋቸው፣ የሶሺያሊስታዊ ርዕዮተ ዓለም አራማጅና የደርግ ዋነኛ አጋዥ የነበረችው የሶቪየት ሕብረት መፍረስና ህወሃት የአሜሪካን ድጋፍ ማግኘቱ እንዲሁም አብዛኛው የኢትዮጵያ ሕዝብም የደርግን አስከፊ ስርዓት አለመደገፉ ዋና ዋናዎቹ ምክንያቶች መሆናቸው ይገመታል፡፡
[51] የኢትዮጵያ ሕዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር አባላት የሆኑት ህወሃት (ህዝባዊ ወያኔ ሃርነት ትግራይ)፣ ብአዴን (ብሔረ አማራ ዴሞክራሲያዊ ንቅናቄ)፣ ኦሕዴድ (የኦሮሞ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ

ድርጅት) እና ከተወሰኑ ዓመታት በኋላ የተቋቋመው ደሕዴግ (የደቡብ ሕዝቦች ዴሞክራሲያዊ ግንባር) ናቸው፡፡

[52] Aregawi Berhe, Dr. (2008) - ገጽ 199

[53] ለሁለት አስርት አመታት የህወሃት መሪ የነበሩት አምባገነኑ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስቴር ሚች መለስ ዜናዊ ለማድረግ ያሰቡት ማንኛውም ነገር በነጋታው ያለምንም ክልካይ ሕግ መሆን እንደሚችል ስንታዘብ ኖረናል፡፡ ለምሳሌ የስልጣን ተቀናቃኝ ብለው ያሰቡዋቸው አቶ ስዬ አብርሃ ታስረው እንዲቆዩ ለማድረግ በተለምዶ ‹‹የስዬ ሕግ›› የሚባለውን የፀረ ሙስና ሕግ በአንድ ቀን ውስጥ በተጽዕኖ አስጸድቀው ተግባራዊ ማድረጋቸው አይረሳም፡፡ አሁንም ቢሆን የሚቹ ተተኪዎች ተመሳሳይ እርምጃዎችን ከመውሰድ የሚመለሱ አይደሉም፡፡

[54] ህወሃት በአፋር፣ በጋምቤላ፣ በሱማሌና በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልሎች (ተቃዋሚ ሊባሉ የማይችሉ) አጋር ፓርቲዎችን ማደራጀቱ ይታወቃል፡፡

[55] ለምሳሌ ምንጮችን በመጠቀስ Lovise Aalen (2002) ገጽ 36፣ 47

[56] Turton (2006) ገጽ 157

[57] የኦሮሞ ነፃነት ግንባር

[58] Vaughan, (2003) ገጽ 92

[59] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት (1987) አንቀጽ 40(3)

[60] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት (1987) አንቀጽ 53፣ 54፣ 61ና 62 - በኢትዮጵያ የፌደራል መንግስት ምክር ቤቶች ሁለት ሲሆኑ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤትና የፌደሬሽን ምክር ቤት ናቸው፡፡[60] የተወካዮች ምክር ቤት አባላት በቀጥተኛ ምርጫ በዴሞክራሲያዊ መንገድ መመረጥ ያለባቸው ሕግ አውጪዎች ናቸው፡፡ በአንፃሩ የፌደሬሽን ምክር ቤት አባላት ግን በክልል መንግስታት የሚገኙ ‹‹ብሄሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ሕዝቦች›› የሚወክሏቸው በክልል ምክር ቤቶች የሚመረጡ ሲሆን ተግባራቸው ሕግ ማውጣት አይደለም፡፡

[61] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት (1987) አንቀጽ 46

[62] እዛው፣ አንቀጽ 47

[63] አማራና ኦሮሞ ክልሎች ተብለው የተከለሉት የአገሪቱ ክፍሎች በአብዛኛው አማርኛ እና ኦሮምኛ ተናጋሪ ዜጎች እንዳሉባቸው የሚገመት ሲሆን በደቡብ ክልል ግን አብዛኛው ሕዝብ የሚናገረው አንድ የደቡብ ቋንቋ አለመኖሩ ይታወቃል፡፡ በክልሉ ከ40 በላይ ቋንቋዎች መኖራቸው የሚነገር ሲሆን በታሪክ አጋጣሚ የተለያዩ ቋንቋዎችን የሚናገረው አብዛኛው ሕዝብ እርስበርስ ለመግባባት የሚጠቀመው ቋንቋ አማርኛ ነው፡፡ ከዚህ እውነታ አንፃር በርካታ የፖለቲካ ተንታኞች የሚስማሙበት አንድ ነገር አለ፡፡ ይህም ህወሃት እነዚህን ሁሉ ሕዝቦች በአንድ ‹‹የብሔር›› ክልል ውስጥ ያስገባቸው በአገሪቱ በመጠንና በሕዝብ ቁጥር የበላይነት ያላቸው የአማራና የኦሮሞ ትላልቅ ክልሎችን ከሌሎቹ ክልሎች ጋር በማነጻጸር በተለይም ከስልጣን ጋር በተያያዘ የእነዚህ ክልሎች ውክልና መጉላት ይኖርበታል የሚል ጫና እንዳይደረግበትና ፍጥጫ እንዳይከሰት ነው፡፡ ማለትም የህወሃት (የዘውግ ብሔርተኝነት) አቋም አብዛኛውን የአገሪቱን ዜጋ እንዲወክል ስለማያስችለው በመጠን ከአማራና ከኦሮሞ ክልሎች ጋር ተመጣጣኝ ሊሆን የሚችለውን የ‹‹ደቡብ›› ክልል የከለለው በዚህ ምክንያት መሆኑ ይታመናል፡፡

[64] Aregawi Berhe, Dr. (2008) - ገጽ 201 ላይ በተለይ የአቶ ስብሃት ነጋ ቡድን ከአማራ ጋር አብሮ መኖር እንደማይቻል ለማሳመን ጥረት ያደርግ እንደነበረ ተመልክቷል፡፡

[65] ለምሳሌ አማራን ‹‹እንዳያንሰራራ አድርገን አከርካሪውን ሰብረነዋል፡፡›› የሚለው አባባል የዚህ ግልጽ አመላካች ነው፡፡

[66] ከነዚህ በደሎች መካከል፡-

1. ከጐንደርና ከወሎ (በአሁኑ አጠራር ከአማራ ክልል) ወደ ትግራይ ክልል መሬቶችን በጉልበት መጠቅለሉ፣ አማርኛ ተናጋሪዎችን አባሮ የትግራይ ሰዎችን በብዛት በቦታው ማስፈሩ፣
2. ለፖለቲካ ጥቅሙ ሲል ከጐንደር መሬት ቆርሶ ለሱዳን መስጠቱ፣ (ይህ ለአገሪቱ ሉአላዊነት መከበር ደንታ የሌለውና ‹‹የአክሱም ሃውልት ለወላይታ ሕዝብ ምኑ ነው?›› የሚለው ዓይነት ከፋፋይና ዘረኛ ቡድን መሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡)
3. በተለይም ትግርኛና ኦሮምኛ ተናጋሪ ሕዝቦች አማርኛ ተናጋሪውን እንዲጠሉ ለማድረግ ተግቶ መስራቱ፣
4. ከአማራ ክልል ውጭ ተወልደው ያደጉ እንዲሁም ለብዙ ትውልዶች የኖሩትን አማርኛ ተናጋሪዎች ማፈናቀሉ፣ እንዲሁም ለስቃይና ለሞት መዳረጉ፣

5. በቁጥጥሩ ስር በተካሄደ የሕዝብ ቆጠራ (አሳማኝ ማስረጃ ሳይኖረውና ለፖለቲካ ጥቅሙ ሲል) የአማርኛ ተናጋሪው ሕዝብ ቁጥር ከቀድሞው ጋር ሲወዳደር በመቶኛ ያለው ድርሻ እንደቀነሰ ማስፈሩ ይገኙበታል፡፡

ህወሃት ከተጠናወተው የ<<አማራ>> ጥላቻ አንፃር እነዚህን መሠሪ ተግባራት ማከናወኑ የሚገርም አይደለም፡፡ እነዚህን ፈጻሚዋቹ የጥንት አውሮፓውያን ቅኝ ገዢዎች ቢሆኑ ብዙም አይደንቅም ነበር፤ ግን የአንድን አገር የመንግስት ስልጣን የያዘ ከአገሪቱ የወጣ ቡድን ይህን ሲያደርግ እጅግ ያሳዝናል፡፡

[67] Teshale Tibebu (1995) ገጽ 176

[68]Turton (2006) ገጽ 146 ያለው የዶ/ር አሰፋ ፍስሐ The Theory versus Practice in the Implementation of Ethiopia's Ethnic FederalismContradictory Interpretations of Ethiopian History: the Need for a New Consensus የሚል ጽሑፍ

[69] Tesfaye, Aaron (2002) ገጽ125

[70] Turton (2006) ገጽ 56 ያለው የዊል ኪምሊካ Emerging Western Models of Multination Federalism: Are they Relevant for Africa? የሚል ጽሑፍ

[71] የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት (1987) አንቀጽ 5 ክልሎች የሥራ ቋንቋቸውን የመወሰን መብት እንዳላቸው ደንግጓል፡፡

[72] የኢፌዴሪ ሕገ መንግስት (1987) አንቀጽ 5

[73] Arel & Kertzer (2002) ገጽ 2

[74] 'a set of exhaustive and mutually exclusive ethnic nationalities' የሚለውን የብሩቤከር ሃሳብ በመጠቀም የኢትዮጵያን ሁኔታ ለማስቀመጥ ነው፡፡ Brubaker (1996) ገጽ 18

[75] አካባቢ፣ ብሔር፣ ሃይማኖት፣ ጐሳ፣ መደብ፣ ፆታ ወዘተ

[76] ለምሳሌ ከቀድሞው በተለየ ሁኔታና በህወሃት የዘር ፖለቲካ ምክንያት በአሁኑ ጊዜ ሁለት የማይተዋወቁ ኢትዮጵያውያን በማንኛውም አጋጣሚ ሲገናኙ (በግልጽ መጠየቅ ባይወዱም) አንዱ ስለሌላው ለማወቅ የሚፈልገው የመጀመሪያው መረጃ የብሔር ማንነትን የሚመለከት መሆኑ እየታየ ነው፡፡

[77] የመጀመሪያው ከኤርትራ ጋር የተደረገው የድንበር ጦርነት እንደተነሳ ነው፡፡ በዚህ ወቅት ህወሃት/ኢሕአዴግ የብሔር ልዩነትን ወደጐን በመተው (ከዚያ በፊት ሲያንቋሽሸው የነበረውን) አገራዊ ብሔርተኝነትና የሃገር ፍቅር ስሜት በድንገት አጽንኦት ሲሰጠው ታይቷል፡፡ የዚህ ድንገተኛ የአቋም ለውጥ ምክንያት የአገሪቱን ወጣቶች ቀስቅሶ ውጤታማ የሆነ ማዕከላዊ ወታደራዊ እንቅስቃሴ በማድረግ የኤርትራን ጦር ማሸነፍ የሚቻልበት መንገድ ይህ ብቻ መሆኑን በመገንዘቡ ነበር፡፡

ህወሃት/ኢሕአዴግ አገራዊ ብሔርተኝነት ላይ እንዲያተኩር ያስገደደው ሁለተኛው ምክንያት ደግሞ በ1997ቱ አገር አቀፍ የፖለቲካ ምርጫ ላይ በምርጫው ያሸነፉት (በኋላ ቢታሰሩም) አገራዊ ብሔርተኝነትን ያቀነቀኑ ኃይሎች መሆናቸውን በመገንዘቡ አቋሙን ቢያንስ በውጭ በሚያሳየው ገጽታው ላይ ሊቀይር ችሏል፡፡ ይህን ያደረገው ከቀድሞው ስህተቱ ተምሮ የሕዝቡን ፍላጐት ያሟላ ለማስመሰልና ሕዝቡን የምወክለው ፓርቲ (አውራ ፓርቲ) እኔ ብቻ ነኝ ለማለት የተጠቀመበት አንዱ መንገድ ነው፡፡ ከልብ የተደረገ ስላልሆነ አሳማኝ አይደለም እንጂ!

(ለምሳሌ ህወሃት/ኢሕአዴግ ለአገሪቱ ሰንደቅ ዓላማ ክብር እንደማይሰጥ ይታወቅ ነበር፡፡ በአንድ ወቅት ሟቹ የቀድሞ ጠቅላይ ሚኒስቴር ባንዲራውን ጨርቅ ነው ማለታቸው በርካታ ኢትዮጵያንን አሳዝኖ እንደነበረ ይታወሳል፡፡ ዘረኝነታቸው ከመብዛቱና ከጋራ ኢትዮጵያዊነት ይልቅ የብሔር ልዩነት ላይ ማተኮራቸውን የሚያሳየው ሌላ ምሳሌም ‹‹የአክሱም ሃውልት ለወላይታ ሕዝብ ምኑ ነው?›› በማለት የኢትዮጵያ ሕዝቦች እርስ በርስ በጋራ የሚያኖራቸው ሁኔታ እንደሌለ ለማሳየት መሞከራቸው ነው፡፡ ሆኖም ከዚያ በኋላ የባንዲራ ቀን ያወጁ ሲሆን የባንዲራ አጠቃቀምን በተመለከተ (ከዚህ በፊት ባልታየ ሁኔታ) የኢሕአዴግ አርማ ያለው ባንዲራ ካልሆነ በስተቀር ሕዝቡ ባንዲራውን ለማውለብለብ እንዳይችል በአዋጅ ከልክለውታል፡፡ )

[78] Eller & Coughlan (1993) ገጽ 186 ላይ Geertz (1973) ገጽ 259ን በመጥቀስ

[79] Chandra (2001) ገጽ 7

[80] Eller & Coughlan (1993) ገጽ 2001, Horowitz (2002)

[81] Chandra (2001) ገጽ 8

[82] Gudina (2003) ገጽ 23, Young (1975) ገጽ 40

[83] Chandra (2001) ገጽ 7

[84] በዚህ አገባብ ወሰን የሚለው “boundary” የሚለውን ሃሳብ ለመግለጽ ሲሆን ይህም ማለት “አንድ ነገር ሌላ ነገር የሚሆንበት ነጥብ … ‹‹እኛ›› የሚለው አልቆ ‹‹እነሱ›› የሚለው የሚጀምርበት’’ ለማለት ነው፡፡ (Lieberman (2009) ገጽ 28 /29 ላይ Migdal (2004)ን በመጥቀስ

[85] ( Lieberman (2009) ገጽ 28 “Only through an institutional framework (formal or informal) for mobilizing the boundaries between groups can groups become socially or politically relevant. The salience of ethnic groups in the political arena depends on ethnic boundaries.’’

[86] የኢ.ፌ.ዴ.ሪ ሕገ መንግስት (1987) አንቀጽ 41

[87] Baseline Survey (2008)

[88] እዛው

[89]Turton (2006) ገጽ167. አማርኛ ለብዙ ዘመናት የኢትዮጵያ ብሔራዊ የመግባቢያ ቋንቋ በመሆን አገልግሏል፡፡ ለምሳሌ በአፄ ዮሃንስ 4ተኛው ዘመነ መንግስት ንጉሱ ከትግርኛ ይልቅ አማርኛን የቤተ መንግስታቸው የይፋ ቋንቋ አድርገው በመጠቀም ጠባብ (parochial) አገዛዝ እንዳይሆን ለማድረግ ሞክረዋል፡፡ Amharic has been used as the lingua franca of Ethiopia for centuries. For instance, the Ethipian Emperor Yohannes IV of Tigray (1872-1889) had tried ‘to avoid becoming a Tigrean monarch by making Amharic, not Tigrinya, the official language at his court.’ (Vaughan (2003) ገጽ110

[90] ትግራይ፣ አፋር፣ አማራ፣ ኦሮሞ፣ እና ሱማሌ

[91] Turton (2006) ገጽ136

[92] እዛው

[93] እዛው ገጽ 202

[94] እዛው ገጽ 200 ያለው የደረጀ ፌይሳ <u>Experience of Gambella Regional State</u> የሚለው ጽሑፍ ላይ ለምሳሌ በጋምቤላ ክልል የሚገኙት ‹‹ደገኞች›› መጤ የሚባሉ በመሆኑ ከብዛታቸውና ካላቸው የኢኮኖሚ ተጽእኖ አንፃር ከክልሉ የፖለቲካ ሂደት በመገለላቸው ብጥብጥ መነሳቱን ይገልፃል፡፡ Turton (2006) ገጽ 226

[95] ለምሳሌ በግልጽ የተከለለ የብሔር ቡድኖች ወሰን የሌለ መሆኑ፣ በወታደራዊ ኃይል የበላይነት ምክንያት የሚካለሉ የብሔር ቡድን ወሰኖች ቢኖሩም እንኳን በእነርሱ ወሰኖች ውስጥ በክልሉ የበላይነት ካገኘው ብሔር ውጭ የሆኑ ሰዎች ስለሚኖሩ በእነሱ ላይ የማግለልና እስከዘር ማጥፋት ሊደርስ የሚችል በደል የሚፈጸም በመሆኑ ዘላቂ ሰላም ሊመጣ አለመቻሉ ወዘተ.

[96] ብሔር ተኮር ያልሆኑ አማራጮችን የሚመለከተው የዚህ ጽሑፍ ክፍል በብሔር ቡድን መገንጠል ዘላቂ መፍትሔ ሊያመጣ እንደማይችል ያብራራል፡፡

[97] አንዳንድ ብሔር ተኮር ልሂቃን የካናዳ፣ የስዊዘርላንድና የቤልጄየምን የመንግስት አወቃቀር ልምዶች በመጥቀስ ከብሔር ተኮሩ ፌደራሊዝም ጋር የተመሳሰሉ በመሆናቸው ለኢትዮጵያም ሊያገለግሉ ይችላሉ ብለው ይከራከራሉ፡፡ ሆኖም እነዚህ አገሮች ቢበዛ ሁለት ወይም ሶስት ቋንቋዎች ብቻ በስፋት የሚነገሩባቸው ከመሆናቸውም በላይ የበለጸጉና ዴሞክራሲያዊ ስርዓት የሰፈነባቸው እንዲሁም የዜጐች ሰብዓዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ከብሔር ተኮር አድሎ በፀዳ ሁኔታ የሚከበሩባቸው በመሆናቸው ልምዳቸው ከኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ጋር የተቀራረበ አይደለም፡፡ በኢትዮጵያ 80 ቋንቋዎች የሚነገሩ ቢሆንም 80ዎቹንም በአገር አቅፍ ደረጃ የሚያገለግሉ የመግባቢያ ቋንቋዎች ለማድረግ የሚቻል አለመሆኑ ይታወቃል፡፡

[98] ለምሳሌ እ.ኤ.አ. በ1993 ዓ.ም. የወጣው የሂዩማን ራይትስ ዋች የዓለም ሪፖርት ላይ እንደተገለጸው ህወሃት ስልጣን ከያዘ በኋላ (እ.ኤ.አ. ዲሴምበር 1991 ዓ.ም.) በወቅቱ የሽግግር መንግስቱ አካል የነበረው ኦነግ ኦሮሚያ ክልል ራሱን በራሱ ያስተዳድራል በሚል መተማመን በሐረርጌ ክፍለ ሃገር በሚኖሩ አማርኛ ተናጋሪዎች ላይ ረብሻ ያነሳሳ ሲሆን ደጋፊዎቹ ለጭፍጨፋው (ብዙ ሰዎችን በአንዴ ለመግደሉ) ኃላፊነት እንዳለባቸው ማመኑ ተገልጿል፡፡ December 1991 when the OLF, then part of the transitional government assured of Oromia’s autonomy, incited violence against the Amhara in Harerghe province and admitted that its supporters were responsible for the massacre Human Rights Watch World Report 1993, pages 11-1፤ በብሔር ልዩነት ምክንያት በየክልሉ በርካታ በደሎች ሲፈጸሙ የቆዩ ሲሆን ቀረብ ያሉትን ለመጥቀስ ያህል ከኦሮሚያ ክልል የተፈናቀሉትን ሲዳማዎች፣ ከደቡብ ክልል የተፈናቀሉትን አማርኛ ተናጋሪዎች ምሳሌ ለመስጠት ይቻላል፡፡

[99] Horowitz (2003) ገጽ 9

[100] Laitin (1985) ገጽ 312

[101] ቀረብ ያሉት አገዛዞች ላይ ስናተኩር የደርግም ሆነ የህወሃት/ኢሕአዴግ መሪዎች ስልጣን የያዙት በጉልበት እንደሆነ ይታወቃል፡፡ ከዚያም በኋላ ደርግ በግልጽ የአንድ ፓርቲ አገዛዝ በማስፈን ህወሃት/ኢሕአዴግ ደግሞ ምዕራባውያንን ለማጭበርበር በሕገ መንግስቱ ላይ የሊበራል ዴሞክራሲያዊ ስርዓትን የደነገገ ቢሆንም

የይስሙላ ምርጫ እያካሄደ አገሪቱን በኃይል በመግዛት ላይ ይገኛል፡፡ በሁለቱም አገዛዞች ዜጎች ብሶታቸውን በነፃነት ገልጸው መፍትሔ የሚያገኙበት መንገድ አልነበረም/የለም፡፡

[102] ከዚህ ጋር በተያያዘ በምርጫ ማጭበርበር፣ ተቃዋሚዎችን ማዋከብ፣ ማሰርና መግደል ወይም ከአገር እንዲወጡ ግፊት ማድረግ ዋና ዋናዎቹ የህወሃት ተግባሮች ናቸው፡፡ ይህንንም የሚያደርገው በዋናነት ሃሳብን በነፃነት የመግለጽና የመደራጀት መብቶችን ያላግባብ የሚገድቡ ሕጎችን በማውጣትና ሕጎቹን ምክንያት አድርጎ ዜጎችን በማሰር እንዲሁም ዜጎች ሊወሰድ የሚችለውን እርምጃ ፈርተው የተቃውሞ እንቅስቃሴ እንዳያደርጉ በመከላከል ነው፡፡ ህወሃት አፈናውን የሚፈጽመው በፕሬስ ፣ በበጐ አድራጐት ድርጅቶች፣ በፀረ-ሽብርተኝነትና በመሳሰሉት ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴን ለመግታት ያወጣቸው ሕጐቹ መሠረት ነው፡፡

[103] Sambanis (2001) **ገጽ** 267

[104] Varshney (2002) **ገጽ** 93

[105] ሴንትሪፔታሊዝም ሶስት መልኮች አሉት፡ 1) የራስ ካልሆኑ የብሔር ቡድኖች የምርጫ ድምጽ ለማግኘት የሚያበረታታ በመሆኑ ወደ ለዘብተኝነት ሊመራ ይችላል፡፡ 2) የተለያዩ የብሔር ቡድኖችን በሚወክሉ ፖለቲከኞች መካከል የምርጫ ድምጽ ስምምነቶች እንዲኖሩ እድሉን ያመቻቻል፡፡ 3) በተለያዩ መንገዶች በብሔር ፖለቲከኞች መካከል የምርጫ ድምጽ ግንኙነቶችን ፈጥሮ እንዲተባበሩ በማድረግ የተለያዩ የፖሊሲ አማራጮች እንዲኖሩ ያደርጋል፡፡ Reilly (2001) **ገጽ** 11

[106] Lijphart (1977) **ገጽ** 25

[107] እዛው ገጽ 31

[108] ከተቺዎቹ መካከል ሮዝቻየልድ እና ሮደር ይገኙበታል፡፡ እነርሱም የዚህ ዓይነት የስልጣን መጋራት የማያመጡዋቸው ሰባት አደጋዎች ብለው የሚከተሉትን ነጥቦች አስቀምጠዋል፡- 1) ዴሞክራሲን የመገደብ 2) የስልጣን መጋራቱን ስምምነት ራሱን መጋፋት የሚችሉትን የብሔር ቡድን መሪዎችን ስልጣን የማረጋገጥ 3) የብሔር ቡድኖችን የሚከፋፍሏቸው (የሚለዩዋቸው) ጉዳዮች ዋና ጉዳዮች እንዲሆኑ የማድረግ 4) ተለዋዋጭ የልሂቃን ግፊቶች 5) በውክልና መስፋፋት (መለጠጥ) ምክንያት አጥጋቢ ውጤት የማይሰጥ መንግስት 6) በየጊዜው ለሚለወጡት ማህበራዊ ሁኔታዎች መንግስት የማይናወጽ መሆን (ምቹ አለመሆን) እና 7) በብሔር ተኮር ልሂቃን የጥቅመኝነት ዓመል ምክንያት የሚመጣ በቂ ያልሆነ አፈፃፀም ናቸው፡፡ Rothchild and Roeder (2005) **ገጽ** 36

[109] Horowitz (2003) **ገጽ** 15

[110] በዚህ መሠረት ላይኘሃርት በመስፈርት አስቀድመው ከሚደራጁ (predetermination of groups) ቡድኖች ይልቅ በሕዝቡ ፍላጐት የሚደራጁት የተሻሉ መሆናቸውን የሚያመለክቱ አራት ምክንያቶችን አስቀምጠዋል፡- (1) አስቀድመው እውቅና ያላገኙ ቡድኖች ላይ አድሎ መፈጸሙ የማይቀር መሆኑ፣ (2) ዜጎች አስቀድመው የተወሰኑትን ቡድኖች እንዲቀላቀሉ ሰው ሰራሽ በሆነ መንገድ የሚያስገድድ መሆኑ፣ (3) የተደራጁትን ማህበራዊ ቡድኖች የማይቀበሉ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች ምንም ዓይነት ውክልና ማግኘት አለመቻላቸው፣ እና (4) የቡድኖችን የውክልና መጠን የመወሰኑ ሂደት ጠንካራ የግትርነት አዝማሚያ (strong tendency of rigidity) ያለው መሆኑ ናቸው፡፡ ለማጠቃለልም የብሔር ማንነቶች በአብዛኛው ግልጽ ካለመሆናቸውም ሌላ ተለዋዋጭ (very often unclear and fluid, and flexible) በመሆናቸው ምክንያት በመስፈርት አስቀድመው ከሚደራጁ ቡድኖች ይልቅ በሕዝብ ፍላጐት የሚደራጁ ቡድኖች የተሻለ ውጤታማ ይሆናሉ፡፡ Lijphart (2001) **ገጽ** 12

[111] Horowitz (2003) **ገጽ** 15

[112] ድምጽ የማሠራጨት መስፈርቶች የምርጫ ድጋፍን ለማስፋትና የአናሳዎችን መብቶች ለመጠበቅ ይጠቅማሉ፡፡ ለዚህ አንዱ ምሳሌ ከመደበኛው የድምጽ ብልጫ በተጨማሪ ከአጠቃላዩ ድምጽ መካከል ለድምጽ ስርጭት አነስተኛ የመቶኛ ድርሻ እንዲኖር የሚያደርግ መስፈርት መጠቀም ነው፡፡ 'standard of plurality plus distribution treshholds in some percentage of the total number of wards or electoral divisions.' (Horowitz (1991) **ገጽ** 186

[113] እዛው ገጽ 166

[114] እዛው ገጽ 167

[115] እዛው ገጽ 233

[116] ለምሳሌ **Norris, Pippa (2009) "Consensus Institutions, Ethnic Fractionalization, and Good Governance: Reexamining the links"** የሚለው ጽሑፍ ይገኝበታል፡፡

[117] ህወሃት ለአማርኛ ተናጋሪው ሕዝብ ካለው ጥላቻ አንፃር የፌደራል በጀትን በሚመለከትም ሆነ በሌላ መልኩ ያ ህዝብ ጥቅም እንዲያገኝ ወይም በስልጣን እንዲቀናቀነው ስለማይፈልግ  እራሱ ባሰራቸው የሕዝብ ቆጠራ ውጤቶች ላይ የዚህን ሕዝብ ቁጥር የመቀነስ ፍላጐት እንዳለውና ይህንንም እንደፈጸመ በሰፊው ይታመናል፡፡

[118] Turton (2006) ገጽ 233 ላይ ያለው የክሪስቶፈር ክላፋም ማጠቃለያ (መውጫ)